የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነት እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ትንተና (ከ1966-1986 ዓ.ም.)

በ

ተሾመ ብርሃኑ

ጥር፣ 2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ትንተና (ከ1966-1986 ዓ.ም.)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት

በ
ተሾመ ብርሃኑ

አማካሪ
አየለ ፍቅሬ (PhD)

2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ትንተና (ከ1966-1986 ዓ.ም.)

በ

ተሾመ ብርሃኑ

2015 ዓ.ም

የፈታኝ ቦርድ አባላት

አማካሪ ፡_____________________________ፊርማ________________

የውጭ ፈታኝ፡ ________________________ፊርማ ____________

የውስጥ ፈታኝ፡ ____________________________ፊርማ__________

# ምስጋና

ከሁሉ በፊት ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን፡፡ በመንገዴ ሁሉ፥ ሳይገባኝ የምታርመኝ፣ ሁሌም ውጥኔ ዳር ይደርስ ዘንድ ብርታት የምትሰጠኝ አንተ ነህና፥ ክበር ተመስገን፡፡

ይህን ጥናት በማረምና ፈጣን ምላሽ በመስጠት በቀና መንፈስ ያገዙኝ አማካሪዬ አየለ ፍቅሬ(Ph.D.) ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት ግብአት፤ በሸክላና በካሴት የታተሙ ዘፈኖችን ከከበረ ክምችቱ ያለገደብ እንድጠቀም እድሉን ያልነፈገኝ መስሪያ ቤቴ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ምስጋና ይድረሰው፡፡

እንዲሁም፤ በተለያየ መንገድ ለዚህ ጥናት የሚሆኑ ዘፈኖችን፣ መጽሐፍትንና ሌሎች መረጃዎችን በመጠቆም ላገዛችሁኝ የስራ ባልደረቦቼና ወዳጆቼ ሁሉ እንሆ የከበረ ምስጋዬን ተቀበሉ፡፡

በመጨረሻም፤ ሁሌም ለትጋት የምታነሳሺኝ፥ በደከምኩበት ጊዜ ሁሉ፤ “አለሁልህ” ብለሽ የምታበረቺኝ ውድ ባለቤቴ እፀገነት ሞላልኝ፥ ይህ ጥናት ያንቺ የመንፈስ ስንቅ ውጤት ነውና፤ እጅግ የተከበረ ምስጋናዬ ይድረስሽ፡፡

ማውጫ ገጽ

አሕጽሮተ ጥናት ..... i
ምዕራፍ አንድ ..... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ..... 4
1.3. የጥናቱ ዓላማ ..... 5
**1.3.1. የጥናቱ አቢይ ዓላማ** ..... 5
**1.3.2. የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች** ..... 5
1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ..... 6
1.5. የጥናቱ ፋይዳ ..... 6
1.6. የጥናቱ ወሰን ..... 6
1.7. የጥናቱ አደረጃጀት ..... 8
1.8. የጥናቱ ዘዴ ..... 8
**1.8.1. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች** ..... 9
**1.8.2. የጥናቱ ናሙና አመራረጥ** ..... 9
ምዕራፍ ሁለት ..... 11
ክለሳ ድርሳናት ..... 11
2.1. ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ ..... 11
**2.1.1. የዓለማዊ (Secular) ሙዚቃ መሠረቶች በኢትዮጵያ** ..... 11
**2.1.2. ዘመናዊ ሙዚቃ በኢትዮጵያ** ..... 12
**2.1.3. ለውጥና ሙዚቃ** ..... 16
**2.1.4. የዘፈን ግጥሞች (Lyrics)** ..... 16
**2.1.5. የዘፈን ግጥሞች ጭብጥና ተግባር** ..... 18
2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ..... 19
**2.2.1. ተግባራዊነት (Functionalism)** ..... 19
**2.2.2. ለውጥ በተግባራውያን እይታ** ..... 21
2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 23
ምዕራፍ ሶስት ..... 30
የለውጥ ሰሞን የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ትንተና ..... 30
3.1. የለውጥ ዋዜማ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ጭብጦች ..... 30

**3.1.1. የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች** 30

**3.1.2. የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች** 34

3.2. የለውጥ ጊዜ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦች ........ 41

**3.2.1. የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ጊዜ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች** ... 41

**3.2.1.1. የድጋፍ ዘፈኖች** ........ 44

**3.2.1.2. እምነት ማጣትና ጥርጣሬ** ........ 46

**3.2.2. የ1983 ዓ.ም የለውጥ ጊዜ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች** .... 51

3.3. የለውጥ ማግስት የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች ........ 57

**3.3.1. የ1966 ዓ.ም የለውጥ ማግስት ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈን ዋና ዋና ጭብጦች** ........ 57

**3.3.2. የ1983 ዓ.ም. ለውጥ ማግስት የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ጭብጦች** ........ 60

ምዕራፍ አራት ........ 66

ማጠቃለያ ........ 66

የዋቢ ጽሑፎች መዘርዝር ........ 69

አባሪዎች ........ 73

# አሕጽሮተ ጥናት

ይህ ጥናት፥ በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ትንተና (ከ1966-1986 ዓ.ም) በሚል ርዕስ የተደረገ ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ፥ በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ለውጡን በተመለከተ ያነሷቸውን አቢይ ጭብጦች በመተንተን የተገኘውን ውጤት ማቅረብ ነው። ጥናቱ ዓይነታዊ የጥናት ዘዴን (Qualitative) በመጠቀም የተሰራ ነው። አቀራረቡ ቴክስት ትንተና (textual analysis) ሲሆን፤ ስልቱ ፍካሬ (interpretative) ነው። የጥናቱ የመረጃ ምንጮች፡- አንድም ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን(EBC) ክምችት ክፍል የተገኙ የሸክላና የካሴት የአማርኛ ዘፈኖችን ወደጽሁፍ በመቀየር የተገኘ ነው። አንድም ከተለያዩ የህትመት ውጤቶች (ለምሳሌ- መጽሐፍት፣ መጽሔቶች) የዘፈን ግጥሞችን በመሰብሰብ የተገኘ ነው። እነዚህ የዘፈን ግጥሞች በየተዘፈኑበት ዘመን በመከፋፈል ያነሷቸውን ዋና ዋና ጭብጦች ከተግባራዊነት (Functionalism) ንድፈ ሀሳብ አንጻር ተተንትነዋል። ጥናቱ በ1966 ዓ.ም. እና በ1983 ዓ.ም. ሁለት የለውጥ ጊዜያት ላይ ትኩረቱን በማድረግ የተሰራ ሲሆን፤ ይህም የለውጥ ዋዜማ፣ የለውጥ ጊዜና የለውጥ ማግስት በሚል ንዑሳን ክፍሎች የተከፋፈለ ነው። በዚህ ጥናት፤ የለውጥ ዋዜማ ማለት፥ ለውጥ ከመከሰቱ አንድ ዓመት በፊት ጀምሮ፤ ለውጥ እስከተካሄደበት ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያካትት ነው። የለውጥ ጊዜ ሲባል ደግሞ፥ ለውጥ ከተከሰተበት እለት ጀምሮ ወደፊት ያሉትን ሁለት ዓመታት የሚመለከት ሲሆን፤ ከሁለት ዓመት በኋላ ወደፊት የሚቆጠሩት ሌሎች ሁለት ዓመታት ደግሞ፤ የለውጥ ማግስት በሚል የተጠኑ ናቸው። በዚህ ጥናት ግኝት፥ በለውጥ ሰሞን ላይ የተዘፈኑ ዘፈኖች፥ በመጀመርያ በድጋፍና ያለፈውን ገዢ በመውቀስ የሚገለጹ ሲሆኑ፤ ሁለተኛው በጥርጣሬ፣ በኢኮኖሚ ጉዳይ፣ በኤርትራ ጉዳይ እና በሀገር ሰላምና አንድነት ላይ አተኩረው የተዘፈኑ ግጥሞች ናቸው።

**ቁልፍ ቃላት፡-** ለውጥ፣ ሰሞን፣ የዘፈን ግጥሞች

## ምዕራፍ አንድ

### መግቢያ

ይህ ጥናት የለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች የጭብጥ ትንተና (ከ1966-1986 ዓ.ም) ፤ በሚል ርዕስ የተደረገ ነው። ጥናቱ በተጠቀሱት ዓመታት የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦችን በመለየት፤ የዘመኑን መልክ ለማሳየት ይሞክራል፤ ብሎም የዘፈን ግጥሞች በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ሚና እና ፋይዳ ይፈትሻል። ለዚህም ተግባራዊ (Functionalism)፣ የሚል ማህበረሰባዊ ንድፈ ሃሳብ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም የዘፈን ግጥሞችን ጭብጦች ተንትኖ አቅርቧል።

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሁሉም ጥበብ የዘመኑ ወኪል ነው ይባላል:: የሚነበቡ፣ የሚታዩና የሚዳሰሱ ጥበባት፤ እንደየቅርፃቸው የዘመናቸውን ቀለም ለማሳየት ይጥራሉ:: ሙዚቃ፥ ሌላኛው የዘመን መዝገብ የማድመጥ ጥበብ ነው (Ferris፣ 1995፣ 2):: በሙዚቃ ውስጥ ሁለት ድምጾች በዋናነት ይደመጣሉ:: የሙዚቃ መሳሪያው(Instruments) እና ግጥሙ (Lyrics):: የዘፈን ግጥሞች ታዲያ በአብዛኛው መልዕክት አዘል ናቸው:: ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሌሎች ጭብጦችን በውስጣቸው ያስተላልፋሉ:: Ferris(1995፣ 20) የዘፈን ግጥሞች አድማጭና ሙዚቃውን የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው ይሏቸዋል:: ስንኞቹ ባዘሉት መልዕክት (ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ሌላ) ምክንያት ሰሚው ስለመልክቱ ቢያንስ እንዲያስብ የማድረግ አቅም እንዳላቸው በማስረዳት:: በኢትዮጵያ የዘፈን ግጥም ላይ ካጠኑ አጥኚዎች መካከል፤ ንጉስ ይልማ (2018፣ 219) ይህኑ ሀሳብ በማጠናከር፤ “Song lyrics do have huge potential to keep records of major historical events of a society that occur within a certain period of time” በማለት የዘፈን ግጥሞች በማህበረሰብ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ትልቅ አቅም ያስረዳሉ:: ሌላዋ አጥኚ ትምክህት ተፈራ(2009፣ 1) እንደዚሁ “Music making is not only an exercise in the organization of sound, but a symbolic sociocultural activity reflecting the values of the past and present ways of human life” ይላሉ:: ፍሬ ነገራቸው ሙዚቃ የድምጽ ስብስብ ብቻ አይደለም ነው:: ይልቁንም የሰው ልጆች ህይወት ያለፈውና የአሁኑ እሴት፣ ብሎም ማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች የሚንፀባረቁበት የትዕምርት ማደሪያ ነው፤ የሚል ሀሳብን የያዘ ነው:: በርግጥ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የዘፈን ግጥሞች የየዘመናቸውን መልክ ሲያሳዩ መስማት አዲስ ነገር አይደለም:: ጥንትም በአዝማሪና

በእረኛ የዘፈን ግጥሞች የነገስታቱ ዘመን እውነታ ሲገለጥ ስለመኖሩ ታሪክ ምስክር ነው(ተክለጻድቅ፣ 1983፣ 505)።

የአዝማሪዎቹ ስንኞች እንኳንስ ለሀገሬው ለውጭውም የተረፉ ነበሩ። ከአድዋ እስከ ማይጨው ኢትዮጵያ ከኢጣሊያ ጋር በተፋለመችባቸው ግንባሮች ሁሉ፤ አዝማሪዎችም ተሰልፈው ከጥይት አረር ያልተናነሱ ወኔ ቀስቃሽ ግጥሞችን በዘፈኖቻቸው ውስጥ ለወታደሩ ስለማቀበላቸው የታሪክ ተመራማሪዎች ይመሰክራሉ(ተክለጻድቅ፣ 1983፣ 505)። በኢጣሊያ ወረራ ወቅት የነዚህን አዝማሪዎች ወሳኝ ሚና የተረዳው የኢጣሊያ ገገርም፤ አዲስ አበባን በረገጠ ማግስት የበቀል በትሩን ሰንዝሮ በርካታ አዝማሪዎችን ገድሏል።

የኢትዮጵያ ሙዚቃ መልክ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሻገር የጀመረው ከአድዋ ጦርነት ወዲህ[1] ነው። ከአድዋው ድል ማግስት አገርኛ ዘፈኖችን በውጭ ሙዚቃ መሳሪያዎች ታጅቦ መዝፈን እየተለመደ መጥቷል። የተለያዩ የወታደር የሙዚቃ ኦርኬስትራዎች[2] ተመስርተዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ የሀገር ፍቅር ማህበር(የአሁኑ ሀገር ፍቅር ቲያትር)፣ የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ባህልና ትያትር አዳራሽ፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትያትር ቤት(የአሁኑ ብሔራዊ ትያትር)፣ የያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ወዘተርፈ ተመስርተዋል። አሸናፊ ከበደ(1976፣ 291) በተለይ ከ1950ዎቹ ወዲህ አዝማሪ ከሚለው ስም ይልቅ ድምፃዊ፣ ሙዚቀኛ፣ አርቲስት የሚሉ ስያሜዎች እየተተኩ መምጣታቸውን ያትታሉ። አዝማሪነት ወይም ድምፃዊነትም ከቀድሞው የተሻለ ማህበራዊ ቅቡልነትን እያገኘ ስለመምጣቱ በጥናታቸው ያስረዳሉ።

ይሁንና አዲሱ የዝመና መንገድ የሙዚቃ መሳሪያዎችንና አቀራረቡን እንጂ የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ላይ ያስከተለው ለውጥ የለም። አዝማሪዎች በመሰንቆና ክራር ታጅበው የዘመናቸውን እውነት እንደገለጹት፣ በቅኔ እንዳንጎራጎሩት ሁሉ፤ ተከታዮቹ ድምፃውያንም እንዲሁ ከውጭ በመጡ መሳሪያዎች ታጅበው የጊዜያቸውን እውነት መታዘብ ይዘዋል። መልካም ያሉትን ማወደስ፣ ክፉ ያሉትን መንቀፉን ቀጥለዋል። በዚህ መልክ ስለስነ ምግባር፣ ስለትምህርት፣ ስለሙስና፣ ስለፖለቲካ፣ ስለኢኮኖሚ ወዘተርፈ ዘፍነዋል። ፍቅር፣ ሞትና ሥራም እንደዚሁ ተነስተዋል። የወል ከሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች በዘለለ የዘመናቸውን መንፈስ የከተቡ፤ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ማህበራዊውን ጉዳይ የዳሰሱ ዘፈኖች ተሰምተዋል። ምንም እንኳ የዘመኑ ሳንሱር

---

[1] የተለያዩ የውጭ የሙዚቃ መሳሪያዎች ወደሀገር ውስጥ በብዛት መምጣት መጀመራቸውን ተከትሎ(ለምሳሌ የሩሲያው ዛር ኒኮላይ ሁለተኛ የላኳቸው 40 የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች)፣ አገሪቱም አዳዲስ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶችን በስፋት ማድረግ የጀመረችበት ጊዜ መሆኑን ተከትሎና በመሳሰሉት ምክንያቶች።

[2] ክቡር ዘበኛ፣ ምድር ጦርና ፖሊስ ኦርኬስትራዎች ናቸው።

የሚያንቀሳቅስ ባይሆንም ሾልከው የወጡ የፖለቲካ ዘፈኖችም አልታጡም። ግጥሞችን በመፈከር ፖለቲካዊ ትርጉም የተሰጣቸውም አሉ። በ1953 ዓ.ም. የነመንግስቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ወቅት በጠቅል ሬዲዮ ተደጋግመው ይሰሙ የነበሩት ዘፈኖች ለዚህ ምሳሌዎች ናቸው። የጥላሁን ገሠሠ-"አልቻልኩም"፣ "ኡኡታ አያስከፋም"፣ የካሳ ተሰማ "ጉምጉም" የመሳሰሉ ዘፈኖች በፖለቲካ ዐይን ተፈክረዋል። ድምፃዊና ገጣሚዎቹም ለእስር ተዳርገውበታል(አየለ፣ 2013፣ 166)።

የ1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ምንም እንኳ ገና ከጅምሩ የከሸፈ ቢሆንም ቢያንስ ሁለት ቁም ነገሮችን ጥሎ ማለፉ አልቀረም። የመጀመርያው የፖለቲካ ለውጥ[3] ፈላጊውን ኃይል ይበልጥ ለትግል ማነሳሳቱ፣ "ንጉስ አይከሰስ" ይሉተን ብሂል ለዘላለሙ መሻሩና አይነኬ የሚመስለው ንጉሳዊ አገዛዝ መነቃነቅ መጀመሩ ሲሆን፤ ሁለተኛው፤ ሙዚቃ በለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚጫወተው ሚና ልቆ መቀጠሉ ነው። በ1966 እና 1983 ዓ.ም. የአገዛዝ ለውጦች ሰሞን የተሰሙ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦች የሂደቱን ቀጣይ ፍሬ እንዲሁ ያሳዩ ይመስለኛል። ምክንያቱም በሁለቱ ለውጦች ሰሞን የተዘፈኑ ግጥሞች በጭብጥም፣ በብዛትም ከ1953ቱ ዘመን በብዙ እጥፍ ልቀው ታይተዋልና ነው።

ስለዚህ በነዚህ ሁለት የለውጥ ሰሞናት (1966 ዓ.ም. እና 1983 ዓ.ም.) ላይ በማተኮር የተዘፈኑ የዘፈን ግጥሞችን በወጉ ለመረዳትና የዘመኑን አብይ ጭብጦች ለመፈተሽ ከለውጥ ዋዜማ እስከ ለውጥ ማግስት የተዘፈኑትን ማጥናት ያስፈልጋል። ምክንያቱም የዘፈን ግጥሞቹ የለውጡ ምርኩዞች ናቸው፤ ለውጡም የዘፈን ግጥሞቹ መዘውር ነው። Falceto (2001፣ 83) እንደሚሉት፥ በአንድ አገር ውስጥ የአገዛዝ ለውጥ ሲካሄድ፤ የለውጥ ሂደቱ የሚንጣቸው አያሌ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች አሉ። እንዲህ ዓይነቱ የለውጥ አጋጣሚ ታዲያ ለዘፈን ግጥም ፀሐፊው የሃሳብ ገበያው ነው ይላሉ። ምክንያቱም ገጣሚው በለውጥ ሂደት የሚቀጣጠለውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ጉዳይና የሌላም አዳዲስ አስተሳሰቦችንና ሁነቶችን በግጥሙ ለመግለጽ ያስችለዋልና ነው።

[3] ለውጥ የሚለውን ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት "የአንድ ህብረተሰብ የፖለቲካ ስርዓት ወይም የመንግስት መዋቅር በሌላ መተካት" በማለት ያብራራዋል(1993፣ 21)።

በኢትዮጵያ ታሪክ ለውጥ በተስተናገደ ቁጥር የሙዚቃ ግጥሞች ጭብጦችም እንደየዘመኑ መንፈስ ሲቀያየሩ ስለመታየታቸውና አንዱ ባንዱ አውድ ስለመቃኘቱ አሸናፊ ከበደ(1976፣ 289) እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> Change in music is frequently brought about by the social, political, and administrative conditions of a country. In Ethiopia, the aspirations and ultimate planned objectives of its rulers and leaders have been important factors in effecting change.

ከአሸናፊ ድምዳሜ እንደምንረዳው፤ ሙዚቃው በመንግስታቱ ለውጥ የሚቃኝ መሆኑን ነው። የሀገሪቱ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ለውጦች የሙዚቃውንም አካሄድ ይለውጣሉ። መሪዎችና የሚከተሏቸው አስተሳሰቦች እንደዚሁ በሙዚቃው ላይ ጫና ያሳድራሉ። በዚህ ምክንያት ገና ከለውጥ ዋዜማ ጀምሮ የሚጻፉ የዘፈን ግጥሞች በአብዛኛው ዘመኑን የሚጠቁሙ ናቸው። ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሂደቱን የማስቃኘት አቅምም አላቸው። ይሁንና በስነ ጽሑፍ ጥናት ውስጥ፤ የዘፈን ግጥሞች ብዙም ትኩረት አግኝተው ሲጠኑ አይታይም። አጥኚዎች እንደሚሉት (ለምሳሌ ስኪነር፣ 2018 እና ጽዮን፣ 2007) በሙዚቃ ጥናት፤ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ቅኝቶች፣ ዜማዎች ወዘተ፤ ትኩረት አግኝተው የሚጠኑትን ያህል የስነ ጽሁፉ አካል የሆነው የዘፈን ግጥም ግን ተገቢውን ትኩረት ያገኘ አይደለም። እኔ ባደረኩት ሀሰሳ፤ የሙዚቃ ግጥሞች ላይ ተመርኩዘው የተሰሩ መጣጥፎች፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ የሁለተኛ ዲግሪና የሶስተኛ ዲግሪ ጥናቶች ብዙ የሚባሉ አይደሉም። ለዚህ ጥናት በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ባደረኩት ንባብ የተመለከትኳቸው ጥናቶች በተለይ ለውጥ ላይ አተኩረው የተሰሩ አይደሉም። ስለዚህ፥ ይህ ጥናት በአማርኛ የተዘፈኑ የለውጥ ሰሞን ዘፈኖች ግጥሞችን በመፈተሽ የዘመኑን አብይ ጭብጦች ተንትኖ አቅርቧል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱኝ ሁለት ምክንያቶች ናቸው። የመጀመርያው የስራ አጋጣሚ ነው። ይህም በኢትዮዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን(EBC)፤ ኤፍ ኤም አዲስ 97.1 ላይ "ትዝታን በዜማ" የሚል ቆየት ያሉ ሙዚቃዎች ላይ የሚያተኩር፤ የሙዚቃ ፕሮግራም

አዘጋጃለሁ። ይህን ፕሮግራም በምሰራበት ወቅት በተለይ መንግስታት ሲለዋወጡ የሚሰሩ ዘፈኖች፤ ለወትሮው ከሚሰሩት የተለየ ስሜት ያላቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። በግጥሞቻቸው ውስጥ (ብዙዎቹ በቅኔና በዘይቤያዊ መንገድ) የጊዜውን የፖለቲካ ትኩሳት የሚያንጸባርቁ፣ የማህበረ ኢኮኖሚውን ሁኔታ የሚያነሳሱ ስራዎች ሆነው እስማቸዋለሁ። በዚህ የተነሳ በለውጥ ሰሞን ላይ ያተኮሩ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦችን የማጥናት ፍላጎት አድሮብኛል።

ሁለተኛው ምክንያት በጥናቱ ዳራ እንደተነሳው ከንባብ የሚቀዳ ነው። በአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ የተሰሩ የሶስተኛ ዲግሪ፣ የሁለተኛ ዲግሪ፣ የጆርናል መጣጥፎችንና የመጀመርያ ዲግሪ ጥናቶችን ሳነብ በለውጥ ሰሞን ላይ ትኩረት ያደረገ ጥናት አላጋጠመኝም። አለመጠናቱ በራሱ ችግር ባይሆንም፤ ጉዳዩን (የለውጥ ሰሞን የዘፈን ግጥሞችን) ማጥናቱ በጊዜው የተነሱ ዋና ዋና ጉዳዮችን(ጭብጦችን) ለመገንዘብ ያግዛል የሚል እምነት ስላደረብኝ፤ ተጨማሪ የመነሳሻ ምክንያት ሆነኝ።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት በለውጥ ሰሞን ላይ ትኩረት ያደረጉ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የሚከተሉትን አቢይ እና ንዑሳን ዓላማዎችን ይዟል።

### 1.3.1. የጥናቱ አቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ፡- በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ለውጡን በሚመለከት ያነሷቸውን ዋና ዋና ጭብጦችን ለይቶ በመተንተንና በመፈከር የተገኘውን ውጤት ማቅረብ ነው።

### 1.3.2. የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች

1. በለውጥ ሰሞን የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ የተስተዋሉ ዋና ዋና ጭብጦችን መለየት፣
2. የዘፈን ግጥሞች ጭብጦችን በመለየት ከተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ አንፃር ፋይዳቸውን መፈከር፣
3. በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ውስጥ የትኞቹ ጭብጦች ጎልተው እንደተስተዋሉ መፈተሽ፣

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚመልሳቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ቀጥለው የቀረቡት ናቸው።

1. በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የሚዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦች በምን አርዕስተ ጉዳይ ላይ ያተኩራሉ?
2. የለውጥ ሰሞን የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች የለውጡን ጊዜ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጭብጥ ያስቃኛሉ ወይ? ከወትሮው የተለየ ባህሪያቸው ምንድነው?
3. የለውጥ ሰሞን ላይ ያተኮሩ የዘፈን ግጥሞች የተፃፉባቸው ምክንያቶች ምንድናቸው?

## 1.5. የጥናቱ ፋይዳ

የዚህ ጥናት ፋይዳ በዋናነት በመስኩ ያለውን የእውቀት ክፍተት መሙላት ነው። በጥናቱ ዳራ እንደተገለፀው በለውጥ ሰሞን የዘፈን ግጥሞች ጭብጦች ላይ ያተኮረ ጥናት በእኔ ዳሰሳ አልተገኘም። ስለዚህ ይህ ጥናት በለውጥ ሰሞን የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦችን በመተንተን በጊዜው የተስተዋሉ አብይ ጉዳዮችን ያስቃኛል፤ ስለዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ሰፋ ያለ ግንዛቤን ይሰጣል። የዘፈን ግጥሞች ትዕምርታዊ ትርጉምና የተፃፉባቸውን ምክንያቶች በማስገንዘብ ሰፋ ያለ መረጃን ያስገኛል። ከዚህ ጥናት በመነሳት ሙግቶች ሊቀርቡ ይችላሉ። ይህም በመስኩ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች የጥናት ርዕስ በማስገኘትና ለምርምር በማነሳሳት፤ በዘፈን ግጥሞች ላይ የሚደረግን ጥናት ይበልጥ ሊያሰፋው ይችላል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1986 ዓ.ም. በነበሩ ሁለት[4] የአገዛዝ ለውጦች ሰሞን የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ ብቻ የተገደበ ነው። የለውጥ ሰሞን ሲባል ከለውጥ ዋዜማ እስከ ለውጥ ማግስት ያሉትን ጥቂት ዓመታት የሚመለከት ሲሆን፤ የቀሩትን የአገዛዝ ጊዜያት አይመለከትም።

በዚህ ጥናት የለውጥ ሰሞን ዘፈኖች የሚባሉት፥ አንድም በለውጥ ዋዜማ የተዘፈኑ፣ አንድም በለውጥ ጊዜ የተዘፈኑ እና በለውጥ ማግስት የተዘፈኑትን ብቻ የሚያካትት ነው። የለውጥ

[4] ወታደራዊው ደርግ እና የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር(ኢህአዴግ)

ዋዜማ ሲባል፥ ለውጥ ከመከሰቱ አንድ ዓመት በፊት ጀምሮ፤ ለውጥ እስከተካሄደበት እለት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያካትት ነው። ይህም ማለት የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ ሲባል፤ ከመስከረም 1966 እስከ መስከረም 1967 ዓ.ም. ያለውን አንድ ዓመት ይይዛል። ምንም እንኳ ለውጡ ከየካቲት 1966 ዓ.ም. ጀምሮ የተካሄደ ቢሆንም፤ ይህ ዓመት አንድም፡-የለውጥ ዋዜማ፤ አንድም፡- የለውጥ ጊዜ ሆኖ የተፈተሸ ነው። ለምን ቢሉ፤ አንድም፡- ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በይፋ ስልጣናቸውን ለቀው ከቤተ መንግስታቸው የወጡት በመስከረም 1967 ዓ.ም. በመሆኑ፤ አንድም፡-የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜአዊ ወታደራዊ መንግስት(ደርግ) በይፋ ስልጣኑን ያወጀው በዚሁ በመስከረም ወር 1967 ዓ.ም. በመሆኑ ነው። ሌላው የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ ሲሆን፤ ይህም ከግንቦት 1982 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 1983 ዓ.ም. ድረስ ያለውን አንድ ዓመት ያጠቃልላል።

የለውጥ ጊዜ ሲባል ደግሞ፥ ለውጥ ከተከሰተበት እለት ጀምሮ ወደፊት የሚቆጠሩ ሁለት ዓመታትን ብቻ የሚያጠቃልል ነው። በዚህ መሰረት የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ጊዜ ማለት፤ ከየካቲት 1966 እስከ ጳጉሜ 1967 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ሲሆን፤ የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ጊዜ ደግሞ፤ ከግንቦት 1983 እስከ ጳጉሜ 1984 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል።

ከሁለት ዓመት በኋላ የሚቆጠሩት ሌሎች ሁለት ዓመታት ደግሞ፤ የለውጥ ማግስት በሚል የቀረቡ ናቸው። ይህም ሲብራራ፤ የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ማግስት ማለት፤ ከመስከረም 1968 እስከ ጳጉሜ 1969 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ማለት ሲሆን፤ የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ማግስት ደግሞ፤ ከመስከረም 1985 እስከ ጳጉሜ 1986 ዓ.ም. መጨረሻ ማለት ነው።

በዚህ መሰረት፤ ይህ ጥናት ከ1966-1986 ዓ.ም. በተከሰቱ ሁለት የለውጥ ሰሞናት(1966 እና 1983 ዓ.ም) ያሉ ዓመታትን ብቻ ከላይ በተነሳው አግባብ መርምሯል። ጥናቱ የዘፈን ግጥሞቹን ጭብጦች እንጂ የግጥሞቹን ቅርፅ፣ የሙዚቃ ቅንብሩን ወይም ሌላ አይመለከትም። በፖለቲከኞች(በገዢው ወይም በተቃዋሚ) ድጋፍና ይሁንታ የተሰሩ የተለያዩ ህብረ ዝማሬዎችና ዘፈኖች የዚህ ጥናት አካል አይደሉም። በለውጥ ላይ ያላተኮሩ[5] የዘፈን ግጥሞች ጭብጦች(ለምሳሌ-የፍቅር ግጥሞች) በዚህ ጥናት አልተዳሰሱም። እንዲሁም ከአማርኛ ቋንቋ ውጭ በሌሎች ቋንቋዎች የተሰሩ የለውጥ ሰሞን የዘፈን ግጥሞችን ይህ ጥናት አላካተተም።

[5] የጊዜውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ የማያሳዩ

## 1.7. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው። ምዕራፍ አንድ ውስጥ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ፋይዳ፣ የጥናቱ ወሰን እና የጥናቱ ዘዴ የሚሉትን ንዑሳን አርዕስቶች የያዘ ነው። ምዕራፍ ሁለት ደግሞ፤ ክለሳ ድርሳናት ሲሆን በውስጡም፥ ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ፣ ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የሚሉ ንዑሳን አርዕስቶችን ይዟል። በምዕራፍ ሶስት የተመረጡ ቴክስቶች በተቀነበበው ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ መሰረት ትንታኔ ተደርጎባቸዋል። በመጨረሻም፥ በምዕራፍ አራት የጥናቱ ማጠቃለያ ቀርቧ። ማጣቀሻዎችና አባሪ ማስረጃዎችም ተካተዋል።

## 1.8. የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ርዕስ ስር የተካተቱት ጉዳዮች፤ የጥናቱ አቀራረብ፣ የጥናቱ መተንተኛ ስልት፣ ጥናቱ የሚከተለው ንድፈ ሀሳብ፣ የጥናቱ የመረጃ ምንጭና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የሚሉት ናቸው።

ይህ ጥናት በአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ላይ የሚካሄድ እንደመሆኑ፤ አቀራረቡ ቴክስት ትንተና(textual analysis) ሲሆን፤ ስልቱ ፍካሬ(interpretative) ነው። የለውጥ ሰሞን የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦችን በዓይነታዊ(Qualitative) የመተንተኛ ዘዴ በመጠቀም ይተነትናል፣ ይፈክራል። የግጥሞቹን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ይፈትሻል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ተግባራዊ(Functionalism)፣ ማህበረሰባዊ ንድፈ ሃሳብ የመተንተኛ ዘዴን ተጠቅሟል።

ይህ ንድፈ ሃሳብ የተመረጠበት አብይ ምክንያት፥ የዘፈን ግጥሞች ይዘቶች ላይ የተሟላ ንባብ ለማድረግ የተሻለ ወይም ለጥናቱ የተስማማ ንድፈ ሀሳብ ሆኖ በመገኘቱ ነው። Haralambos with Herald (2013፣ 11) እንደሚያስረዱት፥ በተግባራዊያን አረዳድ፥ እያንዳንዱ የማህበረሰብ አካል ለማህበረሰባዊው ሁለንተናዊ ጉዞ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል የሚል እምነት አላቸው። ነገሩን ከሰው ልጅ የሰውነት ክፍሎች ጋር በማነፃፀር፤ የሰው ልጅ የሰውነት ክፍሎች እያንዳንዳቸው በሚሰጡት ግልጋሎት የሙሉው አካል ደህንነት እንደሚረጋገጠው ሁሉ፤ ማህበረሰብም እንደዚሁ ነው ይላሉ። ያንዱ ተግባር ለሌላው መኖር ዋስትና ይሆናል፤ አንዱ ባንዱ ላይ መሰረቱን ጥሎ ተደጋግፎ ይኖራል። ያንዱ አካል መጓደል ለሙሉው ሰውነት መታመም ምክንያት ይሆናል። የእያንዳንዱ የማህበረሰብ አባልም ተግባር ለጠቅላላው

ማህበረሰባዊ ጉዞ የየራሱን ድርሻ ያበረክታል። አበርክቶው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል። ዓይነቱ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በኪነ ጥበብ፣ በቤተሰብ እና በመሳሰሉት ሊገለፅ ይችላል። ድምር ውጤቱ በማህበረሰቡ ቀጣይ ጉዞ ውስጥ የሚሰላ ነው። የፖለቲካው ተግባር፣ የኢኮኖሚው ተግብር ወይም የሌላው ተግባር ጤናማነት በእያንዳንዱ ተግባር ውጤታማነት ይለካል። ያንዱ መታመም የአጠቃላዩን ማህበረሰባዊ እንቅስቃሴ ችግር ውስጥ ሊከተው ይችላል (Hammond፣ 2010፣ 21)።

ሙዚቃ በማህበረሱ ውስጥ ሰፊ ድርሻ ያለው አንዱ ተግባር ነው፤ ስለዚህ ተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ የለውጥ ሰሞን ላይ ያተኮሩ የዘፈን ግጥሞችን ጭብጦች ለማጥናት ፍካሬው የጠራው ማንጸሪያ ሆኗል።

### 1.8.1. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናት የተመረጡት በለውጥ ሰሞን ላይ ያተኮሩ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች በዋናነት የተገኙት ከሁለት ምንጮች ነው። ዋናው ምንጭ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን(EBC) ክምችት ክፍል ሲሆን፤ በሸክላ እና በካሴት የታተሙ ዘፈኖች ግጥሞችን ወደ ጽሑፍ በመቀየር የተሰበሰበ ነው። ሁለተኛው፡- ከተለያዩ ህትመቶች (ከጥናት ወረቀቶች፣ መጽሐፍትና መጽሔቶች) የተገኘ ነው።

### 1.8.2. የጥናቱ ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡት(ከ1966-1986 ባሉ ሁለት የለውጥ ጊዜያት) አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት(132) የለውጥ ሰሞን የአማርኛ ዘፈኖች ሲሆኑ፥ ከነዚህ ውስጥ 40 የዘፈን ግጥሞችን ናሙና በመለየት፤ ጭብጦቻቸው ተፈትሸዋል። ይህም የአጠቃላዩ 30% ማለት ነው። የናሙና አመራረጥ ዘዴው ዓላማ ተኮር (Purposive Sampling) ዘዴን የተከተለ ነው። Kothari (2004፣ 59) እንደሚያስረዱት፥ ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ አጥኚው ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን ናሙናዎች አስቀድሞ እንዲለይ ያግዘዋል። ይህም የጊዜና የገንዘብ ብክነትን በመቀነስ የተቀላጠፈ ጥናት ለመስራት ያስችላል። ይሁንና ይህ ዓይነቱ የናሙና አመራረጥ ዘዴ አጥኚው የሚፈልጋቸውን ናሙናዎች ብቻ በመምረጥ አድሏዊ ድምዳሜ ላይ ሊያደርሰው ስለሚችል ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የተገባ ነው። በዚህ መሰረት፥ ለዚህ ጥናት የተመረጡት ናሙናዎች በሁለት መስፈርቶች የተለዩ ናቸው።

አንደኛ፥ ዘፈኖቹ በድምፃውያኑ በግል ተነሳሽነትና ወጪ የተሰሩ መሆናቸው ነው፡፡ በተዘዋዋሪ መንገድ የገዢዎች(ፖለቲከኞች) ፍላጎት ሊንፀባረቅባቸው ቢችልም፥ ቢያንስ ድምፃውያን በግል ወጪያቸው ያሳተሟቸው ካሴቶችና ሸክላዎች የገዢዎቹ ዓላማ ተሸካሚ የመሆን እድላቸው ስለሚቀንስ ቀዳሚ ምርጫን አግኝተዋል፡፡

ሁለተኛ፥ በአገጣጠማቸው ከፍ ያሉና በተለያዩ መንገዶች ሊፈከሩ የሚችሉ የዘፈን ግጥሞች ናቸው፡፡ ስለዚህ በግልጽ ቋንቋ ለፖለቲካዊ ቅስቀሳና ለርዕዮተ ዓለም ማስተማሪያ የተሰሩ ሕብረ ዝማሬዎችና ዘፈኖች በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም፡፡ የዚህ ምክንያት አንድም፡- የግጥም ከፍታቸው ተራና ግልጽ የሆኑ ዘፈኖች(ጭብጣቸው ግልጽ ስለሆነ) ተጨማሪ ፍካሬያዊ ትንታኔ አያስፈልጋቸውም በሚል ነው፡፡ አንድም፡- በፖለቲከኞች(በገዢው መንግስት ወይም በተቃዋሚ) ፍላጎትና ድጋፍ የተሰሩ በመሆናቸው ተገቢውን ውጤት አያስገኙም ከሚል ድምዳሜ ነው፡፡

በመሆኑም፥ ከላይ በተገለጹት መስፈርቶች መሰረት ለዚህ ጥናት የተመረጡት በለውጥ ሰሞን ላይ ያተኮሩ የአማኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦች፤ የለውጥ ዋዜማ፣ የለውጥ ጊዜና የለውጠጥ ማግስት በሚሉ ንዑሳን ፈርጆች ተከፋፍለው ተተንትነዋል፤ ተፈክረዋል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ሶስት አንኳር ጉዳዮች በዋናነት የቀረቡ ሲሆን፤ እነዚህም፥ ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የሚሉ ናቸው።

### 2.1. ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የሚቀርቡት ጽንሰ ሐሳቦች የዓለማዊ(Secular) ሙዚቃ መሰረቶች በኢትዮጵያ፣ ዘመናዊ ሙዚቃ በኢትዮጵያ፣ ለውጥና ሙዚቃ፣ የዘፈን ግጥሞች፣ የዘፈን ግጥሞች ጭብጥና ተግባር የሚሉ ይሆናሉ። የእያንዳንዳቸው ጽንሰ ሐሳቦች ምንነትና ተግባራት ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተላቸው ቀርበዋል።

#### 2.1.1. የዓለማዊ (Secular) ሙዚቃ መሠረቶች በኢትዮጵያ

ዓለማዊ[6] ሙዚቃ ሲባል ለሐይማኖታዊ አገልግሎት ተብለው ያልተሠሩ ዘፈኖችን የሚመለከት ነው። ከቃሉም እንደምንረዳው ዓለማዊነት የዓለም ጣጣ ነው። መነሻና መድረሻው የሰው ልጅ ምድራዊ ውጣ ውረድ ነው። ፖለቲካውን፣ ኢኮኖሚውን፣ ፍልስፍናውን፣ ባህሉን፣ ወጉን፣ ስርዓቱን የሚመለከት ነው። አሸናፊ(1971፣ 40) ዓለማዊ ዘፈንን “Secular music which was practiced outside the church are far removed from soul (yenefs) music” በማለት ያስቀምጡታል። እንግዲህ ዓለማዊ ሙዚቃ ወይም ዘፈን ሲባል ለየትኛውም መንፈሳዊ ኃይል ያልተሰራ፤ ይልቁንም ከሰው ለሰው የተዘፈኑትን ለማለት መሆኑን ልብ ይሏል።

የኢትዮጵያ ዓለማዊ ሙዚቃ መሰረት ሲነሳ በተለይ ሁለት ጎራዎች ጎልተው ይወጣሉ። እነዚህም፥ ከክርስትና እምነት መግባት በፊትና ከክርስትና እምነት መግባት በኋላ የሚሉ ናቸው(ንጉስ፣ 2018፣ 15) ። የመጀመርያው ሀሳብ፤ ኢትዮጵያ የክርስትና እምነትን ከመቀበሏ በፊትም የኖረች ጥንታዊት አገር እንደመሆኗ፥ የዓለማዊ ዘፈን መሰረቱ ከጥንቱ ማህበረሰብና ስልጣኔ የሚቀዳ ነው፥ የሚል ነው። Silvia Pankhurst (1955፣ 108) ነገሩን በመደገፍ “Ethiopian society had existed before the introduction of Christianity having long

---

[6] ዓለማዊ የሚለውን ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት “መንፈሳዊ ያልሆነ፥ ስጋዊ” ይለዋል(1993፣ 302)።

established customs, beliefs which were expressed in music and other manners" ይላሉ። የሲልቪያ ነጥብ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ከክርስትና እምነት መግባት በፊትም የነበረ እስከሆነ ድረስ በሙዚቃና በሌላ ሁኔታ የሚገለጽ ልማድና እምነት ይኖረዋል የሚል ነው። አሸናፊ(1971፣ 25) በበኩላቸው፥ ስለኢትዮጵያ ዓለማዊ ሙዚቃ መነሻ፥ ከሲልቪያ ጥናት በተለየ ያነሱት መከራከሪያ ባይኖርም፤ አድራሻውን ግን ከቀይ ባህር ማዶ ያሻግሩታል። ይህም ከነገደ ሴም ስደተኞች(Hamito-Semitic immigrants) ጋር የተያያዘ ነው ይላሉ። እንደ አሸናፊ ሐተታ፥ የነገደ ሴም ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ለተለያዩ ከበራዎችና መስዋዕት ማቅረቢያነት የሚከውኗቸውን ዘፈኖችና ዳንሶች ይዘው በመግባት፤ በጊዜ ብዛት ከነባሩ ህዝብ ልማድ ጋር እንዲቀየጥ ሆኗል። ይህም ለዓለማዊው ሙዚቃ መሰረትና እድገት አስተዋጽኦ አድርጓል የሚል ነው።

ሁለተኛው ነጥብ፤ የክርስትና እምነት ወደኢትዮጵያ መግባት ወዲህ ያለውን ዘመን የሚመለከት ነው። የክርስትና እምነት ከገባ ወዲህ የቤተክርስቲያን ዝማሬዎች(Sacred music) ለኢትዮጵያ ዓለማዊው ሙዚቃ እድገት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል በማለት የተለያዩ አጥኚዎች ያነሳሉ(ለምሳሌ፥ ሰላም፣ 1988፥ 4፣ ንጉስ፣ 2018፣ 11)። መሰረቱ ደግሞ ቅዱስ ያሬድ ነው። በንጉስ ገብረመስቀል(550-564 ዓ.ም) ዘመን የኖረው ቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶቹ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ ዛሬም ሕያው ግልጋሎት ላይ ናቸው። ዋናዎቹ ዜማዎች ሶስት ዓይነት ሲሆኑ፤ ግዕዝ፣ እዝል እና አራራይ የሚባሉ ናቸው። እንደ አሸናፊ(1971፣ 55) ታዲያ፥ የቅዱስ ያሬድ ዜማዎች ለዓለማዊው ሙዚቃ እድገት ጥሩ ሚና ነበራቸው። በተለይ የቤተክርስቲያን እውቀት ያላቸው አዝማሪዎች ዜማዎቹን ዓለማዊ ይዘት ባላቸው ግጥሞች በመጫወት አዲስ መንገድ አልምደዋል።

### 2.1.2. ዘመናዊ ሙዚቃ በኢትዮጵያ

ዘመናዊነት እንደ ጽንሰ ሀሳብ በተለይ በአውሮፓውያን ዘንድ ገና ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲቀነቀን የኖረ ነው። ከአብይ መገለጫዎቹ መካከል የኢንደስትሪዎች መስፋፋትና የዲሞክራሲ ስርዓት መዘርጋት የሚሉት በዋናነት ይገኙበታል(ባህሩ፣ 2013፣ 2)። ይህ የምዕራቡ ዓለም የዘመናዊነት እንቅስቃሴ ታዲያ ወደ ሶስተኛው ዓለም ሀገራት ታሪክ ሲመጣ መነሻውን ከ19ኛውና 20ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ያሳርፋል። ባህሩ(2013፣ 2) እንደሚያስረዱት፤

ዘመናዊነት ከምዕራቡ ዓለም አተያይ ባሻገር በሶስተኛው ዓለም ሚዛን ተመዝኖ መገለጫ ሆነው ከቀረቡ መስፈርቶች መካከል፤ የከተሞች እድገት መስፋፋት፣ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ መስፋፋት፣ የሀገረ መንግስት ማቆጥቆጥና የዓለም አቀፍ ግንኙነቶች መዳበር የሚሉት ይገኙበታል። ኢትዮጵያ ከዚሁ ጎራ የምትመደብ ሀገር እንደመሆኗ፤ የዘመናዊነት ጉዞ መሰረቶቿ በአብዛኛው ከዚሁ ዘመን ውስጥ የሚቀዳ ይመስላል። አየለ እሸቱ(2013፣ 43) እንደሚያስረዱት፥ የኢትዮጵያ የዘመናዊነት ጉዞ በተለይ ከ1888ቱ የአድዋው ድል ወዲህ ከፍ ብሎ ታይቷል። ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ ተጨባጭ ለውጦች የተመዘገቡት በዚሁ ወቅት ነው በማለት። ለአብነትም ሉአላዊነቷ የተከበረ ሀገረ መንግስት መገንባቱና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች መስፋፋት የሚሉት ይገኙበታል። ሰላም ስዩም(1988፣ 22) ስለኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ ባጠናበት ጥናቱ በአድዋው ማግስት ከታዩ አንኳር ለውጦች መካከል አንዱ የአዲስ አበባ ከተማ መስፋፋት ነው ይላል። ለዚህም ከዋንኞቹ ምክንያቶች አንዱ የተለያዩ ሀገራት ኢምባሲዎች በአዲስ አበባ መከፈት መጀመሩ ነው በማለት። “Since military conquest had failed now, Europeans began to use diplomatic, economic and cultural means for increasing their influence (1988፣ 22)” በማለትም፥ በኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድ ተሸንፎ የተመለሰው የኢጣሊያ ጦር ለአውሮፓውያኑ ሀገራት የአቀራረብ ለውጥ ምክንያት እንደሆነ ያስረዳል። ከኃይል ይልቅ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን በማጠናከር ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ተጽዕኖን ማሳደግ ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን ያትታል።

የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ መነሻ ከዚሁ ማህቀፍ ውስጥ የሚመዘዝ ነው። ከላይ እንዳየነው፥ የአድዋውን ድል ተከትሎ በርካታ ሀገራት ኢትዮጵያን ለዲፕሎማሲያዊ ወዳጅነት ተሻምተዋል። ለወዳጅነት አዲስ አበባ የደረሱት የውጭ ዜጎች ታዲያ ኢትዮጵያን ሲረግጡ ባዶ እጃቸውን አልነበረም። አንድም ለወዳጅነታቸው ማሳያ- እጅ መንሻነት፤ አንድም በአጋጣሚው የራሳቸውን የባህል ተጽእኖ ከጅምሩ ለማለማመድ በሚመስል የተለያዩ ስጦታዎችን ለዳግማዊ ምኒሊክ አስረክበዋል። በዚህ ዘመን የተለያዩ እጅ መንሻ ስጦታዎችን ይዘው አዲስ አበባ ከመጡ መልክተኞች መካከል የሩሲያው ዛር ኒኮላይ ሁለተኛ መልክተኞች ይገኙበታል። ኮሎኔል ሊኦንቴፍ በተባለ ሩሲያዊ የሚመራው ልዑክ ከያዛቸው ስጦታዎች መካከል ታዲያ 40 የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች ይገኙበት ነበር። እነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከጅምሩ ብዙ ባይሳካላቸውም የኋላ ኋላ የኢትዮጵያን ሙዚቃ መልክ እየቀየሩ ስለመምጣታቸው ብዙዎች ይስማማሉ(Falceto፣ 2001፣ 51፤ Timkhet 2010፣ 22)።

እዚህ ላይ በተለያዩ ጸሐፍት የሚነሳን አንድ ጥያቄ ላንሳ፡፡ ጥያቄው በርግጥ እነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዴት ሊመጡ ቻሉ? የሚል ነው፡፡ ነገሩ በጊዜው ከተለመዱት የስጦታ ዓይነቶች አንጻር የሚያጠያይቅ ይመስላል፡፡ አንዳንድ አጥኚዎች ከምኒልክ የዘመናዊነት መሻት በመነሳት በንጉሡ ጥያቄ የመጡ ሳይሆኑ አይቀርም ይላሉ፡፡ ሰላም(1988፣ 23) “It might well be that Menelik, who was preparing to celebrate the first anniversary of Adowa, needed the brass Instruments for the ceremony” በማለት ምኒሊክ የአድዋን አንደኛ ዓመት ለማክበር በሚል ያስመጧቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስረዳል፡፡ በአድዋው ድል ማግስት የእንግሊዝን መንግስት መልክት ይዘው በምኒልክ ፊት ከቀረቡት ልዑካን አንዱ የሆኑት Count Gleichen ግን “With the mission to Menelik” በሚል መጽሐፋቸው ውስጥ፤ የሙዚቃ መሳሪያዎቹ በምኒሊክ ይሁንታ የመጡ ሳይሆኑ እንደውም ያልተወደዱ ስጦታዎች ነበሩ ይላሉ፡፡ እንደማስረጃም፥ በወቅቱ ከእንግሊዝ መንግስት የተላኩትን ልዩ ልዩ የጦር መሳሪያ ስጦታዎች ለንጉሱ ሲያቀርቡላቸው፥ በስጦታዎቹ ተደስተው የተናገሩትን ያቀርባሉ፡፡ “Other nations, ’have treated me like a baby, and given me musical boxes, and magic lanterns, and mechanical toys; but you have given me what is really useful and valuable” (Gleichen፣ 1898 ፣ 144) ፡፡

ከንግግራቸው ምኒልኪ በሙዚቃ መሳሪያ ስጦታዎቹ ደስተኛ እንዳልነበሩ መረዳት ቢቻልም፤ እርግጠኛ ለመሆን ግን አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም አንድም ለዲፕሎማሲያዊ ጠቀሜታ ሲባል ያደረጉት ሊሆን ይችላልና ነው፡፡ አንድም ምኒልክ በተለይ ከሩሲያው መልክተኛ ኮሎኔል ሊኦንቴፍ ጋር የነበራቸው የጠበቀ ወዳጅነት ይህንን የሚሽር ይመስላል፡፡ ምክንያቱም የኮሎኔል ሊኦንቴፍ ልዑክ የሙዚቃ መሳሪያ ብቻ ይዞ አልመጣም፡፡ መሳሪያዎቹን የሚያለማምዱ አሰልጣኞችንም እንጂ፡፡ በተለይ ሚሌውስኪ የተባለ የሙዚቃ መምህር በዘመኑ የተለያዩ ወጣቶችን ለማሠልጠን ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረጉ ተጽፏል፡፡ ጳውሎስ ኞኞ(1984፣ 339) ሞንዶን ቪዳሌን ጠቅሶ እንደፃፈው፥ በወቅቱ ለሙዚቃ ይሰጠው ከነበረው ግምት አንፃር ከፍ ያለ ተግዳሮት ገጥሞት ስለነበርና የአዲስ አበባ ሰዎች አንማርም ስላሉ ለመምህሩ ሚሊውስኪ ከወላይታና ከቤሻንጉል የመጡ ሰዎች ተሰጥተውት አስተምሯል፡፡ በአራት ወራት ልምምድም ተማሪዎቹ የፈረንሳይንና የሩሲያን ብሔራዊ መዝሙር ማቅረብ ችለው ነበር(ይናገር፣ 2014፣ 20)፡፡ እንግዲህ ይህ ሁሉ ጥረት ያለንጉሱ ትብብርና ፈቃድ ሊሆን አይችልም፡፡ ብኋላም የሩሲያ መምህራን ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ እንዲሁ ንጉሱ ሌላ የሙዚቃ አስተማሪዎች እንዲላኩላቸው የተማጽኖ ደብዳቤ ለሩሲያ መንግስት ልከዋል(ጳውሎስ፣ 1984፣ 340)፡፡

ይህ ጥረት በንግስት ዘውዲቱና በአልጋወራሹ ተፈሪ መኮንንም ጊዜ ቀጥሏል፡፡ በ1916 ዓ.ም. ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት ሀገር ሆና በሊግ ኦፍ ኔሽን ጉባኤ አንድትሳተፍ ፍቃድ ስታገኝ ልዑል አልጋ ወራሽ ሀገሪቱን በመወክል ወደ ስፍራው አምርተዋል፡፡ በዚህ ጉዟቸውም ወቅት እየሩሳሌም የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለመጐብኘት ወደ ስፍራው አቅንተው ነበር፡፡ ይህ ጉብኝታቸውም አልጋ ወራሹን ከአንግዳ ጉዳይ ጋር አስተዋውቋቸዋል፡፡ በኢየሩሳሌም ላለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጐረቤት በሆነችው አርመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ታዳጊዎች ለአልጋ ወራሹ አቀባበል የሙዚቃ ትርኢትን አቀረቡ፡፡ እነዚህ ከ13-19 ዓመት የሆናቸው ታዳጊዎች ቱርክ ሀገራቸውን በወረረች ጊዜ ወላጆቻቸውን በጦርነቱ ያጡ ሲሆን ወደ ኢየሩሳሌም የመጡትም በስደት እንደነበር ይገለፃል፡፡ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንንም የእንኳን ደህና መጡ አቀባበሉን ከተመለከቱ በኂላ ስለእነዚህ ልጆች ሁኔታ በእየሩሳሌም ከሚገኙት የአርመን ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ አርክ ቢሾፕ ቴሪዝያን ጋር ተወያይተዋል፡፡ ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን የታዳጊዎቹን ታሪክ ከሰሙ በኂላ አርባ ያህሉን ወጣቶች ከነመሪያቸው ለመውሰድ ፍቃደኛ ሆኑ(መርስኤ ኀዘን፣ 2008፣ 317)፡፡

በዚህ መልክ ወደኢትዮጵያ የመጡት የአርመን ሙዚቀኞች፤ ኪቦልክ ናልባንዲያን በተባለ መሪያቸው አማካኝነት በኢትዮጵያ ሙዚቃ መሰረታዊ እድገት ውስጥ ከፍ ያለ ሚና ስለመጫወታቸው በታሪክ ተመዝግቧል(ዘከሪያ፣2007፣ 150)፡፡ ኪቦልክ ናልባንዲያን በኢትዮጵያ የመጀመርያ የሆነውን ብሔራዊ መዝሙር ዜማና ቅንብር የሰራም ባለሙያ ነው፡፡ በኂላ ለተመሰረቱት እንደ ክቡር ዘበኛ ላሉ ታላላቅ ወታደራዊ ኦርኬስትራዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠትም አገልግሏል(ይናገር፣ 2014፣ 21)፡፡

በዚህ መልክ፥ የ20ኛውን ክፍለ ዘመን ከውጭ በመጡ የሙዚቃ መሳሪያዎችና ባለሙያዎች የተቀላቀለው የኢትዮጵያ ሙዚቃ በተለይ እንደ ክቡር ዘበኛ፣ ፖሊስ ኦርኬስትራና ምድር ጦር የመሳሰሉ ታላላቅ የሙዚቃ ኦርኬትራዎች ከተመሰረቱ ወዲህ ዘርፉ ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግሯል፡፡ አንድም ሙዚቃ ማህበራዊ ቅቡልነቱ ከፍ እያለ መጥቷል፡፡ አንድም ሙዚቃ ተቋማዊ መልክ እየያዘ መጥቷል፡፡ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦችም ከጊዜው ጋር ዘምነው የዘመናቸውን ማህበረ ኢኮኖሚና የፖለቲካ ትኩሳት ማስተጋባቱን ቀጥለዋል፡፡

### 2.1.3. ለውጥና ሙዚቃ

የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣ 21) ‹‹ለውጥ›› የሚለውን ቃል አዲስ ሁኔታ፣ የተለየ ነገር፣ ልዩነት፣ የአንድ ህብረተሰብ የፖለቲካ ስርዓት ወይም የመንግስት መዋቅር በሌላ መተካት ሲል ይበይነዋል። የቃሉ ግስ የሆነውን ‹‹ለወጠ››ን ደግሞ የአንድን ነገር ቀድሞ የነበረ ሁኔታ፣ ባህርይ፣ መልክ፣ በሌላ እንዲቀየር፣ እንዲተካ አደረገ። አንድ ነገር ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ፣ ባህርይ፣ መልክ በሌላ ቀየረ። ተበላሸ፣ ቀድሞ ከነበረው አሻሻለ በማለት ይገልፀዋል።

በገዢዎች መቀያየር ወቅት በተለየ ጭብጥና ስልት ከሚስተናገዱ ኪነ ጥበባዊ እሴቶች መካከል አንዱ ሙዚቃ ነው። ሙዚቃ የፖለቲካውን፣ የኢኮኖሚውን እና የመሳሰሉትን ለውጦች ተከትሎ አብሮ ይለወጣል። ለውጡ በሙዚቃው ውስጥ፥ ሙዚቃውም በለውጡ ውስጥ ይንፀባረቃል። አሽናፊ(1976፣ 289) ለውጥ በተለይ ከሙዚቃ እድገትና እንቅስቃሴ ጋር የተቆራኘ ነው ይላሉ። ለዚህም በአንድ ሀገር ውስጥ የአገዛዝ ለውጦች መኖር የሙዚቃውንም መስመር በመዘወር ለአዳዲስ ጭብጦች መሰማት ምክንያት ይሆናል። Olsen (2014፣ 4) ስለ ደቡብ አፍሪካ ሙዚቃና ማህበራዊ ለውጥ ባጠኑበት ጥናት ውስጥ፥ በለውጥ ሂደት ውስጥ ሁልጊዜም ተስፋና ስጋቶች ስለመኖራቸው ያስረዳሉ። ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በአዳዲስ አስተሳሰቦች ይቃኛሉ። የእድገት፣ የነፃነት፣ የዲሞክራሲና የመሳሰሉ ህዝባዊ ጥያቄዎች በስፋት ይነሳሉ። ፖለቲከኞች፣ ማህበራዊ አንቂዎች፣ መገናኛ ብዙሀንና ኪነ ጥበባት ለውጡን አስመልክተው የተለያዩ መረጃዎችንና ሀሳቦችን ያጋራሉ።

ሙዚቃ፥ በለውጥ ወቅት ንቁ ተሳትፎ ከሚያደርጉ ጥበባት መካከል ዋንኛው ነው። Falceto(2004፣ 83) እንደሚያስረዱት፥ ይህ ዓይነቱ የለውጥ ጊዜ ለሙዚቃ ግጥም ፀሐፊዎች የሃሳብ ገበያቸው የሚደራበት ወቅት ነው በማለት ያትታሉ። የረጋው አገር በለውጥ ሃሳብ ውስጥ ሲናጥ፣ ነባሩ ካዲሱ አስተሳሰብ ጋር ሲታገል ከያኒው ብዙ ጭብጦችን ለማፍለቅ እድል ያገኛል።

### 2.1.4. የዘፈን ግጥሞች (Lyrics)

በዘፈን ስራ ውስጥ ሁለት ድምጾች በዋናነት ይደመጣሉ። የሙዚቃ መሳሪያዎች(instruments) እና ግጥም(lyrics)። የዘፈን ግጥም(Song lyrics) የሚባለው በዘፈን ውስጥ ከሙዚቃ መሳሪያው ጋር ተዋህዶ የምንሰማው ግጥም ነው። Ransom (2015፣ 11) “lyrics are a set of words

that make up a song in a textual format.” በማለት የዘፈን ግጥሞች በሙዚቃ ውስጥ በቴክስት መልክ የሚገለጹ የቃላት ስብስብ ስለመሆናቸው ይበይናል።

የዘፈን ግጥም ነገር ሲነሳ አንድ ጥያቄ አብሮ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም፥ የዘፈን ግጥም ከሌላው ግጥም(Song lyrics and poetry) በምን ይለያል? የሚል ጥያቄ ነው። ልዩነታቸውን ለመረዳት በቅድሚያ አንድነታቸውን፥ ወይም የሚመሳሰሉባቸውን ነጥቦች ማንሳቱ ጠቃሚ ነው። ንጉስ ይልማ(2018፣ 20) (Wickham, 2010፣ 7)ን ጠቅሶ እንደሚያስረዳው የዘፈን ግጥሞች ከሌሎች ግጥሞች ጋር የሚመሳሰሉባቸው ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች አሉ። እነዚህም፥ አንደኛ ሁለቱም በቋንቋ አማካኝነት የሚገለጹ መሆናቸው ነው። ሁለተኛ፥ ሁለቱም ግጥሞች የአንባቢያቸውን ወይም የአድማጫቸውን ስሜት የመቆጣጠር ኃይል ያላቸው መሆናቸው ሲሆን፥ ሶስተኛው፥ ሁለቱም የተመጠነ የቃላት፣ የድምጽና የዜማ ስልት ያላቸው መሆናቸው ነው። ከዚህም በተጨማሪ የዘፈን ግጥሞች የተለያዩ ዘይቤዎችን በመጠቀማቸው፣ በአጻጻፍ ቅርፃቸው፣ በምስል ከሳችነታቸውና በመሳሰሉት ከሌሎች ግጥሞች ጋር አንድነትን ይጋራሉ።

የዘፈን ግጥሞች ከሌሎች ግጥሞች ጋር የሚዛመዱባቸውን ነጥቦች በዚህ መልክ ከተመለከትን፤ ቀጣዩ ጥያቄ ልዩነታቸው ታዲያ እምን ላይ ነው? የሚል ይሆናል። የመጀመርያው ልዩነት ሌሎች ግጥሞች በጽሁፍ የሚነበቡ ሲሆኑ፤ የዘፈን ግጥሞች ግን በጆሮ የሚሰሙ መሆናቸው ነው። ሌላው በመጽሐፍ የሚነበቡ ግጥሞች ከዘፈን ግጥሞች የተሻለ ነፃነት ያላቸው ናቸው። ይህ ማለት በዘይቤ አጠቃቀማቸው፣ በቃላት ምርጫዎቻቸው፣ በሀሳብ ገለፃቸው እና በመሳሰሉት እንደ ዘፈን ግጥም ቀላልና ግልጽ እንዲሆኑ አይጠበቅም። የዘፈን ግጥሞች ግን በተነጻጻሪ ቀላል ቃላትንና ያልተወሳሰቡ ሀሳቦች ያሏቸው እንዲሆኑ ይመከራል(ንጉስ፣ 2018፣ 21)። Eckstein (2010፣ 8) የዘፈን እና የመጽሐፍ ግጥሞችን ልዩነት በተመለከተ በሚከተለው መልክ ያብራሩታል። Unlike a poem, whose language can be abstract as a cubist painting, a lyric should be as direct as a high way sign. Most important, a lyric is designed to be sung... Every word should sing (Eckstein, 2010: 8)። በማለት ቋንቋው እንደ ስዕል ረቂቅ ከሆነው ግጥም በተለየ፤ የዘፈን ግጥሞች እንደ አውራ ጎዳና ምልክት ቀጥተኛ መሆን አለባቸው። ከሁሉ በላይ የዘፈን ግጥሞች ለመዘፈን የተደረሱ ናቸው... እያንዳንዱ ቃል መዘፈን እንደሚኖርበት ያስረዳሉ።

### 2.1.5. የዘፈን ግጥሞች ጭብጥና ተግባር

ጭብጥ፥ በስነ ጽሁፍ ውስጥ ደራሲው በገሀድ ወይም በውስጠ አዋቂ ትኩረት የሚያደርግበት የድርሰቱ ፍሬ ነገር ነው። ደራሲው የፈጠራቸውን የተለያዩ ገጸ ባህሪያት በልዩ ልዩ የህይወት ገጠመኝ እያሳለፈ በመጨረሻ የሚያስተሳስራቸው የድርሰቱ ዋና ዓላማ በሆነው ጭብጥ የተሰኘ ማዕከላዊ መዳረሻ ነው(ዘሪሁን፣ 2009፣ 185)። የዘፈን ግጥም አንዱ የስነ ጽህፍ አካል እንደመሆኑ በውስጡ በርካታ ጭብጦች ይተላለፉበታል። ለአብነት፥ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የስነ ልቦና፣ የፍቅር፣ የጥላቻ፣ የስደትና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

የዘፈን ግጥሞች ተግባር ብዙ ነው። "ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ ነው" እንዲሉ፤ በሙዚቃ ብዙ መልክት ማስተላለፍና ብዙሃኑ ማህበረሰብ ጋር መድረስ ይቻላል። Ransom (2015፣ 11) ሙዚቃና የዘፈን ግጥምን በተለመለከተ እንዲህ ይላሉ፥ "Music has long been an effective way to communicate to the masses, and lyrics have played a massive role." መልክቱ፥ ሙዚቃ ከሰፊው ማህበረሰብ ጋር ስኬታማው የመግባቢያ መንገድ ሲሆን፤ በዚህ ውስጥ የዘፈን ግጥሞች ትልቁን ሚና ይጫወታሉ የሚል ነው።

እያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደ ባህሉና አኗኗሩ፣ እንደ ልማዱና አስተሳሰቡ የራሱ የሆነ ዘፈኖች አሉት፤ ግጥሞች አሉት። በዘፈኖቹ ብሶቱን፣ ደስታውን፣ ተስፋውን፣ ታሪኩንና ማንነቱን ይገልፃል። በዘፈኖቹ ጉልበት ደካማውን ያበረታል፣ የበረታውንም ያሞግሳል። ለምሳሌ የስራ ዘፈኖችን በመጠቀም የሰነፈውን በማበረታታት ወደ ተሻለ ተግባር ያነሳሳል። የክብረ በዓል፣ የጦርነት፣ የአምልኮና የመሳሰሉ ዘፈኖችን እንደየ አውዳቸው በመጠቀም እንደዚሁ ማህበረሰባዊ ሂደቱን ያስጠብቅባቸዋል (ዘሪሁን፣ 2009፣46)።

ስለዚህ የዘፈን ግጥሞች በዘፈን ውስጥ በርካታ ተግባራትን ይከውናሉ። በግጥሞቻቸው አማካኝነት ያለፈውን በማስታወስ፣ ዛሬን በመግለጽና መጪውን በመጠቆም የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ይፈትሻሉ ልንል እንችላለን።

## 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የሚቀርበው የጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ሲሆን፤ ለዚህ ጥናት የተመረጠው ተግባራዊነት(Functionalism) ማህበረሰባዊ(Sociological) ንድፈ ሃሳብ ነው። የተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ ምንነትና ተግባር ቀጥሎ በዝርዝር ይቀርባል።

### 2.2.1. ተግባራዊነት (Functionalism)

ይህ ንድፈ ሀሳብ አንድን ማህበረሰብ ለማጥናት ከሚረዱ የማህበረሰብ ጥናት ንድፈ ሃሳቦች መካከል አንዱ ሲሆን፤ ህብረተሰብ እርስ በርሱ ተዋህዶና ተቀናጅቶ እንደ አንድ አካል የሚኖር ነው ብሎ ያምናል። እንደ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ የትኛውም ማህበረሰብ ከተለያዩ መዋቅሮች ስብስብ የተፈጠረ ነው። እያንዳንዱ ስብስብ ለማህበረሰቡ ቀጣይነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል(Hammond፣ 2010: 21)። እነዚህ ማህበረሰቡን የፈጠሩት ስብስቦች ወይም መዋቅሮች፥ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤቶች፣ የእምነት ተቋማት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የኪነ ጥበብ ቤቶች፣ መገናኛ ብዙሃን እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። Haralambos with Herald (2013፣ 12) ዋና ዋናዎቹን አካላት እንዲህ ይዘረዝሯቸዋል።

> The main parts of society, its institutions, such as the family, the economy, the educational and political systems are major aspects of the social structure. Thus, an institution can be seen as a structure made up of interconnected roles or interrelated norms.

የማህበረሰቡ ዋንኛ አካላትና ተቋማት፥ እንደ ቤተሰብ፣ ኢኮኖሚ፣ የትምህርትና የፖለቲካ ስርዓቶች ያሉት የማህበረሰቡ ዋንኛ መዋቅሮች ናቸው። ስለዚህ ተቋማቱ እርስ በርስ የተያያዙ ሚናዎች ያሏቸው መዋቅሮች ሆነው ሊታዩ ይችላሉ። እነዚህ ማህበረሰቦች የሚያበረክቱት አዎንታዊና አሉታዊ አስተዋጽኦ የማህበሩን ሁለንተናዊ ደህንነትና ቀጣይነት ያረጋግጣል። ይህ ማለት አዎንታዊ አስተዋጽኦዎች በበዙ ቁጥር ማህበረሰቡ የተረጋጋና ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች ይኖሩታል። በተቃራኒው አሉታዊ አስተዋጽኦዎችን የሚያበረክት የማህበረሰቡ አካል እየበዛ ሲሄድ፤ የማህበሩ ደህንነት ያልተረጋጋና ሰላም የራቀው ይሆናል የሚል ንድፈ ሀሳብ ነው።

በዚህ መሰረት የእያንዳንዱ ተቋም እንቅስቃሴ እርስ በርስ የተያያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። ያንዱ ህልውና ባንዱ ላይ የተመሰረተ ነው።

Haralambos with Herald (2013፣ 11) ተግባራዊነትን ለማስረዳት ከስነ ህይወት (Biology) ትምህርት ጋር በማገናኘት ምሳሌ ይሰጣሉ። እንደነዚህ አጥኚዎች ትንታኔ አንድ የስነ ህይወት ባለሙያ የሰው ልጅ አካል አጠቃላይ ደህንነትን ለመመርመር እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል(ለምሳሌ ልብ፣ ሳንባ፣ ኩላሊት፣ ጉበት፣ ዐይን፣ አዕምሮ ወዘተ) እንዴት ተቀናጅተው እንደሚሰሩ ማጥናት ይኖርበታል ይላሉ። ምክንያቱም አንዱን የሰውነት ክፍል ለመመርመር የግድ የሌሎቹንም ደህንነት ማረጋገጥ አለበትና ነው። በሰው ልጅ የሰውነት ክፍል ውስጥ በተናጠል የሚንቀሳቀስ አካል የለም። ሁሉም እርስ በርሱ የተደጋገፈ ነው። ዐይኑን የሚታከም ሰው ሌሎች የሰውነት ክፍሎቹንም አብሮ ያስመረምራል። እግሩን የተጎዳ ሰው ህመሙ ለእግሩ ብቻ አይቀርም፤ በመላ ሰውነቱ ተርፎ ያውከዋል። ስለዚህ የአንዱ አካል መጎዳት የሙሉውን የሰውነት ክፍል ጤንነት ያናጋል። የአንዱ አካል ጤናማነት እንዲሁ የሙሉውን የሰውነት ክፍል ደህንነት ያሻሽላል።

የተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች፤ ማህበረሰብም እንደዚሁ ነው በማለት ያስረዳሉ። የእያንዳንዱ ቤተሰብ ደህንነት ለማህበረሰቡ ጤናማ ጉዞ አዎንታዊ አስተዋፅኦው የጎላ ነው በማለት። በአንድ ሀገር ውስጥ ጤናማ ቤተሰብ ሲበዛ፥ ጤናማ ትምህርት ቤት እንዲኖር ያግዛል፣ የጤናማ ትምህርት ቤት መብዛት፣ ወንጀልን ይቀንሳል፣ ጤናማ ፖለቲካ ይፈጠራል፣ ጤናማ ፖለቲካ ሲኖር፤ ጤናማ ተቋማት ይበዛሉ፣ እነዚህም ሰላምና መረጋጋትን ያሰፍናሉ፣ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ያፋጥናሉ። በጥቅሉ ጤናማና ቀጣይነት ያለው ማህበረሰብ እንዲኖር ይረዳሉ። ለዚህ ነው፤ Hammond (2010: 21) “The functionalist theory claims that society is in a state of balance and kept that way through the function of society’s component part.” በማለት፤ በተግባራዊያን ንድፈ ሀሳብ አረዳድ፤ የአንድ ማህበረሰብ ሚዛን የሚጠበቀው፤ ማህበረሰቡን እንደማህበረሰብ ባቆሙት ልዩ ልዩ አካላት ተግባር እንደሆነ መግለጹ።

ይህ ካልሆነ ግን ጤናማ ማህበረሰብ አይኖርም፤ ወይም ማህበራዊ ቀውስ(dysfunction) ይፈጠራል። ይህ ማለት፤ የጤናማ ቤተሰብ አለመመስረት፤ ወንጀልንና ስርዓት አልበኝነትን የሚያባብስ ትምህርት ቤት ይፈጥራል። በወንጀል የተሞሉ ትምህርት ቤቶች፤ ስርዓት አልባ ፖለቲከኞችን ያባዛሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ ቀውሱ በመላው ማህበረሰብ ውስጥ እንዲዛመት

ያደርጋል፡፡ ይህም ማህበራዊ ቀውስን ያስከትላል፡፡Hammond (2010፣ 21) እንዲህ ዓይነቱ ማህበራዊ ቀውስ ሲፈጠር ወይም እንዳይፈጠር በተግባረውያን ንድፈ ሀሳብ ዘንድ የተሻለ ግንዛቤ አለ በማለት በሚከተለው መልክ ያስረዳሉ፡፡

> Functionalists realize that just like the body, societies get "sick" or dysfunction. By studying society's parts and processes, Functionalists can better understand how society remains stable or adjust to destabilizing forces when unwanted change is threatened.

ከላይ ከቀረበው ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔ እንደምንገነዘበው፤ ተግባራውያን፡- ልክ የሰውነታችን አካል እንደሚታመመው ሁሉ፤ ማህበረሰብም እንደዚሁ ይታመማል፤ ወይም ቀውስ ይፈጠርበታል በማለት ያምናሉ፡፡ ሆኖም፤ የዚህ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች የማህበረሰቡን ህመም ለማከም፤ የማህበረሰቡን አካላት[7] እና ቀውስ የፈጠሩ ማህበረሳዊ ሂደቶችን በማጥናት፤ አንድን ማህበረሰብ ሰላማዊ ፍሰቱን ጠብቆና ባለበት ረግቶ እንዲቆይ ወይም አላስፈላጊ ለውጦችን እንዴት ማስተካከል እንደሚገባ የተሻለ ግንዛቤ አለን የሚሉ ናቸው፡፡

### 2.2.2. ለውጥ በተግባራውያን ዕይታ

በማርክሳዊው ንድፈ ሃሳብ፥ ለውጥ በገዢው መደብ እና በሰራተኛው መደብ መካከል በሚፈጠር ትግል የሚመጣ መዋቅራዊ ለውጥ ነው፡፡ ተግባራዊያን ግን ይህንን አይቀበሉም፡፡ እንደ ተግባራውያን ንድፈ ሃሳብ ለውጥ ዘገምተኛና ረጅም ሂደት ነው፡፡ ንጉስ(2018፣ 32) ላይ Parsons(1940)ንን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት፥ በተግባራዊያን ንድፈ ሀሳብ አረዳድ፤ ለውጥ በሂደት የሚገኝ እንጂ በገዢውና በሰራተኛው መደብ መካከል በሚፈጠር ትግል የሚመጣ መዋቅራዊና መሰረታዊ (Complete structural changes) ለውጥ አይደለም፡፡ ይልቁንም ሂደታዊ ለውጦች ቀስበቀስ በማህበረሰባዊው ስርዓት ውስጥ አዎንታዊ ቅቡልነትን እያገኙ ይሄዳሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ወደማህበረሰቡ በሂደት የሚሰርጹ በመሆናቸው ማህበራዊ ስሪቱን የማናጋትና ማህበራዊ ቀውስ የመፍጠር እድላቸው እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡

እንደተግባራውያን ንድፈ ሀሳብ አራማጆች ገለጻ፤ አንድ ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ጤናማ ሆኖ እንዲቀጥልና አላስፈላጊ ለውጦች ወይም ሃሳቦች የማህበረሰቡን እሴት እንዳይሸረሽሩ

[7] ቤተሰብ፣ ልዩ ልዩ ተቋማት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የእምነት ቤቶች፣ የጥበባት ጉባኤዎች እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

መደረግ ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። Haralambos with Herald (2013፣13) እንደሚያስገነዝቡት፥ አንድ ማህበረሰባዊ ስርዓት እንደ ስርዓት መቀጠል ካለበት ከሁሉ በፊት ማህበረሰቡ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ማስጠበቅ መቻል አለበት። እነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች የተግባራዊነት ቅድመ ሁኔታዎች በመባል ይታወቃሉ። ዋና ዋናዎቹ አራት ነጥቦች ናቸው። እነዚህም፤

- እያንዳንዱ ስርዓት ከአካባቢው ጋር ስሙም መሆን አለበት።
- እያንዳንዱ ሰርዓት ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችለው ዘዴ ሊኖረው ይገባል።
- እያንዳንዱ ስርዓት ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ወይም ማህበራዊ መዋቅር የሚያስተሳስርበትን መንገድ መቀየስ አለበት።
- እያንዳንዱ ስርዓት ስጋቶችን የሚቆጣጠርበትን ዘዴ መቀየስ አለበት።

እነዚህ ነጥቦች በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ዋጋ ያላቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው። በተለይ ኢኮኖሚ፣ ትምህርት፣ እምነትና የህግ ስርዓት በሁሉም ህብረተሰባዊ ስርዓት ውስጥ በተለያየ መልክ ሊገኙ የሚችሉ እንደመሆናቸው፤ ከላይ በተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች ልክ ካልተያዙ ማህበራዊ ህመም ማስከተላቸው አይቀሬ ነው በማለት ያስረዳሉ (Haralambos with Herald፣ 2013፣ 14)።

ይሁንና በአንድም በሌላ ምክንያት፤ እነዚህ ከላይ የተገለጹት አራት ማህበረሰባዊ ሚዛን መጠበቂያ ነጥቦች፤ ሚዛናቸውን ጠብቀው መሄድ ካልቻሉ፤ ማህበራዊ ቀውስ(dysfunction) ሊያጋጥም ይችላል። ማህበራዊ ቀውስ ውጤቱ፡- የፍትህ መዛባት፣ የዲሞክራሲ መጥፋት፣ የፖለቲካ ስርኣት መናጋት፣ የወንጀል መብዛትና መሰል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖሊካዊ ችግሮችን የሚያስከትል ነው።

ማህበራዊ ቀውስ፤ የማህበራዊ ስርዓቱን ጉዞ ጤናማነት ይገዳደራል። ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ ታዲያ ህዝቦች ማህበራዊ ሚዛኑን ለማስጠበቅ እንዲነሱና ለአዲስ ለውጥ ሂደት እንዲታገሉ ይገፋፋል። ማህበራዊ ትግሉ አንድም በተለያዩ ተቋማት፤ አንድም በግለሰቦች ተግባራት የሚገለጽ ሲሆን፣ ውጤቱ በተለያዩ ኪነጥበባዊ ስራዎች(ለምሳሌ በዘፈን)ና በሌሎች መንገዶች ሊንጸባረቅ ይችላል(ዝኒ ከማሁ፣15)።

ስለዚህ፥ ይህ ጥናት፤ በለውጥ ሰሞን ላይ ያተኮሩ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦችን በመፈተሽ፤ በለውጥ ሰሞን ላይ የተነሱ ዋና ዋና ጭብጦችን ለይቶ ተንትኖ አቅርቧል።

### 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ፤ ከጥናቴ ጋር በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚዛመዱ የመጀመሪያ ዲግሪ፥ የሁለተኛ ዲግሪ፥ የጆርናል መጣጥፎችና የሶስተኛ ዲግሪ ጥናቶች ተዳሰዋል። ጥናቶቹ እንደተነሱበት ዓላማ ለየቅል ግብን ያነገቡ ቢሆንም፤ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያዛምዳቸውና የሚያለያያቸው አንኳር ጉዳይ ተነስቶ ተፈትሿል። ይህ ጥናት ያተኮረበት ፍሬ ነገርም ተለይቷል።

ከዚህ ጥናት ጋር በአንድም በሌላ ይዛመዳሉ ብዬ የመረጥኳቸው ጥናቶች በቁጥር ሰባት ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ የመጀመርያ ዲግሪ፥ ሶስቱ የሁለተኛ ዲግሪ፥ አንዱ የጆርናል መጣጥፍና ቀሪው አንዱ የሶስተኛ ዲግሪ ጥናቶች ናቸው። እያንዳንዳቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ቅርበትና ርቀት በቅደም ተከተላቸው መሰረት ቀጥለው ተፈትሸዋል። ሁሉም ጥናቶች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች የተገኙ ሲሆኑ፤ እነዚህም፥ ከቋንቋና ስነ ጽሁፍ፣ ከያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት፣ ከስነ ፆታ ጥናት(Gender Studies)፣ ከውጭ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ እና ከትምህርት ባህሪ ጥናት ትምህርት ክፍሎች የተገኙ ናቸው። ከሌሎች ትምህርት ክፍሎች(ለምሳሌ ሶሾሎጂ፣ አንትሮፖሎጂ፣ ታሪክ) መሰል ጥናቶችን ለማግኘት ሙከራ ተደርጓል። ከተለያዩ ድረ ገጾች ላይም እንዲሁ መሰል ጥናቶችን ለማግኘት ተሞክሯል። ይሁንና ለዚህ ጥናት ርዕስ የቀረቡ ጥናቶች አላጋጠሙኝም።

ከዚህ ጥናት ጋር ባላቸው መጠነኛ ዝምድና፤ በመጀመርያ የማነሳቸው ሁለቱን የመጀመርያ ዲግሪ ጥናቶችን ይሆናል። እነዚህም "የሶስት የወታደር የሙዚቃ ክፍሎች ዘፈኖች የአማርኛ ግጥም ጥናት" በሚል ርዕስ በፈቃደ አዘዘ በ1965 ዓ.ም የቀረበ ጥናት እና "ከ1966 ዓ.ም ወዲህ በብሔራዊ ትያትር የዘመናዊ ኦርኬስትራ የቀረቡ ግጥሞች ቅርጽና ይዘት" በሚል ርዕስ በ1971 ዓ.ም በታምራት ገሰሰ የቀረበ ጥናት ናቸው። ሁለቱም ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቋንቋዎች ጥናት ለመጀመርያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ናቸው።

የመጀመርያው የፈቃደ አዘዘ ጥናት የሶስት የወታደር የሙዚቃ ክፍሎች፤ ማለትም- የክቡር ዘበኛ፥ የምድር ጦር እና የፖሊስ ሰራዊት የሙዚቃ ስራዎችን የሚያጠና ነው። ጥናቱ ከ1960 እስከ 1965 ዓ፥ም በሶስቱ የወታደር ክፍሎች የተሰሩ ዘፈኖችን ተመልክቷል። በፈቃደ ጥናት መሰረት ሶስቱ የሙዚቃ ክፍሎች በአራት ዓመታት ስራዎቻቸው በተለይ ሶስት ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገዋል። እነዚህም ፍቅር፥ ስራና ሞት ሲሆኑ፤ የፍቅር ዘፈኖች ከሁሉም በቁጥር

ልቀው ተገኝተዋል። በዘመኑ የሳንሱር ህግ ምክንያት ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ዘፈኖች ብዙም ሊሰሩ እንዳልቻሉ ያነሳሉ።

የፈቃደ ጥናት ዋና ጉዳይ፤ በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ በሶስቱ የወታደር ክፍሎች የተሰሩ ዘፈኖችን ይዘቶች ማጥናት ነው። ከዚህ አኳያ ይዘቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። ልቀው የተገኙትን ይዘቶችና አንሰው የተገኙትን ይዘቶች ከነምክንያቶቻቸው ለማስረዳት ጥረዋል። በሶስቱ የወታደር ክፍሎች የተሰሩ ዘፈኖችን ሁሉንም ሰብስበው በማጥናት የዘመኑን ዋና ዋና ተተኳሪ ጉዳዮች በወጉ ፈትሸዋል። ይሁንና ጥናቱ ሁለት ድክመቶች አሉበት። አንደኛ ጥናቱ በንድፈ ሀሳባዊ ንባብ ያልተቃኘ መሆኑ ሲሆን፤ ሁለተኛው ጥናቱ በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ የተቀነበበ አለመሆኑ ነው። ይህም ትኩረቱን በመበተን ጥናቱን ጥልቀት አሳጥቶታል።

የፈቃደን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው፤ አንደኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ በመሰራቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው የግጥሞቹ ይዘት ላይ በማተኮሩ ብቻ ነው። በተረፈ የፈቃደ ጥናት ከ1960-1964 ባሉ አራት ዓመታት ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲሆን፤ የኔ ጥናት ከ1966 ዓ.ም ወዲህ የሚጀምር በመሆኑ፥ የፈቃደ ጥናት በሶሰት የወታደር የሙዚቃ ክፍሎች የተሰሩ ዘፈኖችን ላይ ብቻ የተገደበ ሲሆን፤ የኔ ጥናት በሙዚቃ ክፍሎች ያልተገደበ በመሆኑ እና የለውጥ ሰሞን ዘፈኖች ላይ በማተኮሩ የተለየ ያደርገዋል።

ሁለተኛው በዘፈን ግጥሞች ላይ የተሰራ የመጀመርሪያ ዲግሪ ጥናት የታምራት ገሰሰ ጥናት ነው። ይህ ጥናት ትኩረቱን በብሔራዊ ትያትር የዘመናዊ ኦርኬስትራ ከ1966 ወዲህ የተሰሩ ዘፈኖች ላይ አድርጓል። ታምራት ጥናቱን ፖለቲካዊ፥ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ በሚሉ ሶስት ጎራዎች ከፋፍሎ ተመልክቷቸዋል። በነዚህ ሶስት ጎራዎች የሚያርፉ የዘፈን ግጥሞችን በመለየትም የግጥሞቹን ቅርፅና ይዘት ለመተንተን ሞክሯል። ታምራት ከተነሳበት ዓላማ አንፃር፥ ቅርጽ ላይ የተሻለ ፍተሻ አድርጓል። ይዘትን በተመለከተ ግን በበቂ ሁኔታ ፈትሿል ለማለት አያስደፍርም። አካሄዱ ሳይንሳዊ መንገድን የተከተለ ትንተናም አይደለም። ለንባቡ የመረጠው ንድፈ ሀሳብም የለውም። በዚህ ምክንያት የጥናቱ እይታ(perspective) ከምን አንፃር እንደተቃኘ አታወቅም።

የታምራት ጥናት ምንም እንኳ ቅርፅና ይዘትን የተነተነበት መንገድ ብዙም ሳይንሳዊ ሂደትን ተከትሏል ለማለት ባያስደፍርም፤ ቢያንስ ይዘቶችን ከፋፍሎ ለመመልከት በመሞከሩ ከዚህ ጥናት ጋር ያዛምደዋል። እንዲሁም ጥናቱን ከ1966 ዓ.ም ወዲህ መጀመሩ ከኔ ጥናት ጋር

በመጠኑም ቢሆን የዘመን ተጋሪ ያደርገዋል፡፡ ይሁንና የታምራት ጥናት አንደኛ የብሔራዊ ትያትር ዘመናዊ ኦርኬስትራ ዘፈኖች ላይ ብቻ በማተኮሩ፣ ሁለተኛ ቅርፅና ይዘት ላይ በማጥናቱ(የኔ ጥናት ቅርፅን ስለማያጠና) እና የኔ ጥናት የለውጥ ሰሞን በተሰሩ የዘፈን ግጥሞች ላይ በማተኮሩ ጥናቶቹን ለየቅል ያደርጋቸዋል፡፡

ከሁሉ በላይ የፈቃደና የታምራት ጥናቶች ለመጀመርያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ እንደመሆናቸው፤ ይህ ጥናት በሚሰራበት ወሰን እና ንድፈ ሀሳብ ልክ የተሰሩ ባለመሆናቸው ዝምድናቸውን የጠበበ ያደርገዋል፡፡

በሁለተኛነት የተመለከትኳቸው በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን ነው፡፡ ከኔ ጥናት ጋር ባላቸው ቅርበት የመረጥኳቸው ሶስት የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች ሲሆኑ፤ ሶስቱ ጥናቶች ለዚህ ጥናት ባላቸው ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ዝምድና መሰረት ተቃኝተዋል፡፡ ስለዚህ በመጀመርያ መጠነኛ ቀረቤታ ያላቸውን ጥናቶች በማስቀደም ከፍ ወዳለው ተዛማጅ ጥናት ተሻግሬያለሁ፡፡

በቅድሚያ የተመለከትኩት “Analysis of Ethiopian ‘Kignts’ used dominantly in popular songs produced as commercial music in the 1960-1980s: The Modern recording songs in Addis Ababa” በሚል ርዕስ በህሊና ፍቃዱ በ 2020 እ. ኤ. አ ለያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናትን ነው፡፡ ጥናቱ ከ1960ዎቹ እስከ 1980ዎቹ በአዲስ አበባ የምሽት ጭፈራ ቤቶች የተዘወተሩ የሙዚቃ ስልቶችን ይመረምራል፡፡ በተለይም ትዝታ፣ ባቲ፣ አንቺ ሆዬና አንባስል የተሰኙ የሙዚቃ ስልቶች በምሽት ክለቦቹ የተዘወተሩ ስልቶች ስለመሆናቸው የህሊና ጥናት ያሳያል፡፡ ይሁንና ይህ ጥናት ሙዚቃ ላይ ከመሰራቱና የዘመን ወሰኑ ከኔ ጥናት ጋር የተቀራረበ ከመሆኑ ውጭ የቀረ አንድነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ በሙዚቃ ስልቶች ላይ የተካሄደ በመሆኑ ከኔ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና እጅግ ሰፊ ሆኗል፡፡ የህሊና ጥናት ሙዚቃዊ ቅንጣቶች ላይ ሲያተኩር የኔው በዘፈን ግጥሞች ላይ የሚደረግ ጥናት ነው፡፡ ስለዚህ የሁለቱ ጥናቶች ትኩረት ለየቅል በመሆኑ ቅኝቴን እዚሁ ላይ ገትቼ ወደ ቀጣዩ ጥናት እሻገራለሁ፡፡

ሁለተኛው “GENDER ISSUES AND WOMEN’S PORTRAYAL IN SECULAR AMHARIC SONGS PRODUCED IN CASSETTES (IN 1997 E.C.)” በሚል ርዕስ በፅዮን ዮሐንስ በ 2007 እ.ኤ.አ. ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ GENDER STUDIES በሁለተኛ

ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት ነው። ጥናቱ በ1997 ዓ.ም በካሴት የተሰሩ የዘፈን ግጥሞችን በመመርመር ሴቶች በዘፈን ውስጥ የተሳሉበትን አግባብ ከእንስታዊያን(Feminism) ንድፈ ሀሳብ አንፃር ይቃኛል። በግኝቱም ሴቶች በዘፈን ግጥሞች ውስጥ አሉታዊ በሆነ መንገድ ቀርበዋል ሲል ይደመድማል።

የጽዮን ጥናት አጠቃላይ ቅኝቱ ሴቶች በዘፈኖች ውስጥ እንደምን ተስለዋል የሚል እንደመሆኑ፤ ሴቶች በአሉታዊና በዎንታዊ ሁኔታ በዘፈኖች ውስጥ እንደምን እንደተቀረጹ በጥናቷ አሳይታለች። በሴቶች ላይ የሚደርስን አካላዊና ስነ ልቦናዊ ተፅዕኖ በዘፈኖች ውስጥ እንደምን እንደተስተዋሉ በሚገፈባ ፈትሻለች። በሴቶችና በወንዶች መካከል የስራና የተዋረድ (አዛዥ፣ታዛዥ) ክፍፍልን በተመለከተ በዘፈን ግጥሞቹ እንደምን ሰርፀው እንደታዩም ለማሳየት ሞክራለች። በተጨማሪ፥ ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀመችው ንድፈ ሀሳባዊ ንባብም በጥንካሬ የሚታይ ነው። ይሁንና፥ አንዳንድ ድምዳሜዎች የተገቡ አይመስሉም። ለምሳሌ፥ ግጥሙ በአዎንታዊ ጎኑ መታየት ሲገባው አሉታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ በማተኮር፤ ሴቶች በተሳሳተ አኳኋን ተስለዋል ወደሚል ድምዳሜ የሚንደረደሩ አልፎ አልፎ የሚታዩ ትንታኔዎች አሉ። የተጋነኑና የኢትዮጵያን ሴቶች ነባራዊ ሁኔታ ባላገናዘበ መልኩ የተተነተኑ ጉዳዮችም ይስተዋሉበታል። ንድፈ ሀሳባዊ ንባቡ(እንስታዊነት) ለተመረጡት ቴክስቶች የተመቸ ቢሆንም፤ ከኢትዮጵያ ማህበረሰባዊ ስነ ልቦና አንፃር ቢታይ ኖሮ የተሻለ ውጤት ያስገኝ ነበር ባይ ነኝ።

የጽዮን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር ቢኖር አንደኛ፥ ጥናቱ የሙዚቃ ግጥሞች ይዘት ላይ በመሰራቱ ነው። ሁለተኛ፥ በአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ አተኩሮ በመሰራቱ ነው። ከዚህ ውጭ በጥናት ወሰኑ፣ በንድፈ ሀሳብ ምርጫውና በመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ከኔ ጥናት ጋር ፍፁም የተለየ ነው።

ሶስተኛው፤ "THEMATIC SIGNIFICANCE OF BIBLICAL ALLUSION IN CONTEMPORARY AMHARIC SONGS" በሚል ርዕስ በእንዳለ በሽር በ2009 እ.ኤ.አ. ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውጭ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ ክፍል የቀረበ ጥናት ነው። ይህ ጥናት ከርዕሱም እንደምንረዳው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በዘፈን ግጥሞች ውስጥ ያካተቱ ስራዎች ላይ የሚያተኩር ነው። የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ሀሳብን በማጉላት ረገድ ትልቅ ሚና ስለመጫወታቸው ይፈትሻል። ጥናቱ ከተነሳበት ዓላማ አንፃር ተፈላጊዎቹን ጉዳዮች አንስቷል። በአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ውስጥ የተስተዋሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጉዳዮችን አሳይቷል።

ከዚህ ተነስተን የእንዳለ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር ያለውን ዝምድና ስንመዝን እስካሁን ካየናቸው ጥናቶች ብዙ የተለየ አይደለም። ዝምድናው አንደኛ፤ ጥናቱ በዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ላይ የተሰራ መሆኑ ነው። ሁለተኛ፥ በአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ ብቻ መወሰኑ ነው።

የመጨረሻው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት "Content Analysis of secular Amharic Songs produced in Cassettes (1972-1994): Implication for curriculum planning" በሚል ርዕስ በ1995 እ.ኤ.አ. በውቤ ካሳዬ የቀረበ ጥናት ነው። ጥናቱ እስካሁን ካየናቸው በተሻለ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው በመሆኑ፤ ሰፋ ያለ ዳሰሳ ተደርጎበታል። ይህ ጥናት በርዕሱ እንደተመለከተው ከ1972-1994 እ.ኤ.አ. በካሴት የታተሙ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ የዘፈኖቹን የግጥም ይዘት ከተነሳበት የጥናት ዓላማ (Implication for curriculum planning) አንፃር ለመፈተሽ ይሞክራል። በዚህ ጥናት፤ ውቤ የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን ዘመን በከፊል፣ የደርግ ዘመንን በሙሉና የኢህአዴግ ዘመን የሽግግር ወቅት የካሴት የዘፈን ግጥሞችን በአሃዛዊ የጥናት ዘዴ ተመልክቷቸዋል። በዚህ መሰረት የግጥሞቹን ይዘት በአምስት ጎራ የከፋፈላቸው ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው ይዘቶች፣ በየዘመኑ ያላቸውን ሽፋን በፐርሰንት አስልቶ አስቀምጧቸዋል።

በውቤ ጥናት አምስቱ ዋና ዋና ይዘቶች የፍቅር፣ የፖለቲካ፣ መልካአ ምድራዊ፣ ግለሰባዊ-ማህበራዊና ባህላዊ፣ ልዩ ልዩ ሁነቶች የሚሉ ናቸው። በጥናቱ ግኝት መሰረት ከሁሉም ልቆ የተገኘው የፍቅር የዘፈን ግጥም ነው። በፐርሰንት ሲሰላ ከአጠቃላዩ 55%ቱን እንደሚወስድ ጥናቱ አስቀምጧል። ግለሰባዊ፥ ማህበራዊና ባህላዊ የሚለው ጎራ ቀጣዩን ደረጃ(18%) ሲይዝ፤ መልካ ምድራዊ(10%)፣ ፖለቲካዊ ግጥሞች(9%)፣ ልዩ ልዩ ከበራዎች የሚለው የመጨረሻውን ደረጃ (3%) ይዟል። ከዚህ በመነሳት ሁለት ቁም ነገሮችን መውሰድ የሚቻል ይመስለኛል። አንደኛ ይህ ጥናት ተጨማሪ ይዘቶችን(በሌሎች ጥናቶች ያልተካተቱ፤ ለምሳሌ ፈቃደ 1965) ተመልክቷል። ሁለተኛ ከዚህ በፊት እጅግ አንሰው የተመለከትናቸው ፖለቲካዊ የዘፈን ግጥሞች በዚህ ጥናት ከፍ ብሎ ታይቷል። ነገር ግን ጥናቱ እነዚህን ይዘቶት የፍቅር፣ የፖለቲካ፣ መልካ ምድራዊ ወዘተ እያለ ከመዘርዘር በዘለለ፤ የትኞቹ ግጥሞች ፍቅርን፣ የትኞቹ ፖለቲካውን፣ የትኞቹ ሌላውን ይዘት እንደወከሉ በግልፅ አላስቀመጠም። የውቤ ጥናት መደምደሚያ ከነዚህ ግኝቶች በመነሳት የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ እንዴት ሊቃኝ እንደሚገባ ማሳየት ነው።

የእኔና የውቤን ጥናት የሚያቀራርባቸው፤ አንድም የዘፈን ግጥሞች ላይ በመሰራታቸው ነው። አንድም የሚዳስሱት ዘመን ከሞላ ጎደል የተቀራረበ በመሆኑ ነው። እንዲሁም ጥናቶቹ በዘፈን

ግጥሞች ጭብጥ ላይ በማተኮራቸው ነው፡፡ ይሁንና የእኔና የውቤ ጥናቶች የሚለያዩባቸው ቢያንስ አራት መሰረታዊ ነጥቦች አሉ፡፡ አንደኛ የትንተና ዘዴያችን ነው፡፡ የውቤ ጥናት አሀዛዊ (Quantitative) የጥናት ዘዴ ላይ በመመርኮዝ፤ ይዘቶችን በቁጥር ከፋፍሎ ሲያስቀምጥ፤ የእኔ ጥናት የዘፈን ግጥሞችን(ቴክስቶችን) ዓይነታዊ (Qualitative) የጥናት ዘዴን በመጠቀም ይፈትሻል፣ ይፈክራል፡፡ ሁለተኛ የእኔ ጥናት ከ1966-1986 ዓ.ም ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ የውቤ ጥናት እ.ኤ.አ ከ1972-1994 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ1964-1986) ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በመሆኑም፤ ምንም እንኳ መዳረሻ ዘመናቸው ተመሳሳይ ቢሆንም፤ ከመነሻቸው የሁለት ዓመታት ልዩነት አላቸው፡፡ ሶስተኛ የውቤ ጥናት ምንም ዓይነት ንድፈ ሀሳብ ያልተጠቀመ ሲሆን፤ የእኔ ጥናት የማንጸሪያ ንድፈ ሀሳብን ይዞ ቴክስቶችን የሚፈክር ነው፡፡ አራተኛ የኔ ጥናት ትኩረት የለውጥ ሰሞን የቀረቡ የዘፈን ግጥሞች ላይ ብቻ የሚያተኩር እንጂ የተጠቀሰውን ዘመን ሁሉ የሚዳስስ ባለመሆኑ ከውቤ ጥናት ይለየዋል፡፡

በጆርናል ደረጃ ከታተሙ ተዛማጅ ጥናቶች መካከል የትምክኽት ተፈራ (2009). “The Role of Political Songs in Ethiopia During the Long-Protracted War (1974-1991): A Case Study on Identity, Integration and Conflict in Central and Northern Ethiopia.” የሚለው ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ጥናት በተለይ በደርግ ዘመን የተዘፈኑ ፖለቲካዊ ዘፈኖችን በማንሳት ለመተንተን ይሞክራል፡፡ የፖለቲካ ጭብጥ ያላቸው ዘፈኖችን በሁለት ጎራ ከፍሎ ያሳያል፡፡ አንድም ገዢውን(ወታደራዊውን መንግስት) በማገዝ(የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ በመሆን)፣ አንድም በተቃራኒ ጎራ፥ ገዢውን ኃይል በመንቀፍና ህዝቦችን ለትግል በማነሳሳት፤ ዘፈኖች የተጫወቱትን ሚና ያስመለክታል፡፡  ሆኖም የትምክኽት መጣጥፍ ትኩረቱ በፖለቲካዊ ዘፈኖች ላይ ብቻ የተገደበ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የወሰን ልዩነት ፈጥሯል፡፡

በመጨረሻ የተመለከትኩት “Thematic Analysis of Selected Amharic Song Lyrics: A Sociological Approach”፤ በሚል ርዕስ በንጉስ ይልማ በ2018 እ.አ.አ.፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለውጭ ቋንቋና ስነ ጽሑፍ ዲፓርትመንት ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናትን ነው፡፡ ይህ ጥናት በተመረጡ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ የተደረገ በመሆኑ፤ እኔ ከማነሳው ጉዳይ ጋር ከፍ ያለ ቀረቤታ አለው፡፡ ጥናቱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘት ያላቸውን የዘፈን ግጥሞች በመተንተን የየዘመኑን አንደምታ ለመፈከር ይሞክራል፡፡ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስከ ኢህአዴግ ዘመን ያለውን የሶስት መንግስታት ዘፈኖችን በመፈከርም

የየዘመኑን ሙዚቃዊ ጭብጥ አጉልቶ የሚያሣይ ጥናት ነው፡፡ በተጨማሪም የየመንግስታቱን ርዕዮተ ዓለማዊ አስተምሮ በዘፈኖቹ ግጥሞች ውስጥ ለማሳየት ጥረት የሚያደርግ ሰፊ ጥናት ነው፡፡ ይሁንና፥ ጥናቱ ከተነሳበት ዓላማ አንፃር የየዘመኑን ጭብጦች በሚገባ ፈትሿል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ለምሳሌ በዘመነ ኢህአዴግ ብሎ የተመለከታቸው ዘፈኖች ዘመኑን ለመወከል ብቁ አይደሉም፡፡ አንደኛ የተመረጡት ዘፈኖች ከ1986 ዓ.ም ወዲህ የተሰሩ በመሆናቸው የኂላውን(ከ1983 እስከ 1986) ያለውን ዘመን ዘንግቶታል፡፡ ይህ ጊዜ፥ በርካታ ዘፈኖች የተሰሩበት፣ የጊዜውን ነገር በአንድም በሌላ የሚያጠይቁ ዘፈኖች የተሰሙበት ሆነው ሳለ፤ አጥኚው በወጉ ሳዳስሱ አልፈውታል፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ምን ያገናኘዋል ካልን? ዋናው ጥናቱ የለውጥ አካባቢ ዘፈኖችን በመጠኑም ቢሆን ለመዳሰስ መሞከሩ ነው፡፡ ጥናቱ ከያዘው ሰፊ ወሰን አንጻር ለውጥ ላይ ብቻ አተኩሮ የተለየ ጥናት ባያካሂድም፤ አልፎ አልፎ የነካካቸው የለውጥ ሰሞን የዘፈን ግጥሞች ትልቅ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ያም ሆኖ ግን ጥናቱ ለጉዳዩ በቂ ትኩረት አልሰጠም፡፡ ሌላው የንጉስ ጥናት፤ ተግባራዊ(Functionalism)፣ ግጭት(Conflict) እና ትዕምርታዊ መስተጋብር(Symbolic interactionism) የሚሉ ንድፈ ሀሳቦችን በመጠቀም የተሰራ ሲሆን፤ ይህ ጥናት ከሶስቱ ንድፈ ሀሳቦች አንዱን ብቻ በመውሰድ(Functionalism) የተሰራ በመሆኑ መጠነኛ ዝምድናን ፈጥረዋል፡፡ ትኩረታቸው ግን ለየቅል ነው፡፡ የንጉስ ጥናት አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ ሲያተኩር፤ የኔ ጥናት ግን በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ ግጥሞች ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የጥናት ወሰናችን የተለያየ ነው፡፡ ይህ ጥናት በሁለት ለውጦች ሰሞን ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የንጉስ ጥናት ግን ሰፋ ብሎ የሶስት መንግስታትን(የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን፣ የደርግ ወታደራዊ መንግስትና የኢህአዴግ) ዘመናትን የሚፈትሽ ነው፡፡

በመሆኑም፥ ይህ ጥናት የለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ላይ አተኩሮ፤ እስካሁን የፈተሽኳቸው ክፍተቶች ላይ ተመስርቶ የተሰራ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## የለውጥ ሰሞን የዘፈን ግጥሞች ጭብጥ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፥ በለውጥ ላይ አተኩረው የተሰሩ የለውጥ ሰሞን የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦች፥ ጥናቱ ካነሳቸው አብይ ጥያቄዎችና ንድፈ ሀሳብ አንፃር ተፈትሸዋል። የለውጥ ሰሞን የዘፈን ግጥሞቹ በዋናነት በሶስት ጎራ ተከፍለው የታዩ ሲሆን እነዚህም፥ የለውጥ ዋዜማ፣ የለውጥ ጊዜ እና የለውጥ ማግስት በሚል የተከፈሉ ናቸው። በዚህ ጥናት፤ የለውጥ ሰሞን ማለት በጥናቱ ወሰን ላይ እንደተቀነበበው፤ ከለውጥ ዋዜማ እስከ ለውጥ ማግስት ያለውን ጊዜ የሚያጠቃልል ነው። የለውጥ ዋዜማ የሚባለው፥ ለውጥ ከመከሰቱ ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ፤ ለውጥ እስከተካሄደበት እለት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያካትት ነው። የለውጥ ጊዜ ሲባል ደግሞ፥ ለውጥ ከተከሰተበት እለት ጀምሮ ወደፊት የሚቆጠሩ ሁለት ዓመታትን የሚመለከት ሲሆን፤ ከሁለት ዓመት በኋላ የሚቆጠሩት ሁለት ዓመታት ደግሞ፤ የለውጥ ማግስት በሚል የቀረቡ ናቸው። ስለዚህ፥ በዚህ ቀመር መሰረት፤ የ1966 እና የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ፣ የለውጥ ጊዜና የለውጥ ማግስት የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ጭብጦች በቅደምተከተል ተተንትነው ቀርበዋል።

### 3.1. የለውጥ ዋዜማ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ጭብጦች

#### 3.1.1. የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች

በኢትዮጵያ የለውጥ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ምዕራፍ ያለው ነው የ1966ቱ ለውጥ። አንድም፥ ለዘመናት የዘለቀው የሰለሞናዊ ስርወመንግስት መቋጫውን ያገኘበት ለውጥ በመሆኑ፤ አንድም፥ የንጉሳዊው ፊውዳል ስርዓት የተገረሰሰበት በመሆኑና የታችኛው መደብ ኃይል ስልጣን መቆናጠጥ የቻለበት ጊዜ በመሆኑ ለውጡን ከእስካሁኖቹ ለውጦች የተለየ ያደርገዋል(ባህሩ፣ 2002፣ 235)።

በዚህ በ1966 ዓ.ም የለውጥ ዋዜማ፤ በአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ላይ የሚስተዋሉት ጭብጦች ብዙ ዓይነት ሊሆኑ ቢችሉም፥ በተለይ በለውጡ ላይ አተኩረው የተዘፈኑት የዋዜማ ዘፈኖች በሁለት አበይት ጭብጦች ላይ ያተኮሩ ሆነው ተገኝተዋል። የመጀመርያው አሮጌው ስርዓት አክትሞ አዲስ የዲሞክራሲና የኢኮኖሚ ተስፋን የሰነቀ ስርዓት እየመጣ መሆኑን የሚጠቁሙ

ስንኞች ናቸው፡፡ ቀኑ ሊነጋ ነው፣ ሰላም እኩልነት ሊሰፍን ነው የሚሉ ዘፈኖች፤ የጊዜውን የሲቪልና የወታደር የለውጥ እንቅስቃሴ የሚደግፉ ዘፈኖች፤ በግልፅም በምስጢርም(በተምሳሌታዊ አገላለፅ) የተዘፈኑ ናቸው፡፡

ኩኩሉ አለ ዶሮ፣

ምን ይሰማ ይሆን ጆሮ፣

ዘንድሮ፡፡

ለካስ ሊነጋ ነው፣

ኩኩሉ ሲል የሰማነው፣

ተስፋ ነው፡፡

ይህ ግጥም፥ የክብር ዘበኛው የሙዚቃ አቀናባሪ ሳህሌ ደጋጎ ሲሆን፥ ግጥሙን የዘፈነችው ብዙነሽ በቀለ ናት፡፡ ብዙነሽ ይህንን ዘፈን የተጫወተችው የ1966ቱ አብዮት ፈንድቶ ወታደራዊው ደርግ ወደ ስልጣን መንበሩ ከመውጣቱ አምስት ወራት ቀደም ብሎ ነው፡፡ በዚህ ጥናት እንደታየው በለውጥ ዋዜማ ከተሰሙ የዘፈን ግጥሞች መካከል አንዱ እንዲህ ዓይነት ተስፋን የሰነቁ ጭብጦች ናቸው፡፡

ዘፈኑ ሁለት ነገሮችን በዋናነት ይነግረናል፤ አንድም ዶሮው ከመጮሁ በፊት ያለውን ጨለማ፤ ያልነጋን ዘመን፡፡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ንጉሳዊ አገዛዝ ስርዓት ያስታውሳል፡፡ በዚህ ውስጥ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥያቄዎች ታምቀዋል፡፡ በጨለማ ውስጥ ተሰልፈው ንጋትን የሚጠብቁ፡፡ አንድም አሮጌው ስርዓት አክትሞ የአዲስ ለውጥ ወጋገን መታየቱን ያበሰራል፡፡ ኩኩሉ አለ ዶሮ በማለት፡፡ በልማድ እንደሚታወቀው ዶሮ ንጋትን አብሳሪ ነው፥ ከጭለማ ወደ ብርሃን አሻጋሪ ነው፡፡ በህንድ አፈ ታሪክ ዶሮ የአማልክት መልክተኛ ተደርጎ ስለሚታሰብ ስጋውን መብላት የተከለከለ ነው፡፡ ጩኸቱም የፀሐይ መውጣትንና የአዲስ ቀን መጀመርን የሚያበስር ነው፡፡ በክርስትና እምነት አስተምሮ ዶሮ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ጴጥሮስን ከስህተቱ የመለሰው የዶሮ ጩኸት መሆኑን ልብ ይሏል(ሄኖክ፣ 2010፣ 149)፡፡ በእስልምናውም አስተምሮ ዶሮ መልአክ አይቶ ይጮሃል ተብሎ ይታመናል፡፡

በብዙነሽ ዘፈን የምናገኘው ንጋት ታዲያ ለወትሮ እንደምናውቀው ዓይነት ያንድ ሌሊት ንጋት አይደለም፤ ያንድ ዘመን ንጋት እንጂ። የዶሮው ጩኸት ልክ እንጴጥሮስ ዘመናትን ከተሻገረ የእምነት የስህተት ጎዳና የሚመልስ ነው። ዘፋኟም፤

ዶሮ ጮሆ ነግቷል ለኛ፣

ልማድ መስሎን እንዳንተኛ።

በማለት ነገሩ የልማድ አለመሆኑን አጽንኦት ትሰጣለች። የደርግ ዋዜማ በብዙ ህዝባዊ ጥያቄዎች የተሞላ ነው። የተማረው ክፍል "መሬት ላራሹ" እያለ ባላባቱን ይሞግታል። ወታደሩ የደሞዝ ጥያቄ አለው። ባለታክሲዎች ነዳጅ ተወዶባቸዋል። ህዝቡ በረሀብ ተጎድቷል። የMarxist ሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም አስተሳሰብ ከነባሩ ንጉሳዊ ስርዓት ጋር ተፋጧል(Henze፣ 2000፣ 283)። ቀጣዩ የክብር ዘበኛው ሳህሌ ደጋጎ የዘፈን ግጥም ይህንኑ እውነት ያጎላል።

ወዛደሩም ነቅነቅ አለ፣

እኩል አድሮ እኩል ዋለ፣

ሲኖር በዱቤ እየለፋ፣

ዛሬ አገኘን በቂ ተስፋ።

የለውጡ ተስፋ ወዛደሩን ከባላባቱ፣ ደሃውን ከባለሀብቱ እኩል የሚያደርግ ነው። በማርክሳዊው የለውጥ እሳቤ፤ የታችኛው መደብ(ወዛደሩ) የላይኛውን መደብ(ባላባቱን፣ ካፒታሊስቱን) ታግሎ ሲጥል አዲስ ስርዓት ይፈጠራል። ይህ ስርዓት አንዱን በዝባዥ፣ አንዱን ተበዝባዥ የማያደርግ፤ ሁሉን እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ኮሚኒስታዊ ስርዓት ነው። "ወዛደሩም ነቅነቅ አለ"፣ የሚሉት ቃላት የሰርቶ አደሩን የትግል እንቅስቃሴ የሚያሳይ ነው። በትግሉ እኩልነትን ያሰፍናል። ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነትን ያስወግዳል። ተስፋው እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች እውን ለማድረግ የሚሻ ነው።

ሁለተኛው፥ በ1966 ዓ.ም ለውጥ ዋዜማ የታየው ጭብጥ የረሃብ ጉዳይ ነው። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ውድቀት ካፋጠኑት ክስተቶች አንዱ በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረው የወሎው ረሀብ እንደመሆኑ፤ በሀገሪቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የራሱን ጫና አሳርፏል። ይህ ረሃብ ለብዙ ኢትዮጵያውያን ምስጢር ሆኖ የቆየ ነው። ጆናታን ዲንቢልቢ(Jonathan Dimbleby) የተባለ የቢቢሲ ጋዜጠኛ ለዓለም እስኪያሳየው ድረስ ጉዳዩ ትኩረት ያገኘም አልነበረም። ደርግ

ወደ ስልጣን ከመውጣቱ ዋዜማ ይህንኑ ክስተት ለህዝብ በቴሌቪዥን እንዲታይ በማድረግ የህዝቡን ትኩረት ለማግኘት ችሏል(ባህሩ፣ 2002፣235)። በአንፃሩ የባላባቱ የተቀማጠለ ህይወት ይበልጥ እንዲኮነን ምክንያት ሆኗል። በዚህ ወቅት ከተሰሙ ዘፈኖች አንዱ የጥላሁን ገሠሠ "ዋይ ዋይ ሲሉ" የሚለው ይገኝበታል። ይህ ዘፈን የረሀቡን አስከፊነት በዝርዝር የሚተርክ ነው።

ተአምር ነው የአምላክ ስራ፣

መቼ ያልቃል ብናወራ፣

አንዱን ጎርፍ አጥለቅልቆት፣

ሌላው ያልቃል በድርቆት።

መስከረም አንድ 1967 ዓ.ም ምሽት፤ ማለትም ንጉሱ ከስልጣን ከመውረዳቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ ደርግ የወሎን ረሃብ በቴሌቪዥን ሲያስቃኝ በእለቱ በተጨማሪ ከቀረቡ ዝግጅቶች መካከል ይህ ጥላሁን የተጫወተው ዘፈን ይገኝበት ነበር። ደርግ በአንድ መልኩ ረሃቡ ያስከተለውን ሰቆቃ እያስቃኘ ወዲህ ንጉሱና ባለስልጣኖቻቸው በሀገሪቱ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ፤ በተቃራኒው የሚኖሩትን የተንደላቀቀ ህይወት በመተረክ በአገዛዙ ላይ የተቀጣጠለውን አብዮት ፍፃሜውን ያፋጠነበት ይመስላል። በዚህ መነሻ ከላይ የቀረቡትን ስንኞች ስናያቸው ቢያንስ ሁለት እውነትን ተሸክመዋል። ከላይ ከላይ ሲታይ ግጥሙ ተፈጥሮን ይሞግታል። በአምላክ ስራ ይገረማል። አንዱ ጋ ዝናብ አብዝቶ ይዘንባል፤ የጎርፍ አደጋ ብዙዎችን ይቀጥፋል። ውሃ የጥፋት ምክንያት ሆኖ አያሌዎችን ይወስዳል። ሌላው ጋ ደግሞ ተቃራኒው ይፈፀማል። የውሃ መጥፋት፣ ድርቅ የሰው ልጆችን ህይወት ይቀጥፋል። እዛ ለጥፋት የተሰለፈው ውሃ እዚህ ነብስ አድን መድሃኒት ሆኖ በጥብቅ ይፈለጋል። ግጥሙ ይህንን ተፈጥሮአዊ እውነት ያነሳል። "አንዱ ጎርፍ አጥለቅልቆት፣ ሌላው ያልቃል በድርቆት"፤ እያለ። ነገሩን ጠለቅ ብለን ስንፈትሸው ግን ግጥሙ ጉዳዩ ከተፈጥሮ ወይም ከአምላኩ ጋር ብቻ ነው ለማለት አያስደፍርም። "አንዱ ጎርፍ አጥለቅልቆት፣ ሌላው ያልቃል በድርቆት" ሲል ሁለት ያልተመጣጠኑ መደቦች ተነፃፅረዋል። የላይኛው መደብና የታችኛው መደብ፣ የሞላለትና የጎደለበት፣ ጭሰኛና ባላባት። ይህ ደግሞ ወደ ዘመኑ አቢይ ጥያቄ የሚወስደን ነው። የኢኮኖሚ አለመመጣጠን። ስርዓቱ አንዱን ባለመሬትና ባለሀብት፤ ሌላውን ጭሰኛና ተመፅዋች ያደረገ

ነው የሚል ነው። ጥያቄው ኢኮኖሚያዊ ፍትህ ነው። አንዱ.ጋ የተረፈው ሌላውም.ጋ ይድረስ ነው።

የግጥሙ ሙግት በሌሎችም ስንኞች ላይ የቀጠለ ነው። ተፈጥሮ ዝናብ ነፍጎ ብዙዎችን ለረሃብ የመዳረጉን ያህል፤ የምድሩም ስርዓት የሰማይን ያህል መራቁን የሚጠቁሙ ስንኞች አሉ።

ምድር ሰማይ ሆነባቸው፣

ሰማይ ጥላ ነፈጋቸው፣

በረሀብ ስቃይ ተጨነቁ፣

ተሰደው አገር ለቀቁ።

የዘፈኑ አጠቃላይ ጭብጥ ይኸው ነው። ሰውና ተፈጥሮ ፊቱን ያዞረበት ህዝብ። ቅጣቱ በረሃብ አለንጋ መገረፍ ነው። ውጤቱም ለሞትና ለስደት መዳረግ ነው የሚል። በዚህ ግጥም ውስጥ "ምድር" እና "ጥላ" የሚሉት ቃላት ፍካሬያዊ ትርጓሜ የያዙ ናቸው። ምድር ሰማይ የሆነባቸው እነማን ናቸው? ለምን? ምድር ሰማይ መሆን ይችላል ወይ? ከተባለ መልሱ አዎን ይችላል ነው። እንዴት? አንድም በርቀቱ፤ አንድም በንፍገቱ። ላብራራ፤ ሁለተኛው ስንኝ ላይ "ሰማይ ጥላ ነፈጋቸው" የሚል ሀሳብ ሰፍሯል። ሰማይ እንደ ዛፍ የሚያጠላው ጥላ የለውም። ነገር ግን ከጥላ በላይ የሚፈለግ ጥላ አለው። ዳመና መያዝና ዝናብ መጣል። ይኸው ነው የሰማይ በረከት። ዝናቡን ቢጥል ይህ ሁሉ ሞትና ስደት ባልመጣ ነበር። ይህን ካላደረገ ግን ንፉግ ይሆናል፤ እንደ ርቀቱም የማይጨበጥ ይሆናል። "ምድር ሰማይ ሆነባቸው" የሚለው የመጀመርያው ስንኝም እዲሁ ምድራዊውን ስርዓት የሚመለከት ነው። ይበልጥ ስንገልጠው የቀዳማዊ ኃይለስላሴን የአገዛዝ ስርዓት የሚመለከት ነው። እንደሰማይ እርቆ በጊዜው ያልደረሰላቸውን የቅርብ ሩቅ ገዢ የሚታዘብ ቋጠሮ ነው። ንፍገቱም የራሱን ምቾት እያደላደለ እንዲህ ዓይነቱን አሰቃቂ ችግር ከሀገሩም ከዓለምም ጆሮ ሸሽጎ ለማቆየት መሞከሩ ነው።

### 3.1.2. የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች

በ1983 ዓ.ም የለውጥ ዋዜማ ወቅት ከተዘፈኑ በርካታ ዘፈኖች ውስጥ በአንድም በሌላ መንገድ የለውጡን መምጣት የነካኩ ዘፈኖች አሉ። ሁሉም አንድ የሚያደርጋቸው ጭብጥ ታዲያ አብዛኞቹ ስለሀገር አንድነት፣ እርስበርስ ስለመተባበርና እርስበርስ መከዳዳት እንደማይገባ

የሚያነሱ መሆናቸው ነው። Henze(2000፣ 308) እንደሚያስረዱት ይህ ወቅት ኢትዮጵያ በጦርነት፣ በርዕዮተ ዓለምና በኢኮኖሚ ውድቀት አጣብቂኝ ውስጥ የገባችበት ነው። በሰሜን የኤርትራ የመገንጠል ጥያቄን ያነገበ ጦር ከህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይና ከሌሎች የኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር በማበር የወታደራዊውን ደርግ አገዛዝ ለማስወገድ እየተንደረደረ ያለበት ጊዜ ነው። በሌላ በኩል ደርግ ለዓመታት ሲመራበት የቆየው ሶሻሊስታዊ ርዕዮተዓለም በዓለም አቀፍ ደረጃ ውድቀትን ያስተናገደበት ወቅት ነበር። በተለይ የዚህ ርዕዮተ ዓለም ዋንኛ አቀንቃኝና ደጋፊ የሆነችው አገር፤ የሶቭየት ህብረት መፈረካከስ የደርጉን መንግስት ያለ ደጋፊ ሜዳ ላይ አስቀርቶታል።

ሌላው ልክ እንደ 1966 ዓ.ም ሁሉ፤ በ1977 ዓ.ም በሀገሪቱ የተከሰተው ዳግማዊ ድርቅ ጉዳይ ነው። በዚህ ድርቅ አያሌዎች ለረሃብ፣ ለስደትና ለሞት ተዳርገዋል። ነገሩን ለማድበስበስ የሞከረው ደርግም ታላቅ ፖለቲካዊ ኪሳራን አስተናግዶበታል። አስረኛውን አብዮታዊ ክብረበዓልና የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ(ኢሠፓ) ምስረታን ሲያከብር ያሳየው የተትረፈረፈ ድግስ ለዚህ ማሳያ ሆኖ ይቀርባል። ከአስር ዓመታት በፊት ንጉሱ በህዝባቸው ላይ ያሳዩትን ቸልተኝነት ደግሞታል በማለት ተተችቷል። ይህ ሁሉ ተደማምሮ ከጦርነት አውድ ያልተለየችው ሀገር በተለይም በደርግ ውድቀት ዋዜማ ኢኮኖሚዋ እጅግ ተዳክሞ ነበር።

በ1983ቱ ለውጥ ዋዜማ በአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ውስጥ ከተነሱ ጭብጦች መካከል ሌላኛው የኤርትራ ጉዳይ ነው። በጊዜው ለኤርትራ ነው የተዘፈነው ተብለው ከተፈከሩ የዋዜማ ዘፈኖች መካከል ይሁኔ በላይ የተጫወተው "ኧረ ተይ ግቢ ግቢ" የሚለው ዘፈን ይገኝበታል። ይህ ዘፈን የወጣው ከለውጡ አስወራት ቀደም ብሎ ነው።

ኧረ ተይ ግቢ ግቢ ግቢ፣

ኧረ ነይ ግቢ ግቢ ግቢ፣

በኔ ሞት ግቢ ግቢ ግቢ።

ውጡና አነጋግሯት አንድ ሁለት ሆናችሁ፣

የቆመችበትን ምክንያት ጠይቃችሁ፣

እሷ ውጭ ቆማ በር ተቀምጣ፣

ማን እህል ሊበላ ማን ውሃ ሊጠጣ?

በዚህ ግጥም ውስጥ ሶስት ጉዳዮች በዋናነት ተነስተዋል፡፡ የመጀመርያው ተማፅኖ ነው፡፡ "ኧረ ተይ ግቢ ግቢ" እያለ በር ላይ ቆማ "አልገባም" ያለችውን ገፀ ባህሪ ይማፀናል፤ ግቢና ከወገኖችሽ ተቀላቀይ ይላታል፡፡ ፍካሬው አንድነት ይሻላል፤ መገንጠል አይበጅም ነው፡፡ ሁለተኛው ጉዳይ የድርድር ሀሳብ ያለው ይመስላል፡፡ ከዋናው ቤት ተነጥላ በር ላይ አኩረፋ የቆመችውን "ግዛት" በደሏን እንጠይቃት፤ ምንድነው ያስከፋት የሚል ጭብጥን ይዟል፡፡ አንድ ሁለት ሆናችሁ ምክንያቷን ጠይቁ በማለት ምናልባትም ለወቅቱ ገዢ የቤት ስራ ይሰጣል፡፡ ፖለቲካዊ መፍትሔን ያመላክታል፡፡

መረር የሚሉት ግን የመጨረሻዎቹ ስንኞች ናቸው፡፡ ሶስተኛው አማራጭ፡፡ ከተማፅኖ ከድርድር ቀጥሎ ባንቺ ዋዛ የለም የሚል ነው፡፡ "እሷ ውጭ ቆማ በር ተቀምጣ፣ ማን እህል ሊበላ ማን ውሃ ሊጠጣ" ይላል፡፡ "ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር!" ከሚለው የጊዜው መፈክር ጋር የተስማማ አገላለፅ ይመስላል፡፡ የአገሪቱ አንድ አካል የሆነችው ኤርትራ ክፍለ ሀገር፤ ከእናት ሀገሯ ተገንጥላ ልትወጣ ስትንደረደር ማን ዝም ይላል ነው ነገሩ፡፡ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት!" የሚሉ ኃይሎችን ድምፅ የያዘ መልክት ነው፡፡

በዚህ ግጥም ላይ ተስፋ መቁረጥ ድምፆችም አሉ፡፡ በተማፅኖ አልመለስ ያለችውን ገፀባህሪ እንዲህ ይላታል፤

አንቺም ሂጂ ሂጂ ወደ ነጫጮቹ፣

አንቺም ሂጂ ሂጂ ወደ ፈረንጆቹ፣

ለኛም እግዜር አለን ለጥቋቁሮቹ፡፡

ለአንዲት ኢትዮጵያ በሚል በሷ ምክንያት የተከፈለውን ዋጋ ግን ይዘረዝራል፤ እንዲህ በማለት፤

አባትሽ ባጥር ላይ የወረወሩኝ፣

እናትሽ በሰፌድ ዐይን አይኔን ያሉኝ፣

ወንድምሽ በሽጉጥ ተኩሶ ሳተኝ፣

አያትሽ በምርኩዝ አንጌ ዡለጡኝ፣

ወደል ውሻ አይደለሁ ሊጥ አልደፋሁኝ፣

እንቺን እንቺን ስል ነው የተገኘሁኝ፡፡

በዚህ ግጥም ላይ ሌላው የተነሳው ነገር በወቅቱ በስፋት ይነሳ የነበረው የብሔር ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ መነሻ ካየነው "ኧረ ግቢ ግቢ" የሚሉት ስንኞች ለኤርትራ ብቻ ሳይሆን ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ላይ ለነበረው የኢህአዴግ ኃይልም የሚሰራ ይመስላል፡፡ ግጥሞቹ የብሔር ብሔረሰቦችን ልዩ መገለጫዎች በመዘርዘር አንዱ ላንዱ ያለውን ጠቀሜታ ለማሳየት ይሞክራሉ፡፡

ኧረ እናንተ ሰዎች ካማራ ውደዱ

ካማራ ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

ጉች ጉች ያለ ጡት ትራስ ካማራችሁ፣

የዶሮ ፍትፍቱን መብላት ካማራችሁ፡፡

ኧረ እናንተ ሰዎች ኦሮሞ ውደዱ

ኦሮሞ ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

ወርቅና ወርቅ ልጅ ማግኘት ካማራችሁ፡፡

ኧረ እናንተ ሰዎች ከትግራ ውደዱ

ከትግራይ ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

የስንዴ አምባሻውን መብላት ካማራችሁ፣

የቴስታውን ነገር ጥንቃቄ አርጋችሁ፡፡

በዚህ ግጥም በተለይ ሶስት ብሔሮች ተነስተዋል፤ አማራ፣ ኦሮሞና ትግሬ፡፡ እነዚህ ሶስት ብሔሮች በአንድም በሌላ በሀገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍ ያለ ታሪክ ያላቸው ናቸው፡፡ ደርግን በመጣል ሂደት ውስጥም እንደዚሁ ግንባር ፈጥረው ታግለዋል፡፡ ይህ ግጥም ወደ ደቡብም ተሻግሮ "ኧረ እናንተ ሰዎች ጉራጌን ውደዱ" በማለት ተመሳሳይ አበርክቶዎችን ይዘረዝራል፡፡ ስለዚህ ግጥሙ በብሄረሰቦች መካከል ያለን ያልተገባ መገፋፋት በመተው መልካም ነገሮች ላይ ማተኮር እንደሚሻል ይጠቁማል፡፡ አንዱ አንዱን ሲወድ የሚያገኘውን በረከትም ያስረዳል፡፡ በሀገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸው እነዚህን

አራት ብሔሮች አንስቶ በረከታቸውን መዘርዘሩ ያለምክንያት አይመስልም። ይልቁንም አንዱ አንዱን ሲወድና ሲያከብር ሀገር ትረጋለች፣ ሀገር ትበለፅጋለች የሚል አንደምታ አለው። የብሔር ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር፣ የእኩልነትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች የጊዜው ፖለቲካ አንዱ ጭብጥ ነው። ከዚህ አንፃር ካየነው ግጥሙ ለለውጥ እየታገሉ ያሉ ኃይሎችን ደግፎ የቆመ ነው። ሌላው በዚህ ግጥም ውስጥ ማሰሪያ የሚመስሉ ስንኞች ናቸው። እነዚህ ስንኞች ይህ ሁሉ ብሔር እርስ በርስ እንዲዋደድና ተከባብሮ እንዲኖር የሚያደርጉ የጋራ ድልድይን የሚገልፁ ናቸው። ድልድዩ ሀገር ነው። በሀገር ውስጥ ብሔርም፣ ማማርም፣ መኩራትም፣ ሁሉም አለና ይለናል።

ከሁሉም ከሁሉም ሀገሬን ውደዱ

ኢትዮጵያን ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

ማማር በሀገር ላይ መሆኑን አውቃችሁ፣

መኩራት በሀገር ላይ መሆኑን አውቃችሁ።

በ1983 ዓ.ም የለውጥ ዋዜማ ሌላው ስለሀገር አንድነትና መተባበር ላይ ያተኮረው ዘፈን፣ አረጋኸኝ ወራሽ፣ ፀጋዬ እሸቱ እና ነዋይ ደበበ በጋራ የዘፈኑት “ሁሉም ቢተባበር” የሚለው ነው። ይህ ዘፈን የጊዜውን እርስ በርስ መጠራጠር፣ የሀገር ክህደት፣ መገዳደልና የመሳሰሉትን ወደ ጎን ትቶ በአንድነት መቆምና መተባበር እንደሚያስፈልግ የሚሰብክ ነው።

ሁሉም ቢንቀሳቀስ ቢጣጣር እንደአቅሙ፣

በስራ ነበረ ሀገርን መጥቀሙ።

ቢሰራ ቢደክም ሁሉም ሰው ቢተጋ፣

አምላክ ችሮን ነበር የተፈጥሮን ጸጋ።

ግጥሙ ሁሉም በአቅሙ ቢሰራ ሀገር የት በደረሰች የሚል ነው። በተፈጥሮ የተቸርነውን ፀጋ በአግባቡ አልተጠቀምንበትም። ትኩረታችንን ከሌሎች ጉዳዮች ላይ ቀንሰን ሁሉም ፊቱን ወደ ስራ ቢያዞር ይሻል ነበር፤ የሚል የቁጭት ድምፅ ነው። ቁጭቱ በጊዜው የነበረውን ሀገራዊ ምስቅልቅል የሚያስቃኝ ይመስላል። በአንድ ወገን በደርጉ ወታደራዊ ኃይል፤ በሌላ ወገን

በለውጥ ፈላጊው ኃይል አጣብቂኝ ውስጥ የገባውን ዜጋ ያስባል። በግርግር የሚያልቀውን ሰውና ንብረትም ያነሳል።

መጠፋፋት ቢቀር በተንኮል በሀሜት፣

ሁሉም ቢደጋገፍ በእውነተኛ ስሜት፣

ሰው በሰው ባይገባ ባያጋጭው ነገር፣

ሁሉም ቀና ቢያስብ ሁሉም ቢተባበር፣

ማን ኧረ ማን ይደርስብን ነበር።

ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክርልን ሌላኛው ዘፈን በዚሁ ሰሞን የተዘፈነው የፀጋዬ እሸቱ "እውነት ትኖራለች" የሚለው ዘፈን ነው። ይህ ዘፈን በተለይም ሳይበድሉ በድላችኋል፣ ሳይዋሹ ዋሽታችኋል፣ ሳይክዱ ክዳችኋል እየተባሉ ያለፍርድ በግፍ ያለቁትን ሁሉ የሚያስታውስ ነው።

ሰው ምላሱ ታስሮ ስጋው ቢቀበርም፣

ደግም ሆነ ክፉ ሀቅ አይሸፈንም።

መሬቱ አይናገር አፍ የለው እንደሰው፣

ደግ አይል ክፉ አይል ባፈሩ ሲያለብሰው፣

ሞት ቢጋርደውም ከመቃብር ጎራ፣

አይቀርም ተዳፍኖ የሰው መልካም ስራ።

ግጥሙ ሁለት ጭብጦችን ይዟል። አንደኛው እውነትን የያዘ ሰው እንዳይናገር ምላሱ ተሸብቦ በግፍ ተቀብሯል ይለናል። ሁለተኛው ሞት መልካሞችን መውሰድ ቢችልም እውነትን ግን ጨርሶ እንደማያጠፋት ይመሰክራል። ግጥሙ ዛሬ ፍርድ ያጎደሉ፣ ዳኝነት በእጃችን ያሉ፣ እውነትን በአምሳላቸው የቀረፁ ሁሉ ነገ ታሪክ ሆነው የተቀበረው እውነት መውጣቱ አይቀርም የሚል መልክት አለው። ምናልባትም የወታደራዊው ኃይል ማክተሙን፥ ሌላ የለውጥ ንጋት ማስገምገሙን እያመካከተ ይሆን? ጊዜው የሙዚቃ ግጥሞች በጥብቅ የሳንሱር ሂደት ውስጥ አልፈው የሚሰሩበት እንደመሆኑ ብዙ ጉዳዮች በግልፅ አይዘፈኑም። ፍካሬው ግን ወደዛ ይመራናል። ይህ ዘፈን የወጣበት ጊዜ አንድም፥ ደርግ በ1981 ዓ.ም. የተሞከረበትን መፈንቅለ

መንግስት ምክንያት በማድረግ አያሌ ወታደራዊ መኮንኖችን ያለ ፍርድ የረሸነበት ማግስት ነው። አንድም፥ በሰሜን ያሉ አማፅያን ኤርትራን ለመገንጠል ሰፊ ዘመቻ እያካሄዱ ያሉበት ወቅት ነው። አንድም፥ የህወሓት ወያኔና ሌሎች ኢትዮጵያን ከደርግ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ወታደራዊ ትንቅንቅ እያካሄዱ ያለበት ጊዜ ነው። በዚህ ሁሉ ፍልሚያ መሃል ፍትህ ሳያገኙ ያለቁ ብዙዎች ናቸው። የእነሱ እውነት ታዲያ ነገን ተስፋ አድርጋለች። እዛ ተቀብራ እዚህ ልትወጣ። አሮጌው ሲቀበር አዲሱ ለውጥ ሲመጣ። ይህ ነው የዘፈኑ ጭብጥ።

የወቅቱን የዘፈን ሳንሱር ከሚያሳዩ ጭብጦች ሌላው በ1982 ዓ.ም. ማብቂያ የተዘፈነው የፀሐይ ዮሐንስ "ዝም ይሻላል" የሚለው ዘፈን ነው። በዘፈኑ እንደተገለጠው በጊዜው ብዙ ሊባሉ የሚችሉ በደሎች ቢኖሩም ከመናገር ዝም ይሻላል በማለት፥ መናገር የሚያመጣውን ጣጣ ይጠቁማል።

እንዲያው ዝምታ ነው ዝም ይሻላል፣

ሁሌ በእንጉርጉሮ በትካዜ ስብሰለሰል፣

ሲያነደው ሲያከስለው በሆዴ ውስጥ ይብሰል፣

ምንስ ሰሚ ላገኝ ዋይ አንጀቴ ሲቃጠል።

በዚህ ግጥም ውስጥ ያለው ዋናው ጭብጥ ተናጋሪው በደሉን፣ ህመሙን ችሎ በዝምታ ጊዜውን ማሳለፉ አይደለም። ዋናው ጉዳይ ሰሚ መጥፋቱ ነው። ንግግር መጥፋቱ ነው። ከመነጋገር፣ ከመደማመጥ ይልቅ ነፍጥ ማንሳት መቅደሙ ነው። ሆኖም ተስፋ አይቆርጥም። ገጣሚው ለውጥ አይቀሬ መሆኑን ይጠቁማል።

የኔ ዓለም እንኳን ሰው ግብዙ ጊዜ ሚለውጠው፣

ሲያገኝ የሚርቀው፣

የኔ ዓለም ጀምበርም ከመሸ መጥለቋን አትተው፣

አትገኝ ከስፍራው።

በነዚህ ስንኞች ገጣሚው ለውጥን ተፈጥሮአዊ ባህሪ ይሰጠዋል። ቀን ሲመሽ ጀምበር እንደምትጠልቀው ሁሉ፥ ፣ ቀን ሲለወጥ፣ ያጣ ሲያገኝ፣ ንጉስ ንግስናውን ሲያጣ፣ ሹመኛ ሲሻር ወዘተርፈ ውድቀት መከተሉ አይቀርም። አዲስ ቀን፥ አዲስ ፀሐይ፣ አዲስ ስርዓት ይከተላል። ለዚህ ነው "እንኳን ሰው ግብዙ" ማለቱ። የሰው ስርዓት፣ የሰው አገዛዝ መውደቁ አይቀርም፤ አዲሱ ለውጥ ዝም ያለውን የፍትህ ጥያቄ፣ የመኖር፣ እራስን በራስ የማስተዳደር፣

ንብረት የማፍራትና የመሳሰለውን ጥያቄ ይመልሳል ወይ የሚለው ጭብጥ የለውጡ የቤት ስራ ነው። ግጥሙ የሚነግረን የለውጡን አይቀሬነት ብቻ ነው።

## 3.2. የለውጥ ጊዜ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ጭብጦች

### 3.2.1. የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ጊዜ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች

በብዙ ጥያቄዎች የተወጠረው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ፍፃሜውን ማግኘቱ እውን ሲሆን፤ በአገዛዙ ተማረው እንደነበር የሚገልፁ ብዙ ዘፈኖች ተሰምተዋል። በዚህ ወቅት ከተሰሙ የዘፈን ጭብጦች መካከል ያለፈው ስርዓት ሰውን ከሰው በዘርና በዝምድና ከፋፍሎ ሲጠቅም ነበር፣ በሙስና ተዘፍቆ ነበር፣ የጥቂቶች የኢኮኖሚ የበላይነት ሰፍኖ ነበር እና የመሳሰሉ የብሶት ግጥሞች ተዘፍነዋል። በግጥም ቅርጻቸው ተራና ግል የሆኑ(ኪናዊ ከፍታ ያሌላው) በርካታ ዘፎኖች ወጥተዋል፡፡ እነዚህኞቹ በአብዛኛው ለለውጥ ኃይሉ ፖለቲካዊ ትርፍ(ajitprop) የተሰሩ ናቸው። ለምሳሌ በዚያው በ1967 ዓ. ም. የተሰሩት የጥላሁን ገሠሠና የወጋየሁ ደግነቱ ዘፈኖች በዚህ ዘርፍ ሊመደቡ ይችላሉ። ሁለቱም ዘፋኞች ያለፈውን ስርዓት የስድብ ያህል ግፉን እየዘረዘሩ ኮንነዋል። ስራዎቹ እንደ ግጥም ከፍ ያለ የአገጣጠም ስልትን የተከተሉ ሳይሆኑ ተራ የሚባሉ ናቸው። ስሜትን በዝርው እንደመግለፅ ያህል ናቸው። ጭብጣቸው ግን ትናንትን መውቀስ ነው። መውቀስ ብቻም ሳይሆን የበቀል ፍርድን የሚሰጥ ነው። ቀጣዮቹ የወጋየሁ ደግነቱ ስንኞች ሁነኛ ምሳሌዎች ናቸው።

*ሀገሪቱን የጎተተ ወደ ኋላ፣*

*በደሀ ላብ የግል ሀብቱን የሚያሟላ፣*

*ሰራተኛን በስልጣኑ የሚያጉላላ፣*

*ምን ይዋጠው ከህዝብ ላይ ጉቦ የበላ፣*

*ይቀጣታል አይቀርለት*

*ይለቀማል ከየቤቱ፣ ከየወንዙ ከያለበት።*

*ለውጥ መጣ ያ ጉደኛ ፈረደበት፣*

*ለሰራው ግፍ ተለቃቅሞ ወደ እስር ቤት።*

በጥላሁን ገሠሠ ነበረ በተሰኘው ዘፈን ላይም እንደዚሁ ያለፈው ስርኣት በደሎች አንድ ባንድ ተዘርዝረው ተኮንነዋል፡፡ የተዘረዘሩት በደሎች ከፍ ባለ ግነት የተፃፉ ናቸው፡፡

ዝሙትና ስካር ይደገስ ነበረ፣

በፍርድ ማንከራተት ይፈቀድ ነበረ፣

ጉቦና አድሎ በአዋጅ ሲወጣ፣

ትንሽ ሲቀረው ነው ይሄ ለውጥ የመጣ፡፡

የለውጡ ጊዜ ብዙ መሰል ዘፈኖች ተሰምተውበታል፡፡ የአብዘኞቹ ጭብጥ ታዲያ ያለፈውን ስርዓት እንዲህ ማብጠልጠልና በበቀል ለመቅጣት ማሰብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የከተማ እንዳሻው “ብድሩን ቀመሰው” የተሰኘው ስራም እንደዚሁ ሌላኛው ምሳሌ ነው፡፡ ዘፈኑ በ1967 ዓ.ም በዚያው በለውጡ ሰሞን የወጣ ነው፡፡

ስጋዬን ጨርሶ አጥንቴን የላሰው፣

በሰፈረው ቁና ብድሩን ቀመሰው፡፡

በዚህ ጥናት ዘዴ ላይ እንደተገለጸው፤ እንንዚህ ዓይነቶቹ ዘፈኖች የዚህ ጥናት ትኩረት ስላልሆኑ፤ በግጥም ከፍታቸው የተሻሉና ለፍካሬ ክፍት ወደሆኑ ዘፈኖች እንሻገር፡፡ ከእንደዚህ ዓይነት ዘፈኖች አንዱ በ1967 ዓ.ም. የተሰራው የአያሌው መስፍን “ጉንፋን” የተሰኘው ዘፈን ነው፡፡ ይህ ዘፈን ለውጡ በመጣ ወራት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተሰራ ነው፡፡

የጥንቱ ህመሜ ያምናው እንፍሎይንዛ፣

ሊለቀኝ ነው መሰል ዘንድሮ እንደዋዛ፡፡

አሰልስሎ አንጀቴን እስኪሰበር ቅስሜ፣

ዘንድሮ ለቀቀኝ ያ ጉንፋን ህመሜ፡፡

አያሌው በዚህ ግጥም ያለፈውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዘመን “ጉንፋን” በሚል ተለዋጭ ዘይቤ ገልፆታል፡፡ በርግጥ ጉንፋን የአጭር ጊዜ ህመም ነው፡፡ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረጅም የአጋዘ ዘመን አንፃር የተገባ ንፅፅር አይመስልም፡፡ ሆኖም ስርዓቱ ከበሽታ ጋር መነፃፀሩ በአንድም በሌላ የአገዛዙን አስከፊነት የሚያሳይ ነው፡፡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ስርዓት በጉንፋን የመመሰል ነገር በአያሌው መስፍን ዘፈን ላይ ብቻ የታየ አይደለም፡፡ በዚሁ ሰሞን የወጣው የፍስሃ ኃይሌ “መስከረም ነፃነት” በሚለው ዘፈን ላይም እንዲሁ የፊውዳሉ ዘመን ከጉንፋን ጋር ተነፃፅሯል፡፡

ተውሳኩ ተባዩ ጉንፋን ቅራቅንቦ፣

ከምድረ ኢትዮጵያ እንዲወድም ተሰቦ።

ይህ አስከፊ ጉንፋን የስርዓቱ አድሎአዊ አገዛዝ ነው፣ የስርዓቱ ሙስና ነው፣ የሰርዓቱ ኢዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ነው። ይኸው ነው በአያሌው ግጥም "ቅስም ሰባሪ ጉንፋን"፣ በፍስሃ ደግሞ "ጉንፋን ቅራቅንቦ" ሲባል የተገለፀው። እንግዲህ ግጥሙ እንደሚነግረን ይህ አስከፊ ጉንፋን ፈውስ የሚያገኘው ታዲያ በለውጡ ኃይል ነው። በጊዜአዊው ወታደራዊ የደርግ ስርዓት። የአያሌው ግጥም ዝቅ ሲል ዝርዝር ጉዳዮችን ያነሳል።

ህዝቡም ወታደሩ ባያንጎራጉር፣

ህዝቡም ወታደሩ ባይተባበር፣

ጉንፋን ስንቱን ነበር ሲቀብር የሚኖር።

መጥፋት አትጠፋም ትኖራለህ ለስም፣

ጉንፋን ግን ደህና ሁን ዳግም አትመለስም።

በዚህ ግጥም ውስጥ ሁለት ጭብጦች በዋናነት ተነስተዋል። የመጀመርያው የለውጡ ተሳታፊዎች ናቸው። በለውጡ እንቅስቃሴ ውስጥ ወታደሩ ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበረው። ተማሪው ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበረው። መምህሩ ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበረው። ሌላውም እንደሁኔታው አብዮቱን ተቀላቅሎ የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል። ለዚህ ነው ግጥሙ የወታደሩንና የህዝቡን ትብብር እንደወሳኝ ኃይል የሚያነሳው። ሁለተኛው እውነት "ጉንፋን" በሚል የተገለፀው ስርዓት ላይመለስ መሸኘቱ ነው። ስርዓቱ ሲሸኝ የሰው ለውጥ ብቻ አይደለም። አገዛዙ የተሸከማቸው ብልሹ አሰራሮችም አብረው ተሸኝተዋል የሚል መልክትን ያዘለም ጭምር ነው። በዚህ ግጥም ውስጥ ምንም እንኳ ስርዓቱ ላይመለስ ሄዷል ቢባልም፤ "መጥፋት አትጠፋም ትኖራለህ ለስም" የሚል ስንኝ ተካቶበታል። ያለምክንያት የገባ አይደለም። እያለን ያለው አስተሳሰቡን ነው። ንጉሳዊው ስርዓት ቢወገድም የስርዓቱ ደጋፊ ግን ጨርሶ አይጠፋም ነው። ለዚህም ይመስላል ገጣሚው በግጥሙ መጨረሻ ስጋቱን በቀጣዮቹ ስንኞች በግልጽ ማስቀመጡ።

አይመልስህ እንጅ ከተመለስክማ፣

ይሄን ተናግሬ ምን ተረፍኩ እኔማ።

#### 3.2.1.1. የድጋፍ ዘፈኖች

ደርግ አብዮቱን እየመራ መንበረ ስልጣኑን ሲረከብ በህዝቡ ዘንድ ሰፊ ድጋፍ ነበረው። የትናንቱ በደል ተሽሮ አዲስ የተሻለ አገዛዝ ይመጣል በሚል እምነት ከተማሪ እስከ መምህር ግፋ በለው እያለ አብዮቱን ደግፏል። የዚህ ምክንያቱ አንድም፥ የወታደሩም፣ የህዝቡም የጋራ ጠላት የሆነው የፊውዳሉ ስርዓት በመውደቁ፣ አንድም፥ ወታደሩ ብልሹውን ስርዓት አስወግዶ ሲያበቃ ለህዝባዊ አገዛዝ ለቆ ወደመጣበት ይመለሳል በሚል ተስፋ ሊሆን ይችላል። በዚህ ሰሞን ከተሰሙ ድጋፍ ሰጪ ዘፈኖች መካከል አንዱ ችለን ማለፍ ጥሩ በሚል ርዕስ በ1967 ዓ.ም. መጀመርያ የተዘፈነው የመሐሙድ አህመድ ዘፈን አንዱ ነው።

ድፍርሱን አጥርተን ልንጠጣ፣

ጨለማን አልፈን ልንወጣ፣

ልንበላ በፍቅር ገበታ፣

ጽዋችንን ሞልተን በእርጋታ፣

ውይይት ጀመርን በፈገግታ።

ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው፥ ጊዜው እንደ ደፈረሰ ውሃ ነው። ንፁህና ድፍርሱ የተቀላቀለበት፣ ሰንዴና እንክርዳዱ ያልተለየበት፣ ጨለማና ንጋት የተቀላቀሉበት፤ ሆኖም እንዲህ ያለውን ጊዜ ለማለፍ የሚያስችል አንድ ምቹ መደላድል ግን ተፈጥሯል። ሁሉንም ችግር ፈትቶ ወደፊት ለማራመድ የሚያስችል የውይይት መድረክ። መድረኩ በፍቅር የተሞላና ተስፋ ሰጪ ሆኖ ቀርቧል። አንድ እውነት ግን በግጥሙ ውስጥ ለፍካሬ ቀርቧል። ፍካሬው ለውጡ ገና የውይይት ጅማሮ ምቹ ሁኔታ እንጂ ፍፃሜ አለመሆኑን የሚገልጽ ነው። የውይይቱ ውጤት ለህዝቡ የተሻለውን መሪ የሚመርጥ ሊሆን ይችላል። አንድም ህዝባዊውን መሪ የሚወልድ፤ አንድም ደርጉን በወንበሩ የሚያጸና ሊሆን ይችላል። ዋናው ጥሩ ነገር ጉልበት ተትቶ ለውይይት በር መከፈቱ ነው። ይህንኑ ጭብጥ ይበልጥ የሚያጠናክሩት ደግሞ ቀጣዮቹ ስንኞች ናቸው።

በአንድነት ጉዞ ጀምረናል፣

የብርሃን ብልጭታ ይዘናል፣

ማንነታችንን አውቀናል።

ድምፃዊው ከተማ እንዳሻውም እንደዚሁ ድጋፉን የገለፀበትን ስንኞች በዘፈኑ ውስጥ አካቷል።

የእኩልነት መብቴን አገኘሁ በይፋ፣

ኢትዮጵያ ትቅደም የኔ ህይወት ተስፋ።

እንዲህ ዓይነት የድጋፍ ዘፈኖች በሌሎችም ድምፃውያን ስራዎች ውስጥ ተስተውለዋል። የሁሉም የድጋፍ መነሻ ታዲያ አንድ ማሰሪያ ያለው ይመስላል። ይህ የድጋፍ መነሻ መሰረቱ ተስፋ ነው። ተስፋው ህዝባዊ አብዮቱን አቀጣጥሎ ወደ ስልጣን የወጣው ወታደራዊ ኃይል ሽግግሩን በፍጥነት ፈፅሞ ስልጣኑን ለህዝባዊ አገዛዝ አስረክቦ ወደመጣበት ይመለሳል የሚል ነው። ለዚህ ነው ቀጣዩ የ1967 ዓ.ም. የንጉሴ ወልደማርያም ዘፈን ከደርጉ በኋላ የሚመጣው ህዝባዊ መንግስት እንዴት ያለ ይሆን በማለት በግልጽ መጠየቁ።

ጅምሩን ሲጨርስ የጦር ኃይላችን፣

ተምሮ ራሱን ሲያውቅ መላው ህዝባችን፣

እነማን ይሆኑ መሪዎቻችን።

ግጥሙ እንደ ግጥም ከደርጉ በተቃራኒ ለቆሙ ኃይሎች ፖለቲካዊ ትርፍ በግልጽ ቋንቋ የተሰራ በመሆኑ ለፍካሬ የሚያበቃ ኪናዊ ክፍታ የለውም። ጭብጡ ግን የጊዜውን ፖለቲካዊ ፍትጊያ የሚያሳይ ነው። አንድም የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜአዊ ወታደራዊ መንግስት እድሜ አጭር መሆኑን ያሳያል። አንድም የደርጉ ኃይል ጅምሩን ጨርሶ ለህዝባዊ መሪ ያስረክባል የሚል ተስፋን ይዟል።

ደርግ ወደ ስልጣን እንደወጣ በአጭር ጊዜ ውስጥ መልስ ከሰጠባቸው ህዝባዊ ጥያቄዎች መካከል አንዱ የመሬት ላራሹ ጥያቄ ነው። የመሬት ላራሹ ጥያቄ በጊዜው ጎልተው ከሚሰሙ የመብት ጥያቄዎች ውስጥ ዋንኛው ነው። የፊውዳሉ ስርዓት መሬቱን ሁሉ ለባላባቶች ሸንሽኖ ስለሰጠ ጭሰኛው ገበሬ ከልፋት ውጭ በገዛ አገሩ የበይ ተመልካች ሆኗል የሚል ነው ጥያቄው። ጥያቄውን ተማሪዎች ቀዳሚ መፈክራቸው አድርገው ታግለውበታል፥ ህዝቦች ደግፈውታል። ይህ የዘመናት ጥያቄ በደርጉ ኃይል ምላሽ ማግኘቱና ገበሬው የገዛ መሬቱ ጭሰኛ ሆኖ የሚቀጥልበት ስርዓት ማክተሙ ሲታወጅ ከተሰሙ ዘፈኖች መካከል የጥላሁን ገሠሠ “ሀገሬ ኢትዮጵያ” የተሰኘው ዘፈን አንዱ ነው። ዘፈኑ በ1967 ዓ.ም የመሬት አዋጅ በታወጀ ማግስት የወጣ ነው።

እንባዬ ደረቀ ምኞቴ ተሳካ፣

አንድነትም መሀል ውጤት አለ ለካ።

ድል አገኘሁ ዛሬ መሰንበት ጥሩ ነው፣

ከእንግዲህ ጭሰኛ የሚለኝ ሰው ማነው?

ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው ጭሰኝነት ከዚህ ዘፈን በኋላ ተሰናብቷል፡፡ ገበሬው የመሬት ባለቤት ሆኗል፡፡ ስለዚህ በበላባቶች በደል ሲያለቅስ፣ ሲራብ፣ ሲሰደድ የነበረ ሁሉ በደሉ ፍትህ አግኝቷል፡፡ የመሬት ባለቤትነት ምኞቱም ተሳክቷል፡፡ ግጥሙ የዚህ ውጤት መሰረቱ አንድ ሆኖ መታገል መሆኑንም እንዲሁ ያስታውሳል፡፡ ይህንን አድራጊው፥ ለዘመናት የቆየውን የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ የመለሰው ደግሞ ደርግ ሆኖ ተመስግኗል፡፡ "ኢትዮጵያ እንድትቀድም" የምትለዋ በዘፈቀደ የገባች ሳትሆን፤ "ኢትዮጵያ ትቅደም!" በሚል መፈክር የተነሳውን የደርጉን አገዛዝ ለማሞገስ የገባች ሐረግ መሆኗ ግልጽ ነው፡፡

ስለዚህ አንድ ላይ በህብረት ተስማምተን፣

ኢትዮጵያ እንድትቀድም መስራት ነው ያለብን፡፡

የህብረታችን እሸት ተንዘርኋል ዛላው፣

ጠንክረን መስራት ነው ማንም እንዳይበላው፡፡

#### 3.2.1.2. እምነት ማጣትና ጥርጣሬ

"የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜአዊ ወታደራዊ መንግስት" በሚል ስያሜ የተቋቋመው ደርግ የተነሳበትን ዓላማ ስቷል የሚሉ ድምፆች መሰማት የጀመሩት ገና ከጅምሩ ነው፡፡ ያለ ምንም ደም በሚል መፈክር የተጀመረው ለውጥ የታላላቅ ባለስልጣናትን ደም በማፍሰስ ተሻረ፡፡ በርካታ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች ገና በእንጭጩ መዳፈን ጀመሩ፡፡ ከተማሪ እስከ ምሁር፣ ከገበሬ እስከ ወዝአደር የተረባረበበት አብዮት በዚህ መልክ የተጣለበትን ተስፋ ማጨለም ጀመረ፡፡ እነዚህንና መሰል እንቅስቃሴዎችን የታዘቡ ዘፋኞች ታዲያ ሙገሳውን ባስደመጡ በወራት ልዩነት ውስጥ ቅሬታቸውን ማንጎራጎር ጀምረዋል፡፡ ትናንት ደርጉን እሰይ ብለው አመስግነው ወዲያው ቅሬታቸውን ካሰሙ ዘፋኞች መካከል አንዱ አያሌው መስፍን ነው፡፡ ድምፃዊ አያሌው መስፍን በ1967 ዓ.ም. ራሱ ፅፎ በዘፈነው ግጥሙ የደርግ መንግስት አካሄድ ገና ከወዲሁ እንዳልጣመው የሚያሳዩ ጭብጦችን በዘፈኑ አካቷል፡፡

እፍ እፍ ያሉት ፍቅር ጭቅጭቅ አያጣም፣

ቸኮልሽብኝና ጠረጠርኩሽ በጣም፡፡

የአያሌወው ጥርጣሬ ከደርግ ውሳኔዎች ፍጥነት የሚመነጭ ይመስላል። በርካታ አዋጆች በፍጥነት ይሰማሉ። ሰዎች ያለፍርድ ይሞታሉ። ህዝብ ያልመከረባቸው ውሳኔዎች ይተላለፋሉ። እነዚህና መሰል እንቅስቃሴዎች ገጣሚውን አሳስበውታል። ይህ ኃይል እፍ እፍ ማለቱ ምን ቢወጥን ነው አስብለውታል። በዚህ ምክንያት ከዛሬው በላይ ነገውን የፈራ ይመስላል።

*መጀመሪያ ጣፋጭ ቆይተሽ መራራ፣*

*እንዳይሆን ፍቅራችን በጣም ልቤ ፈራ።*

የዘፈኑ ጭብጥ በአጭሩ በነዚህ ሁለት ስንኞች ውስጥ ተጠቃሏል። ሁለት ነገር፥ አንድም የደርጉን አመጣጥ ያስታውሳል። ወታደራዊው ኃይል በህዝብ ድጋፍ ስልጣኑን ከፊውዳላዊው ስርዓት ሲረከብ፥ ቢያንስ ከቀደመው የተሻለ ስርዓትን ያሰፍናል የሚል ተስፋ ተጥሎበታል። ቀዳሚ እንቅስቃሴዎቹም ይህንኑ ተስፋ የሚያረጋግጡ በመሆናቸው ብዙዎች ደግፈውታል፥ ዋጋም ከፍለውለታል። አንድም የነገውን መድረሻ ከአካሄዱ ይገምታል። ግምቱ ተራ ግምት አይደለም። ከስርዓቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ነው። መጀመርያ ለቀቅ ተደርገው የነበሩ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ቀስበቀስ እየተሸረሸሩ መምጣታቸው፣ ከሁሉ በላይ ጊዜአዊ መንግስት ተብሎ ተቋቁሞ "ጊዜአዊነቱ" አብቅቶ መቼ ነው ህዝባዊ መንግስት የሚመሰረተው የሚሉ ጥያቄዎች የግምቱ መሰረቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

ደርግ ስልጣን በያዘ በወራት እድሜ ውስጥ የደርጉን ከፍተኛ አመራር ጀነራል አማን አንዶምን ጨምሮ ስልሳ የሚሆኑ ከፍተኛ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ አገዛዝ ባለስልጣናትን በመረሸን፤ ቃል የገባለትን ደም አልባ ሽግግር ሻረ። ባህሩ ዘውዴ(1991፣ 238)፤ ይህ ክስተት የሀገሩንም ሆነ ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ በእጅጉ ያስደነገጠ ነበር በማለት ይገልጡታል። በዚህ ወቅት ተዘፍነው የአገዛዙን አካሄድ የሚኮንኑ ጭብጦች ከተገኙባቸው የዘፈን ግጥሞች በተስፋዬ ለማ የተደረሰው "ዘንድሮ"[8] የተሰኘው ጥላሁን ገሠሠ የተጫወተው ዘፈን ይገኝበታል። ግጥም ገና ከጅምሩ "እህህ" በማለት ይጀምራል። እህህ ብሶት ነው። ህመም ነው። ገጣሚው እህህ ያሰኘውን ነገር ዝቅ ሲል እየዘረዘረ ይገልፃቸዋል።

ዘንድሮ ዘንድሮ ዘንድሮ፣

የስንቱ ተወርቶ የስንቱ ተነግሮ።

ዘንድሮ።

---

[8] በዚህ ዘፈን ምክንያት ጥላሁን ገሠሠ እና የግጥሙ ደራሲ ተስፋዬ ለማ ለእስር ተዳርገው ነበር(ዘከሪያ፣ 2007)።

ውሎ በማደሩ ተዋሃደንና፣

መጥፎ ከደህና ጋር ተማታብንና፣

ብዙ ዓመቶች አልፈው ዛሬ ነቃንና፣

ያስቀን ጀመረ ግራ ገባንና።

ከግጥሙ ሁለት ጭብጦችን መገንዘብ ይቻላል። አንድም የአብዮቱን ህዝባዊ ቅቡልነት ያስረዳል። እንዴት ቢሉ፥ ገጣሚዊ "ብዙ ዓመቶች አልፈው ዛሬ ነቃንና" በሚለው ስንኝ ውስጥ ዋናውን ጭብጥ ያነሳልናል። "ብዙ ዓመቶች አልፈው" ሲል አገሪቱ በንጉሱ አገዛዝ ያሳለፈችውን ዓመታት ያስገነዝባል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ብዙ እምቢታዎች አልተሰሙም። ላደባባይ የበቁ ተቃውሞዎች አልታዩም። በንጉሱ አገዛዝ ላይ ፖለቲካዊ ተቃውሞዎች እየበረቱ የመጡት ከ1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላ ነው። ለዚህ ይመስላ በዚሁ ስንኝ ውስጥ "ዛሬ ነቃንና" የሚል ሐረግ መካተቱ። ዛሬ ነቃን ሲል ወደ ኋላ እንደዋዛ ያለፉትን በርካታ ዓመታት በመታዘብ ነው። በተቃራኒው የንጉሱ የመጨረሻዎቹ ዓመታት ከተማሪ እስከ ገበሬ አያሌ ተቃውሞዎች የተነሱባቸው ዓመታት ናቸው። የኢኮኖሚ ጥያቄ፣ የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ፣ የርዕዮተ ዓለም አስተሳሰብ ጥያቄ፣ ሌሎችም ብዙ ጥያቄዎች ተነስተዋል። እነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ናቸው "ንቃት" ተብለው የተጠቃለሉት። ንቃቱ፥ አንድም በትምህርት የተገኘ ነው። የተማሪዎቹን እንቅስቃሴ ልብ ይሏል። አንድም፥ ዓለማቀፋዊውን ሁኔታ ተከትሎ የመጣ ነው። በተለይ የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም በመላው ዓለም እየተጥለቀለቀ መምጣት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከቱ የሚቀር አይደለም።

ሁለተኛው ጭብጥ የለውጡ ሂደት ግራ አጋቢ ውሳኔዎችን የሚመለከት ነው። ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው፤ ጥያቄው የለውጡ ተገቢነት ላይ አይደለም። ጥያቄው የ"ነቃ" የተባለው ማህበረሰብ የፈጠረው አብዮታዊ ለውጥ ሂደት ነው። አብዮቱ ከጅምሩ በወጉ ይመልሳቸዋል የተባሉትን ጥያቄዎች ወደጎን ትቶ ወደ ወታደራዊ አባገነን ስርዓት መንደርደሩ፤ ለለውጥ ዋጋ የከፈለውን ማህበረሰብ ግራ በተጋባ መስመር ላይ እንዲቆም አስገድዶታል። ከዚህ በመነሳት 'ያለፈውን ስርዓት ስንቃወም ጭራሽ የባሰው መጣ' የሚል ጭብጥ ያላቸው ቀጣዮቹ ስላቃዊ ስንኞች በዘፈኑ ውስጥ ተካተዋል።

በዚያኛው ተገርመን ጥቂት ሳንቆይ፣

የዚህኛው መባስ አያስቅም ወይ?

ሌላው፥ ደርግ ከዛሬ ነግ ህዝባዊ መንግስት ይቋቋማል በሚል ተስፋ የራሱን ወንበር ሲያደላድል፤ ይሄ ነገር ወዴት ነው? የሚሉ ጥርጣሬዎች እዛም እዚህም መሰማት መጀመራቸው ነው። በዚህ ጭብጥ ሊታዩ ከሚችሉ ዘፈኖች መካከል ሌላኛው የጥላሁን ገሠሠ "አንድ ቀን" የተሰኘው ዘፈን ነው። ዘፈኑ በዛው በ1967 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ የተሰራ ሲሆን ግጥሙ የተስፋዬ ለማ ነው። ይህ ዘፈን እንዲሁ ግጥሙን ሰምቶ ወይም አንብቦ የሚረዱት አይደለም። ጭብጡን በወጉ ለማግኘት የዘመኑን መንፈስ በወጉ መረዳትን ይጠይቃል። ግጥሙ እንዲህ ይነበባል።

አንድ ቀን እያልኩኝ አንድ ቀን አለፈ፣

ሌላ አንድ ቀን ስል እሱም ቶሎ አለፈ፣

የኔ አንድ ቀን አያልፍ እድሜዬ ከነፈ።

አንዱ ሁለት ሆኖ ሳምንቱም አለፈ፣

ሳምንት ተደምሮ ወደ ወር ከነፈ፣

ይሄ ሁሉ ሲሆን እላለሁ አንድ ቀን፣

አንዱ ቀን ቀን ወልዶ ተለወጠ ዘመን።

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፥ ግጥሙ የተመሳሳይ ሁነቶች መደጋገምን ያሳያል። ለውጥ ያልታየባቸው አንድ ዓይነት ቀናት። ዛሬ ከትናንት ያልተለየበት አሰልቺ ድግግሞሽ። ቀናት ቀናትን እየተኩ ይሄዳሉ። ሳምንታት ያልፋሉ። ወራት ይቆጠራሉ። ለውጥ ግን የለም። ወታደራዊው ደርግ ስልጣኑን ከተረከበበት ዕለት ጀምሮ አንድ ትልቅ የቤት ስራ አለበት። ይኸውም ህዝባዊ መንግስት ማቋቋምና ወደመጣበት መመለስ ነው። ጥያቄው በብዙ የማህበረሰብ ክፍሎች በተደጋጋሚ የሚነሳ ነው። ይሁንና በደርጉ በኩል ተደጋጋሚ ተስፋ ከመስጠት የዘለለ በተጨባጭ ስልጣኑን ለህዝባዊ መንግስት የማስረከብ አዝማሚያ አላሳየም። ከቃል የዘለለ በተግባር የወሰደው እርምጃም የለም። በዚህ የዘፈን ግጥም ውስጥ የምናገኘው ጭብጥ ይህንኑ ጉዳይ የሚያስረዳ ነው። ከዛሬ ነገ ህዝባዊ መንግስት ይቋቋማል በሚል ተስፋ እንደዋዛ የባከኑ ጊዜያት። ቀናት አልፈው፣ ሳምንታት ተቆጥረው፣ ወራት ተደምረው፣ ብሎም ዘመን ተለውጦ ምንም የታየ አዲስ ነገር የለም። ዛሬም እንደትናንቱ አሰልቺ ተስፋ ብቻ።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ ደርግ ስልጣን ሲይዝ ይሻሻላሉ ተብለው ተስፋ የተጣለባቸው የዲሞክራሲ፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥያቄዎችም እንዲሁ፤ የረባ ለውጥ አለማሳየታቸውና ተስፋ ብቻ እየሆኑ መምጣታቸው የአሰልቺው ድግግሞሽ መነሻ ናቸው።

በዚሁ በጥላሁን ገሠሠ የ1967 ዓ.ም. የዘፈን ሸክላ ውስጥ የተካተተውና ፖለቲካዊ ትርጉም የተሰጠው ሌላው ዘፈን "ጥሩ ወርቅ" የተሰኘው ስራ ነው:: ዘፈኑ ብዙውን ጊዜ "አልማዝ" በሚል ርዕስ ቢታወቅም በዘፈኑ ሸክላ ላይ የተሰጠው ትክክለኛ ስያሜ ግን "ጥሩ ወርቅ" የሚል ነው:: የዚህም ግጥም ደራሲ ተስፋዬ ለማ ነው:: ይህ ዘፈን የወቅቱን ሶስት የደርግ ሊቀመናብርት የተመለከተ ነው በሚል ጥያቄ አስነስቷል:: ሶስቱ ሊቀመናብርት ጀነራል ተፈሪ በንቲ፣ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም(በኋላ ኮሎኔል) እና ሻለቃ አጥናፉ አባተ ናቸው:: ሊቀ መንበር፣ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ መንበርና ምክትል ሊቀ መንበር ሆነው የደርጉን ስርዓት ይመራሉ(ዘከሪያ፣ 2007፣ 244):: ሶስቱን ሊቀመናብርት ይመለከታል የተባሉት ስንኞች እነዚህ ናቸው::

አልማዝን አይቼ አልማዝን ሳያት፣

ሶስተኛዋ አልማዝ ብትመጣ ድንገት፣

ሁለቱን አልማዞች ስላስረሳችኝ፣

ምርጫዬ በምርጫ ተበላሸብኝ::

ከግጥሙ በመነሳት በርግጥም ሶስቱ አልማዞች፤ ሶስቱን ሊቀ መናብርት ለማነጻጸር ሆን ተብሎ የተገጠመ ነው ብሎ መገመት ይቻላል:: የግጥሙ ደራሲና ዘፋኙ በወቅቱ የተጠየቁበት ነው:: ጉዳዩ ግን ጥያቄ ማስነሳቱ ወይም ወይም ፖለቲካዊ ትርጉም መሰጠቱ አይመስለኝም:: በዚህ ዘፈን ላይ የተጻፉ ሌሎች ጥናቶች(ለምሳሌ ንጉስ፣ 2018፣ 131) ፖለቲካዊ ጥያቄ የተነሳው ሶስቱን መሪዎች ለምን ተነጻጸሩ በሚል ነው የሚል ትንታኔ ይሰጣሉ:: ይሁንና ግጥሙ ከንጽጽሩ በሻገር የያዘው ሌላ ጭብጥ አለ:: እንደውም ዋናው ጭብጥ ነው:: ምክንያቱም ገጣሚው ሶስቱን አልማዞች አነጻጽሮና ለምርጫ መቸገሩን ገልፆ አያበቃም:: ከግራ መጋባቱ መልስ የሱን ምርጫ ያሳውቀናል:: ምርጫው ከሶስቱ አልማዞች ውጪ ነው:: ከሶስቱ ሊቀ መናብርት ውጪ ልንለው እንችላለን:: ሶስተኛዋ ምርጫ ጥሩ ወርቅ ናት::

የሶስስት አልማዝ ምርጫ ስላስጨነቀኝ፣

ጥሩወርቅ ተሽላ ስለታየችኝ፣

ሄድኩኝ ከጥሩወርቅ አልማዞቹን ትቼ፣

አላዋጣም ቢለኝ ነገሩን ገምቼ::

በሶስት አልማዞች ምርጫ የተቸገረው ሰው ፊቱን ወደ "ጥሩወርቅ" ማዞሩ ያለምክንያት አይመስልም:: በቅድሚያ ለምርጫ መቸገሩ ለምን ሲባል፥ አንድም በሶስቱ አልማዞች መካከል

እንደስማቸው የግብር ልዩነት ማጣቱ ነው፡፡ አንድም ሶስቱ አልማዞች በተመሳሳይ ደረጃ ላይ መቀመጣቸው ነው፡፡ ያውም በአልማዝ ዋጋ፡፡ በተለዋጭ ዘይቤ የቀረበው የአልማዝ ዋጋ በስልጣናቸው ክብደት የሚመነዘር ነው፡፡ ሶስቱም ሊቀመንበሮች ናቸው፡፡ ሶስቱም ወታደሮች ናቸው፡፡ የአልማዝ ዋጋ መወደድ ገዢን እንደሚያርቀው ሁሉ፤ ስልጣኑ ከፍ ያለም እንዲሁ በቀላሉ አይገኝም፡፡ በውትድርና ላይ ስልጣንን የደረበ ለተገዢ የሩቅ ሩቅ ነው፡፡ ስለዚህ፥ ገጣሚው ምርጫውን ወደ ጥሩ ወርቅ የማዞሩ ዋናው ምክንያት፥ ከአልማዝ ዝቅ ያለውን ወርቅን መምረጡ ነው፡፡ ዝቅታው በስልጣን፣ ወደህዝብ በመቅረብ የሚገለጽ ነው፡፡ ከሶስቱ አልማዞች የተለየው ወርቅ እንደነሱ በውትድርና ላይ ስልጣን ያልደረበው ሲቪል ገዢ ነው፡፡ በወርቅ ተለዋጭ ዘይቤ የቀረበው ሲቪል ገዢ ወርቅ ብቻም አይደለም-ጥሩ ወርቅ እንጂ፡፡ ገጣሚው ስሙን ከግብሩ ጋር ማጣመሩ ያለምክንያት አይደለም፡፡ ይልቁንም ከሁሉም ጥሩውን ህዝባዊ ገዢ መምረጡን ያሳውቃል፡፡

በ1967 ዓ.ም በጌታቸው ደባልቄ የተፃፈው "ሎሚ ተራ ተራ" የተሰኘው የጠለሳ ከበደ ዘፈንም እንዲሁ የጊዜውን አለመረጋጋትና በየሰበቡ ያለፍርድ ሞት መብዛትን የሚያሳይ ነው፡፡ በየምክንያቱ የሚታሰሩ መብዛታቸውንም ግጥሙ ይጠቁማል፡፡ ስደትና አመጽም እንዲሁ በዘመኑ እያቆጠቆጡ መምጣታቸውን ዘፈኑ ያሳያል፡፡

አባባም ተግዞ ወህኒ ገብቷል አሉ፣

ጋሽዬም ጤና አጥቶ ካገር ወጥቷል አሉ፣

አብዬም ሸፍቷል አምጿል ይላሉ፣

ሎሚ ተራ ተራ ሎሚ ተራ ተራ፣

የማምዬን ነገር ጎረቤቱ አደራ፡፡

## 3.2.2. የ1983 ዓ.ም የለውጥ ጊዜ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች

### 3.2.2.1. የኤርትራ ጉዳይ

ኤርትራ ለአምሳ ዓመታት በጣሊያን ቅኝ ግዛት ስር ቆይታለች፡፡ ብኋላም በእንግሊዞች ወታደራዊ አስተዳደር ለአስር ዓመታት ስትገዛ ቆይታ በ1952 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውሳኔ ከኢትዮጵያ ጋር በፌድሬሽን እንድትዋድ ሆኗል(ዘውዴ፣ 1963፣ 10)፡፡ ይሁንና

የኤርትራ በፌዴሬሽን መተዳደር እንደታሰበው አልዘለቀም። በዛው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አገዛዝ ዘመን ከፌደሬሽን ወደ ፍፁም ውህደት እንድትሸጋገር በመደረጉ በርካታ ተቃዋሚ ኃይሎችን ማስነሳቱ አልቀረም። ይኸው ተቃውሞ በተለያየ መልኩ እየጎለበተ ሄዶ ዓመታትን የፈጀ ደም አፋሳሽ ጦርነትን አስተናግዷል። ለዓመታት የዘለቀው ጦርነት በ1983 ዓ.ም ከደርግ ውድቀት ጋር ኤርትራን በመገንጠል ተደምድሟል።

በ1983 ዓ.ም. ለውጥ ጊዜ፥ ለውጡን አስመልክተው ከተሰሙ ዘፈኖች፥ ይህንን የኤርትራን ጉዳይ በተለያየ ጭብጥ አንስተው የዘፈኑ ብዙ ናቸው(ለምሳሌ ቴዎድሮስ ታደሰ፣ አስናቀ ገብረየስ፣ ኤፍሬም ታምሩ)። ከነዚህ መካከል ቴዎድሮስ ታደሰ በ1984 ዓ.ም ባሳተመው የሙዚቃ አልበም "ስንቱን ጉድ ቻለ" ሲል የዘፈነው፥ የጊዜውን መንፈስ በወጉ ከሚያሳዩ ዘፈኖች ቀዳሚው ነው። የዚህ ዘፈን የግጥም ደራሲ ተመስገን ተካ ሲሆን፥ በጊዜው በርካታ ፖለቲካዊ ጭብጥ ያላቸውን ግጥሞች በመፃፍ ይታወቃል። ተመስገን በዚህ "ስንቱን ጉድ ቻለ" በተሰኘ የቴዎድሮስ ታደሰ ዘፈን ውስጥ ኢትዮጵያ በኤርትራ ጉዳይ በዓለምና በሀገር ውስጥ ያስተናገደችውን ውጣውረድ ይፈትሻል። "ያም ለኔ ያም ለኔ እኔም ለኔ ስላት፣ ቆንጆ ከሷ ወዲያ የሌለ መሰላት፣" በማለት፥ በጊዜው ኤርትራን በመገንጠልና በማዋሀድ መካከል ያለውን ፍትጊያ ያሳያል። በሴት አምሳል የተሳለችው ግዛት በተለይም "ያም ለኔ ያም ለኔ" ሲል ከኤርትራና ከኢትዮጵያ ኃይሎች በዘለለ ሌላ ሶስተኛ ወገን መኖሩን ያሳብቃል። በአንድ ወገን ኤርትራ እንዳትገነጠል የሚዋደቁ ሲኖሩ፤ በሌላ ወገን ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመነጠል የሚሹ ሌሎች ኃይሎች(የተለያዩ ሀገራት) መኖራቸው ግዛቷን(ኤርትራን) ብዙ አማራጭ ያላት አስመስሏታል የሚል በስላቅ የተሞላ ጭብጥን የያዘ ግጥም ነው።

ገለል በሉ፣ ፈረሱን አስጭኖ፣

ገለል በሉ፣ ጦር እየሰበቀ፣

ገለል በሉ፣ ስንቱ ጎበዝ ጀግና፣

ገለል በሉ፣ በሷ ስም አለቀ።

ለ30 ዓመታት በዘለቀ ውጊያ፤ ሻዕቢያ በ1983 ዓ.ም. የአስመራ ከተማን በእጁ ማስገባቱን አረጋገጠ። ይህ ሂደት ብዙዎችን መስዋዕት ያደረገ ነው። በሁለቱም ተፋላሚ ኃይሎች(የደርግና የሻዕቢያ) ውስጥ በርካቶች ሞተዋል፣ አካላቸው ጎድሏል፣ ተፈናቅለዋል፣ ንብረታቸው ወድሟል(ተከስተ፣ 1997፣ 167)። ዘፈኑ ይህንን ሀቅ ነው የሚተርከው። ትረካው ከቁጭት ጋር ነው። "ስንቱ ጎበዝ ጀግና" በምትል ሀረግ ስር በኤርትራ ምክንያት ለዓመታት የተዋደቁትን

ወታደሮች፣ የጦር መሪ ጀነራሎችን በቁጭት ያነሳል። ቁጭቱ መሄዷ ላይቀር ስንቱ አለቀላት የሚል ነው። ለዚህ ነው በቀጣዮቹ ስንኞች አዲሲቷን “አገር” “አፋጀሽ” የሚል የዳቦ ስም ይውጣላት በማለት የሚደመድመው።

ገለል በሉ፣ ዳቦዉም ይቆረስ፣

ገለል በሉ፣ እስኪ ስም ይዉጣለት፣

ገለል በሉ፣ ስንቱን አነደድሽዉ፣

ገለል ገለል፣ አፋጀሽን እንበላት።

በዚሁ የቴዎድሮስ ታደሰ የ1984 ዓ.ም. አልበም ሌላው ከዚሁ የኤርትራ መገንጠል ጋር የሚገናኝ ጭብጥን የያዘው ዘፈን “ህልምሽ ቅዠት ነው” የሚለው ስራ ነው። የዚህም ግጥም ደራሲ ተመስገን ተካ ነው። ግጥሙ በጊዜው ኤርትራን በተመለከተ ይነሱ የነበሩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በማጣጣል ይሳለቃል። ማርቲን ፕላውት Understanding Eritrea በሚለው መፅሐፋቸው እንደሚያስረዱት፤ በጊዜው ኤርትራ በኢኮኖሚ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትበለፅጋለች፤ እንደ ሲንጋፖርም ትሆናለች፤ የሚል ተስፋ በብዙዎች ዘንድ ይቀነቀን ነበር(2016፣ 103)። የቴዎድሮስ ዘፈን የዚህን መንፈስ የሚፈትሽና ታስቦበት የተሰራ ለመሆኑ አያጠራጥርም።

እኔን ሲኦል ብለሽ ጓዝሽን ጠቅለልሽ፣ ገነት ገባሁ ያልሽው፣

ከኔ ተለይተሽ ስትሄጂ ከመንገድ፣ ማር አገኘሁ ያልሽው፣

ወለል ካለው ሜዳ ወርቅ አልማዝ ልትበይ እንቁ አገኘሁ ያልሽው፣

በገሀድ አልታየም ያንቺስ ህልም አልሆነም አንቺ እንደፈታሽው።

በዚህ ግጥም ውስጥ፤ ሁለት መሰረታዊ ጭብጦች ተዛንቀዋል። የመጀመርያው ጭብጥ፥ “ሲኦል እና ገነት” ከሚሉ ቃላት ስር የሚፈለቀቅ ነው። ከላይ በተነሳው መንደርደሪያ ሀሳብ መሰረት ተነፃፃሪዎቹ ኢትዮጵያና ኤርትራ ናቸው። በደህነት አረንቋ ውስጥ የተዘፈቀችው ኢትዮጵያ ለመኖር የማትመረጥና ተስፋ ያሌላት መሆኗን ለመግለፅ “ሲኦል” በሚል ተለዋጭ ዘይቤ ስትቀርብ፤ እንደሲንጋፖር ታድጋለች በሚል ህልም የተሞላችው ኤርትራ በተቃራኒው “ገነት” በሚል ተለዋጭ ዘይቤ ተገልፃለች። በዚህ የተነሳ ብዙዎች “ወደ ተስፋይቱ ምድር” በተስፋ መሄዳቸውን ግጥሙ ያስረዳል። ሁለተኛው ጭብጥ፥ ከተስፋው በዘለለ የኤርትራን ተፈጥሮዊ እውነታ በማንሳት የታለመው ህልም፤ ህልም ብቻ መሆኑን የሚገልፅ ነው። ለዚህም በጦርነት

የደቀቀው ምድር ወለል ካለሜዳ የዘለለ ሀብት እንዳሌለው በመግለፅ፥ እውነቱ ይህ ነው ለማለት ይሞክራል።

በኤርትራ መገንጠል ጉዳይ ላይ ሌላ የምናገኘው ዘፋኝ አስናቀ ገብረየስን ነው። አስናቀ ገብረየስ በ1984 ዓ.ም. "ሴትን በሴት[9]" በሚለው ስራው የኤርትራ መገንጠል የአዲሶቹ መሪዎች(ኢህአዴግ) የሀገር ክህደት ውጤት መሆኑን ይዘረዝራል። በጊዜው ከሚነሱ አብይ ጭብጦች መካከል ህወሓት መራሹ የኢህአዴግ የሽግግር መንግስት ከውጭ ኃይሎች(በተለይም ከአሜሪካ) ጋር በመመሳጠር ኤርትራን አስገንጥሏል የሚል ክስ ይቀርባል። በዚህ ሂደት ውስጥ የአሜሪካው አደራዳሪ ሄርማን ኮኸን ሚና ከፍተኛ እንደነበር Intervening in Africa ከሚለው መጽሐፋቸው መገንዘብ ይቻላል(Cohen፣2000፣ 39፣ 53)። ዘፈኑ ነገሩ የውጭ ኃይል አይዞህ ባይ ያለበት መሆኑን ሲገልፅ እንዲህ ይላል፤

ማን በልጣብሽ ከኔ ከማን እልፍኝ ገባሽ?

ማነው አቀማጥሎ ያኮራሽ ያደራሽ?

ፍቅርን እንደ ቅርጫ እያቀራመትሽው፣

ቅብጥብጥ ልብሽን ለስንቱ መገብሽው?

ዘፈኑ የመሪዎቹን አዲስነት በማንሳት፤ ሀገር እንዲህ አይመራም ለማለት "የፍቅር ፀበል ፅዋው ሲጠጣ፣ እንዲህ አይደለም ጎጆ ሲወጣ" በማለት የለውጡ መሪዎች አጀማመር ገና ከወዲሁ እንዳላማረው ያስረዳል። ከሁሉም በላይ ግን በዚህ ዘፈን ውስጥ ጎልተው የሚደመጡት ጭብጦች የእስካሁኖቹ አይደሉም። ዋናው ጭብጥ ሀገር መገንጠልን በተመለከተ የተነሳው ነው።

ወገኛ፥ መስሎሽ ነው እንጂ ዋዘኛ፣

ፌዘኛ፥ ደሞ አንቺን ብሎ ሰርገኛ፣

ወትሮም አድኋዊ ዳኛ፣

ይላል የዶሮ ሻኛ፣

ማቀራረቡን እንጂ መገንጠል አናውቅ እኛ።

[9] በዚህ ስራው እርሱም ከሀገር ለመልቀቅ ተገዷል።

በዚህ ግጥም፥ መሆን ያልነበረበት አድሏዊ ፍርድ መፈፀሙን በተለያዩ አኳኋን መገንዘብ ይቻላል። የመጀመርያው "ደሞ አንቺን ብሎ ሰርገኛ" በሚለው ስንኝ ውስጥ የተገለፀው መራር ጭብጥ ነው። ጭብጡ አንድም ለኤርትራ፣ አንድም ለኢትዮጵያ የወቅቱ መሪዎች የተላለፈ ይመስላል። እንዴት ቢሉ፥ አንድም ሁለቱም ኃይሎች ሀገር በመምራት ጅማሮ ሽርጉድ ውስጥ በመሆናቸው "ሰርገኛ" መባላቸው ከዚህ የተነሳ በመሆኑ። አንድም አንዱ ተገንጣይ፥ አንዱ አስገንጣይ ሆነው በመቅረባቸው "ደሞ አንቺን ብሎ" በሚል ስላቅ የተገለፁ በመሆኑ ነው። ሁለቱ ኃይሎች አንድ አገር ሆነው መቀጠል ሲችሉ ሀገር ገነጣጥለው በየፊና ለመንገስ መጣደፋቸውም እንዲሁ "ወገኛ" በሚል ያልተሟላ ሰርግ ወይም ንግስና መሆኑን ግጥሙ ጠንከር ባለ(ወደ ስድብ በተጠጋ) አገላለፅ ያስረዳል።

ሁለተኛው "መገንጠል አናውቅ እኛ" በሚለው ስንኝ ውስጥ "እኛ" የምትለው ቃል ጠለቅ ያለ ትርጓሜን ያዘለች ናት። በዚህ ግጥም ውስጥ እኛ የምትለዋ ቃል መላውን ኢትዮጵያዊ የምትመለከት ናት። ኢትዮጵያዊ ደግሞ በታሪኩ ምድሩን የማያስነካ እምቢ ባይ ነው። ስለዚህ ጥያቄው ኢትዮጵያዊ በታሪኩ የማያውቀውን አገር የመገንጠል ባህል እናንተ ከየት አመጣችሁት ነው? ይህንን ጥያቄ አብይ ጭብጡ ያደረገው ዘፈን ከላይ እንደተገለጸው ርዕሱ "ሴትን በሴት" የሚል ነው። ለምን? በሁለት ምክንያቶች ሊሆን እንደሚችል ከግጥሙ ይዘት መገንዘብ ይቻላል። አንዱና ቀላሉ፥ ግጥሙ የያዘውን መልክት ከጊዜው መሪዎች ለመደበቅና ለሴት የተዘፈነ ነው የሚል አመክንዮ ለማቅረብ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ግን ሴትን በሴት መተካት እንደሚቻለው ሁሉ፤ መሪን በመሪ መተካት ይቻላል የሚል የእምቢታ ድምጽ መሆኑ አያጠራጥርም።

#### 3.2.2.2. የተቃውሞና የስደት ድምጾች

በ1983ቱ ለውጥ ጊዜ ከሰሙ የአማርኛ ዘፈኖች ውስጥ ሌላው ጭብጥ በተቃውሞና በስደት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ይህ ወቅት ሀገሪቱ በብዙ መልኩ ኢኮኖሚዋ የተመሰቃቀለበት ጊዜ ነው። Adejumobi(2007፣ 138) በለውጡ ወቅት የነበሩትን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፈተናዎች በሶስት ጎራ ይከፍላቸዋል። የመጀመርያው አገሪቱ በጦርነትና በድርቅ ብዙ የተጎዳች መሆኗ ነው። ሁለተኛው የውጭ ምንዛሪ እጥረትና ከፍተኛ የሆነ እዳ ነው። ሶስተኛው ብሔርን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ አደረጃጀት ነው። የነዚህ ሶስት ጉዳዮች ድምር ሀገሪቱን ያልተረጋጋች ሀገር እንድትሆን አድርጓታል። የተለያዩ የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት እንዲጎለብትም እድል

ከፍቷል። ለዚህ ይመስላል ገና በጅምሩ የተቃውሞ ድምጾች መሰማታቸው። የተፈራ ነጋሽ "ያሁኑ ይባስ" የተሰኘው የ1983 ዓ.ም. ስራ ጥሩ ምሳሌ ነው።

እንደ ወፍ በረረች ፈጠነች ከነፈች፣

ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።

ተይ ተመለሽ በሏት አጥፍቼ እንደው ልካስ፣

ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።

ይሄ ሁሉ ሩጫ ወዴት ለመድረስ፣

ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።

እንዲህ ቀላል ነው ወይ የካቡትን ማፍረስ፣

ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።

ለምን አላዝን ለምን አይከፋኝ፣

የኑሮው ቅያስ ዘዴው ሲጠፋኝ፣

ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው ለውጡ የከፋ ነገርን እንጂ የተሻለ ሆኖ አላገኘውም። "እንደወፍ በረረች" በሚል ንጽጽር የቀረበው የለውጥ አራማጅ፥ የውሳኔዎቹ ፍጥነት ህይወትን የሚያቀሉ ሳይሆኑ ይበልጥ የሚያወሳስቡና ለዘመናት የተካቡትን ሳይቀር የሚያፈርሱ ሆነውበታል። ለዚህ ነው "እንዲህ ቀላል ነው ወይ የካቡትን ማፍረስ" ማለቱ። ከሁሉ በላይ "የኑሮው ቅያስ ዘዴው ሲጠፋኝ" የምትለዋ ስንኝ የጊዜውን የኢኮኖሚ ድቀት የምታሳይ ናት። ኢኮኖሚያዊው ጫና ገጣሚውን አዲሱን ከድሮው እንዲያነፃፅር አድርጎታል። ሚዛኑ "ያሁኑ ይባስ" ቢያስብለውም ያኛው ጥሩ ነበር ማለት ግን አይደለም። ምክንያቱም ለዚህኛው ውድቀት የዛኛው አስተዋፅኦ አለበት።

ሌላው በዚህ ዘፈን ውስጥ የሚነሳው ጭብጥ የብሔር ጉዳይ ነው። በብሔር የመደራጀት ፖለቲካ አንዱን ባለዘመድ ሌላውን ብቸኛ እያደረገው መሆኑን የሚያሳዩ ስንኞች ተካተዋል።

እንዳቀራረቧ እንደ አለሳለሷ፣

ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።

ማን ነበር ለሰው ልጅ ተቆርቋሪ እንደሷ።

አንቺ ባለዘመድ መካሪሽ ብዙ ነው፣

የኔን ልብ ያስከፋው ብቸኝነቱ ነው፣

መለየት ፈርዶብኝ በማጣት ብቀጣም፣

እኔም ያለልኝ እለት አስታማሚ አላጣም።

ግጥሙ ተቃውሞን ብቻ ሳይሆን ድጋፍንም የያዘ ነው። የመጀመሪያዎቹ ስንኞች ቀድሞ የነበረውን አቀራረብና ተቆርቋሪነት በማድነቅ ዛሬ ወዴት ሄደ? ብለው ይጠይቃሉ። “ማን ነበር ለሰው ልጅ ተቆርቋሪ እንደሷ” በማለት። አሳዛኙ ግን ተቆርቋሪነቷ ወደ ነበር መቀየሩ ነው። ለምን? “አንቺ ባለዘመድ” በማለት ይቀጥላል ዘፈኑ። ግጥሙ እንደሚያሳየው መከፋፈሉ፣ መለያየቱ የሚጀምረው እዚህጋ ነው። ከላይ ለሰው ልጆች ሁሉ ተቆርቋሪ የነበረው ኃይል ዝቅ ሲል በዝምድና መከፋፈልና መለያትን ይጀምራል። ዝምድናው አንድም በብሔር፣ አንድም በፖለቲካ አመለካከት፣ ወይም በሌላ ሊሆን ይችላል። ዋናው ጭብጥ ግን ጎራ መለየት መጀመሩ ነው።

ሌላው ጭብጥ ስደት ነው። ጊዜው በጦርነት፣ በረሃብና በፖለቲካዊ አመለካከት ልዩነት ምክንያት ብዙዎች ለስደት የተዳረጉበት ነው። ከደርጉ ዘመን የጀመረው ሀገር ለቆ መሰደድ በ1983ቱም ለውጥ ጊዜ አልቆመም። በዚህ ምክንያት ስደትን የሚያስተጋቡ ዘፈኖች መሰማት ጀምረዋል። በ1983 ዓ.ም. አስቴር አወቀ “እኔም ሀገር አለኝ” ስትል የተጫወተችው የቁጭት ጭብጥ ያለበት ስራ አንዱ መሳያ ነው።

ሀገር ሀገር ይላል ይህ ሀገረ ብርቁ፣

እኔም ሀገር አለኝ የሚታይ በሩቁ።

## 3.3. የለውጥ ማግስት የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች ዋና ዋና ጭብጦች

### 3.3.1. የ1966 ዓ.ም የለውጥ ማግስት ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈን ዋና ዋና ጭብጦች

ደርግ ስልጣን በያዘ ጥቂት ዓመታት ውስጥ የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች በሀገሪቱ ተስተናግደዋል። በፖለቲካ ረገድ የተለያዩ ተቃዋሚ ኃይሎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል(አንዳርጋቸው፣ 1993፣ 175)። ከዚህ ጋር ተያይዞ በጊዜው የሚወጡ ዘፈኖችም እንዲሁ የዘመኑን ጭብጥ ለመፈተሽ ሞክረዋል። በዚህ ወቅት ከወጡ የለውጥ ማግስት ዘፈኖች

መረዳት እንደሚቻለው ሁለት ጭብጦች በዋናነት ተስተውለዋል። እነዚህም፥ የመጀመርያው የደርጉን አገዛዝ ደግፊው በጽናት የቆሙ ናቸው። በ"ጽናት" ማለቴ አንዳንድ ዘፋኞች(ለምሳሌ አያሌው መስፍን፣ ጥላሁን ገሠሠ) በለውጡ ሰሞን የድጋፍ ዘፈኖችን ቢያሰሙም፤ ኋላ ላይ የተቃውሞ ጭብጦችን የያዙ ግጥሞችን በመዝፈናቸው ነው። ሁለተናው ጭብጥ የአገዛዙን አካሄድ በተለያየ መልክ የሚቃወሙ ናቸው። እነዚህኞቹ በጊዜው በተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች የሚነሱ ጭብጦችን ሳይቀር በግጥሞቻቸው በማካተት ለመዝፈን ሞክረዋል።

ከመጀመርያው እንነሳና፥ በድጋፍ መልክ ከሚጠቀሱ ዘፈኖች መካከል አንዱ የመሐሙድ አህመድ "ጊዜ ደጉ ነገር" የተሰኘው ዘፈን ነው። ዘፈኑ በ1968 ዓ.ም. የተዘፈነ ሲሆን፤ ግጥሞቹ የለውጡን መልካም እድሎች በመዘርዘር ጊዜው ያመጣቸውን በረከቶች የሚያስቃኙ ናቸው።

ወይ ጊዜ ሁሉን ለይቶ የሚያሳይ፣

የአንድነት የፍቅር የጋራ ሲሳይ፣

ህብረትን አወቀ ሁሉም በየዘርፉ፣

የሰላም መንገድ ህይወት ሆነ ትርፉ።

የዘፈኑ አጠቃላይ ጭብጥ በነዚህ አራት ስንኞች ውስጥ ተጠቃሏል። ዋናዎቹ ነጥቦች "አንድነት"፣ "ሕብረት" "ፍቅር" እና "ሰላም" የሚሉት ናቸው። እነዚህ ነጥቦች ሁሉም ወገን የሚፈልጋቸውና የሚያነሳቸው ናቸው። ተቃውሞና ክርክሩም እነዚህ አራት ነጥቦች ይሟሉ፣ ይስፈኑ በሚል ነው። ስለዚህ ገጣሚው ተፈላጊዎቹን ነጥቦች በተለያዩ ስንኞች ውስጥ በመበተን ሁሉም በዚህ የለውጥ ኃይል ውስጥ ተሟልተው ተገኝተዋል ሊል ይሞክራል። ገና በመጀመርያው ስንኝ "ሁሉን ለይቶ የሚያሳይ" በማለት የጊዜውን ገዢ ምሉዕነት ያጸናል።

ሌላው በድጋፍ መልክ የጸና የለውጥ ማግስት ዘፈን የድምጻዊ ቀለመወርቅ ደበበ "ንጋት" የተሰኘው ስራ ነው። ይህ ዘፈን በ1969 ዓ.ም. የወጣ ሲሆን ድርሰቱ የራሱ የቀለመወርቅ ደበበ ነው። በዚህ ግጥም ደርግ ወደ ስልጣን የወጣበት ጊዜ፤ በርዕሱ እንደተገለጸው የንጋት ያህል አስደሳችና አዲስ ስሜት ሰጪ መሆኑ ተደጋግሞ ተነስቷል። በተለይ ደርግ በይፋ አገር ገዢነቱን ያወጀባት መስከረም ወር በዘፈኑ ብዙ ሙገሳ ቀርቦላታል። ከሁሉ በላይ ግን በዚህ ዘፈን ውስጥ የሚነሳው ጭብጥ በለውጡ ማግስት ብቅ ብቅ ያሉ ተቃዋሚዎች ከወዲሁ መከላከልና አደብ ማስገዛት ይገባል የሚል ነው።

ሰርጎ እየገባ ቤታችንን የጎዳው፣

ይደፈን በቶሎ የጠፈጠፍ መግቢያው፣

ጠፈጠፉ ጠፍቶ እንዲሚሚቅ ቤቱ፣

አዲሱ እልፍኛችን ይጥበቅ መሰረቱ፣

የጸደይን ጸሀይ እንደልብ ለመሞቅ፣

የጠፈጠፉን ምንጭ ኩሬውን ነው ማድረቅ፡፡

ከግጥሙ መረዳት የሚቻለው ቁም ነገር፥ የለውጥ ኃይሉ(ደርግ) በአገዛዙ ጸንቶ ይቆይ ዘንድ "ጠፈጠፍ" በሚል የቀረቡት ተቃዋሚ ኃይሎች ሊጠፉ ይገባል ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋናውን ምንጭ "ኩሬውን" በማድረቅ መፍትሔ እንደሚገኝ ግጥሙ ይመክራል፡፡ ኩሬው የቀደመው ስርዓት ሲሆን ጠፈጠፎቹ ደግሞ ከዛ የተረፉትና የለውጥ ጉዞውን ያልተቀበሉት መሆናቸው ነው፡፡

ሁለተኛው፥ በለውጥ ማግስት የሚታየው ጭብጥ የተቃውሞ ወይም በአገዛዙ ያለመስማማትና የጋራ ሀገርን የመሻት ድምጽ ነው፡፡ አገር የአንድ ገዢ አስተሳሰብ የሚንጸባረቅባት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዓይነት አስተሳሰብ ማዕከል ናት የሚል ነው፡፡ አንዱ አንዱን ማሳደድ ሳይሆን ተስማምቶ በጋራ መኖር ይገባል የሚሉ ጭብጦች ተሰምተዋል፡፡ በዚህ ጭብጥ ከሚጠቀሱ ዘፈኖች አንዱ የጥላሁን ገሠሠ "ኧረ ተይ" የተሰኘው ስራ ነው፡፡ ይህ ዘፈን የተዘራ ኃይለሚካኤል የግጥም ስራ ሲሆን፤ ግጥሙ በሀገር ጉዳይ የጋራ ስምምነት እንደሚያስፈልግ ያነሳል፡፡

ኧረ ተይ ለሁሉም ሀገር የጋራ ነው፣

አብረን ብናስብበት ምነው፣

እባክሽ በፍቅር እንያዘው ተስማምተን፣

የማይዘልቅ አምባጓሮ ትተን፡፡

ሌላው ዘፈን የአያሌው መስፍን "ተመለሺ" የተሰኘው ዘፈን ነው፡፡ ዘፈኑ በ1969 ዓ.ም. በራሱ በአያሌው መስፍን የተደረሰ ስራ ነው፡፡ በዚህ ዘፈን ውስጥ በአገዛዙ አለመስማማትን ብቻ ሳይሆን ተስፋ መቁረጥንም እናያለን፡፡

ተመለሺ አንቺ ልጅ ተመለሺ፣

ተመለሺ ናፍቆቴ ተመለሺ፣

እኔን ብቸኛ አድርገሽ የት ትሄጃለሽ።

ግጥሙ ካላይ ከላዩ ሲታይ የፍቅር ነው። ጥላው ለሄደች እንስት የተዘፈነ ይመስላል። ዝርዝሩ ግን ሌላ ነው። አያሌው "ተመለሺ" እያለ የሚዘፍነው የዘመኑ ገዢ ተስፋ ስላስቆረጠው የቀደመውን ስርዓት ነው። የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን ዘመን። አሁን ያለው ገዢ ከቀድሞው ገዢ የባሰ በደሎችን እያደረሰ ነው ስለዚህ ያው የጣልነው ይሻላል የሚል ነው የዘፈኑ ጭብጥ። ቀጣዮቹ የተማጽኖ ስንኞችም እንዲሁ ይህንኑ ጭብጥ የሚያጸኑ ናቸው።

የምታውቂው ዘመድ ታመመ ብላችሁ፣

ያቺን ልጅ በመላ አምጡልኝ እባካችሁ።

### 3.3.2. የ1983 ዓ.ም. ለውጥ ማግስት የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች ጭብጦች

ደርግ ወድቆ፥ ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ሀገር መምራት ከጀመረ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ወዲህ የሚነሱ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የአስተዳደሩን አካሄድ በአንድም በሌላ የሚያጠይቁ ናቸው። በጊዜው ይነሱ ከነበሩ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች መካከል በጎሳና በቋንቋ ላይ የተመሰረተው ያልተማከለ አስተዳደር ሀገሪቱን ወደመከፋፈል ይመራታል የሚለው አንዱ ነው። በተጨማሪም፥ በተለይ በተለያዩ አካባቢዎች ተንቀሳቅሰው የሚሰሩ ባለሀብቶችን በመገደብ የሀገር ኢኮኖሚ ይጎዳል የሚሉ አስተያየቶች ይሰጣሉ። ይህ ዓይነቱ አስተዳደር በጊዜው በገዢው ኢህአዴግ ውስጥ ሰፊ ድርሻ የነበረውን ፓርቲ፤ የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይን(ህወሓት) ለመጥቀም የወጣ ነው በማለት በርካቶች ይተቻሉ (Adejumobi(2007፣ 139)።

በዚህ ወቅት ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች በሁለት አበይት ጭብጦች ላይ ያተኮሩ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ የለውጡን ኢፍትሀዊነት የሚያነሱና ከሄደው ብዙ ያልተሻለ መሆኑን የሚገልጹ ሲሆኑ፤ ሁለተኛው ከደርግ መውደቅና ከኤርትራ መገንጠል ጋር የተያያዙ ጭብጦች ናቸው። በቅደምተከተል እንያቸው።

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራዊያዊ ግንባር(ኢህአዴግ) ገና ከሽግግር ጊዜው ማግስት አካሄዱን በመቃወም ከዘፈኑ ድምጻውያን መካከል አንዱ ይሁኔ በላይ ነው። ዘፈኑ "ወጀብ ነው"

የሚል ሲሆን ግጥሙ በጸጋዬ ደቦጭ የተጻፈ ነው። በዚህ ዘፈን በርካታ ጭብጦች ተነስተዋል። በዋናነት ግን አሁንም ለወጥ የለም የሚሉ ሀሳቦች ተነስተውበታል።

የመጣም የሄደው አንዱ ባንዱ ሲስቅ፣

አንዱ አንዱን ሲነቅፍ፣

ብቸኩል ባይነጋም ለምን ልጣ እንቅፍፍ፣

አልነጋም ወይ ሌቱ፣

ገና ነው ሰዓቱ።

ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው፥ በሀገሪቱ የለውጥ ሂደት ውስጥ የተለመዱ ናቸው ያላቸውን ተመሳሳይ ባህሪያት ያነሳል። የሄደውም የመጣውም እርስበርስ ይነቃቀፋል። ያለፈው እኔ እሻል ነበር ይላል። የመጣው የቀደመውን ይወቀወሳል፥ ይነቅፋል። በዚህ መሀል ለውጥ ፈላጊው ህዝብ ይጎዳል። ነገጋልኝ ሲል መልሶ ይጨልምበታል። ቀጣዮቹ ስንኞች ገጣሚው ባለው አስተዳደር ተስፋ መቁረጡን የሚጠቁሙ ናቸው። የገፋ መገፋቱ፣ የበደለ መበደሉ አይቀሬ ነው በማለት ውጤቱን ለጊዜ ይተዋል።

ተስፋ አትጣ ልቤ ታገሰው ይነጋል፣

ተወው ችዬ ልደር፣

የገፋም ይገፋል ተራ ዋንጫው አይቀር።

ቀጣዩ የጸሐይ ዮሀንስ ዘፈንም እንዲሁ ከላይ የተነሳውን ጭብጥ የሚያጠናክር ነው። የዘፈኑ ርዕስ “ያስጠይቃል” የሚል ሲሆን በ1985 ዓ.ም በታተመ አልበሙ ውስጥ የተካተተ ስራ ነው። የዚህ ዘፈን ግጥም ደራሲ ተመስገን ተካ ነው።

ገና ከጠዋቱ ፍቅራችን ሲወጠን፣

ለዚህ ነበር ለካ ቅብጥብጥ ያረገን፣

ይጣፍጥ ነበረ አጀማመራችን፣

አላማረም እንጂ ኋላ አጨራረሳችን።

አይወነጀልም ደርሶ መውደድ እንደ ገዳይ፣

ያስጠይቃል ፍቅር ሲግል የቃልኪዳን አጉዳይ።

ከዚህ ዘፈን ግጥም የምናገኘው ጭብጥ ቢኖር፥ ለውጡ ሲጀመር በርካታ ተስፋ ሰጪ ቃልኪዳኖች መኖራቸውን ነው። “ይጣፍጥ ነበረ አጀማመራችን” በማለት ይገልጽና ቃልኪዳን

መሻሩን ያስታውሳል፡፡ ቃል ኪዳን ደግሞ በቀላል የሚታለፍ ነገር አይደለም፡፡ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ ለዚህ ይመስላል በዘፈኑ ውስጥ "ያስጠይቃል" የሚለውን ቃል አጽንኦት ሰጥቶ መደጋገሙ፡፡ በዚሁ አልበም ውስጥ "መስሎሻል" የሚለው ዘፈንም እንደዚሁ በዘይቤዎች ተከልሎ ተመሳሳይ ጭብጦችን ያነሳል፡፡ በተለይ "ተነቃቃን፣ ተለያን እስኪበቃን" በምትለዋ ስንኝ ከአዲሱ ገዢ ጋር በይፋ ፍቺ መፈጸሙን ያጸናል፡፡ ምክንያቶች አሉት፡፡ ምክንያቶቹ እስካሁን የተዘረዘሩት ናቸው፡፡ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የፍትህ መጓደል፣ የቃል ኪዳን መሻር፣ በጎሳና በቋንቋ ላይ የተመሰረተው የአገዛዝ ስርዓት፣ የኤርትራ መገንጠል፣ ወዘተርፈ ጉዳዮች የጊዜው ጭብጦች ናቸው፡፡ በነዚህ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በወቅቱ በሚወጡ የአማርኛ ዘፈኖች ውስጥ መሰል ጭብጦች ተስተውለዋል፡፡ ለምሳሌ በዛው በ1985 ዓ.ም የወጣው የንዋይ ደበበ "ሀገሬ ሰው አጣሽ ወይ" የሚለው ዘፈን ይህንኑ ጭብጥ የሚያጠናክር ነው፡፡ ገና ከጅምሩ "ሀገሬ ሰው አጣሽ ወይ" በማለት፥ ሀገር የሚለውጥ፣ ፍትህ የሚያሰፍን፣ ኢኮኖሚውን የሚያሳድግ፣ በጥቅሉ ሀገር ከፍ የሚያደርግ ትውልድ ጠፍቷል በማለት፤ በተለይም ከጥንት ጀምሮ የተፈራረቁ መሪዎች፥ መሪነታቸውን ከራሳቸው ፍላጎት በዘለለ ሀገራ ለመለወጥ እንዳልሰሩበት በቁጭት ድምጸት ይወቅሳል፡፡

እስቲ ሁላችን ያብከንክን ይቆጨን፣

ከራብ ስደት ሌላ ምን ታሪክ አቆየን?

በማለት ይብከነከናል፡፡ ገጣሚው ጥያቄውን ለራሱ ጭምር ያነሳል፡፡ ከእኔ ጀምሮ ምን የረባ ቁምነገር ለሀገር ሰራን ይላል፡፡ በተለይ ደግሞ ሀገር እንለውጣለን፣ የተሻለ ለውጥ እናመጣለን ብለው ስልጣን የሚይዙ ሹመኞች ከሹመት የዘለለ ስራ መስራት እንዳልቻሉ ያነሳል፡፡ "አንዱ ሲያሳድግሽ አንዱ ይዘርፍሻል፣ አንዱ ሲሞትልሽ ደግሞ አንዱ ይሸምብሻል" በማለት፤ የመጣው ከሄደው ያልተሻለ እንደሆነና ተመሳሳይ ስርዓቶች በተለያዩ ጊዜና ሰዎች አሁንም መቀጠላቸውን ይገልጻል፡፡ አንዱ ሲሰራ አንዱ እያፈረሰ፥ ጉዟችን ሁሉ "ከድጡ ወደ ማጡ" እንደሚሉት አባባል ወደፊት ያልተራመደ መሆኑን በቁጭት ይፈትሻል፡፡

በኢኮኖሚ ረገድ፥ በሀገሪቱ ብዙ እድገት ሊያመጡ የሚችሉ ምቹ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ቢኖሩም፣ መስራት የሚችል በቂ የሰው ኃይል ቢኖርም፤ ማንም በወጉ ሊሰራባቸው እንዳልቻለ በቀጣዮቹ ስንኞች ይዘረዝራል፡፡ በእንቶኔ ዘይቤ ኢትዮጵያን ይጠይቃል፥ ያናግራል፡፡

ወንዝ እያለሽ አለማሽም፣

ልጅ እያለሽ አልተጠቀምሽም ፣

ውስታሽስ ይሄ ነው ወይ?

ሀገሬ ሰው አጣሽ ወይ?

ሀገሬ አሳቢ አጣሽ ወይ?

ሀገሬ ልጅ አጣሽ ወይ?

ወደ ሁለተኛው ጭብጥ እናምራ። ከ1983 ዓ.ም. ለውጥ ማግስት፥ ለውጡን አስመልክተው የተዘፈኑ የአማርኛ ዘፈኖች ሌላው ትኩረታቸው፥ ልክ እንደ ለውጥ ጊዜው ሁሉ አንደኛው የኤርትራ ጉዳይ ሲሆን፤ ሌላው "የደርግ ሰራዊት" ናቸው በሚል፤ በህወሓት መራሹ የኢህአዴግ አገዛዝ የተበተኑትን ወታደሮች የሚመለከቱ ጭብጦች እንደሆኑ በዚህ ጥናት ተፈትሿል።

እነዚህ ሁለት ጭብጦች በተለይም በኤፍሬም ታምሩ የ1985 ዓ.ም. መጨረሻ አልበም ውስጥ የተገኙ ናቸው። በዚህ አልበም ውስጥ ከተካተቱ ዘፈኖች መካከል "ጎጆሽ ይሻላል" የተሰኘው ስራ አንዱ ሲሆን ግጥሙ የአበበ መለሰ ነው። በዚህ ግጥም ውስጥ ኤርትራን የሚመለከቱ የሚመስሉ ስንኞች ለፍካሬ ቀርበዋል። "ጎጆሽ ይሻላል" በሚል ተለዋጭ ዘይቤ፥ ጎጆዋን ጥላ ስለሄደች እንስት ይዘፍናል። ራሮት በተሞላው ድምጸት ትልቁን ቤቷን ጥላ ወደ ከተማ ስለኮበለለች ሴት ያነሳል። ጎጆሽ ይሻላል ተመለሺ እያለ ይማጸናል።

የዚህ ዘፈን ፍካሬ ከዘመኑ መንፈስ የሚቀዳ ነው። ዘመኑ ኤርትራ የተገነጠለችበት፣ ቤተሰብ ከቤተሰብ ዘመድ ከዘመድ ይበልጥ መራራቅ የጀመረበት ነው። ከለውጥ ጊዜው በላይ የኤርትራ መገንጠልና እንደ ሌላ ሀገር መታየት ለብዙዎች መቀበል የከበደበት ጊዜ ነው። ስለዚህ ገጣሚው "ጎጆሽ" በሚል ተለዋጭ ዘይቤ፥ የሁለቱን ሀገራት የጋራ ቤት የነበረችውን ኢትዮጵያን በመፍትሄነት በማቅረብ፥ ተገንጣዩዋን ሀገር ተመለሽ ወደነበርሽበት በማለት ይማጸናል።

እንደምነሽልኝ እንደምን ባክሽ፣

ከተማው ኑሮው እንዴት አረገሽ፣

ሁሉንም ትተሽ ተመለሽ፣

ውብ ዓለም እባክሽ፣

ጎጆሽ ይሻላል ንብረትሽ፣የደሃው ትዳርሽ።

ግጥሙ፥ የለውጡን ማግስት ጭብጥ የሚያሳይ እንደመሆኑ፥ የኮበለለችዋ እንስት(የተገነጠለችዋ ሀገር) ኩብለላዋ ውሎ ያደረ መሆኑን ለማስታወስ አከራረሟን ይጠይቃል። "ከተማው ኑሮው እንዴት አረገሽ?" በማለት፤ ዋናውን ጎጆዋን ትታ ብቻዋን ከቆመችበት እለት አንስቶ የገጠማትን

ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተግዳሮት ይጠይቃታል። ተጠያቂዋ መልስ ባትሰጥም፤ ገጣሚው ግን መልስ ይሰጣል። ከአመላለሱ አንድ ነገር መረዳት ይቻላል። ሂያጇ አልደላትም። ኑሮው እንዳሰበችው አልሆነላትም። ስለዚህ ትታ ወደሄደችው ወደ ደሃው ጎጆዋ እንድትመለስ ይማጸናታል። እዛም ያልተመቸ ሁኔታ ከገጠማት፣ እዚሁ በለመደችው ደሃ ጎጆ አብሮ መጓዙ የተሻለ ውጤት ያመጣል የሚል መደምደሚያን ያዘለ ጭብጥ ነው። ገጣሚው ጎጆ ሲል የገለጻትን አገር ደሃ አድርጎ ማቅረቡ፤ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሌላው በዚህ ዘፈን ውስጥ የተካተተው ጭብጥ፥ በተለይም በኢትዮጵያ በኩል የኤርትራ መገንጠልና አገር መሆን ያሳደረውን ስሜት በተመለከተ ሲሆን፥ ነገሩን ከቀጣዮቹ ስንኞች መረዳት ይቻላል።

እኔስ ከማፍቀር፣

ከመንሰፍሰፌ ዋይ ከመውደድ በቀር፣

ቤቴን አፍርሳው ትጓዘዋለች አላልኩም ነበር።

እሷስ ቆርጣለች ለካስ ሄዳለች ዋይ በኔው ጨክና፣

ጨለማ አልብሳኝ ሃዘን አውርሳኝ ዋይ ቤቴን በትና።

በዚህ 1983 ዓ.ም. የለውጥ ማግስት፥ በኤፍሬም ታምሩ አልበም ውስጥ የተካተተው ሌላው ዘፈን "ገዳይ ነሽ ገዳይ" የሚል ርዕስ የተሰጠው ሲሆን፤ የግጥሙ ደራሲ ይልማ ገብረአብ ነው። በዚህ ዘፈን ውስጥ ምናገኘው ጭብጥ በዋናነት "የደርግ ሰራዊት" ተብለው በጊዜው ስርዓት የተበተኑትን ወታደሮች የሚመለከት ነው። ግጥሙ የወታደሮቹን መበተንና ያሳደረውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምስቅልቅል በማሳየት፥ የድርጊቱን ኢፍትሀዊነት ያስረዳል።

እኔ እንደ ጀግና፣ ሽጉጥ ታጥቄ፣

ቀረሁኝ ወድቄ።

እኔ እንደ ጀግና፣ ብረት አንግቼ፣

ቀረሁ ተረትቼ።

ከግጥሙ መረዳት እንደሚቻለው፥ ሽጉጥ ይዞ፥ ሌላም መሳሪያ ታጥቆ የቆመ ግና በአንዳች ምክንያት የተሸነፈ ገጸ ሰብ ይታያል። ሽንፈቱን በቁጭት የሚተርክ ተብከንካኝ። አንድ ጥያቄ ግን ያስነሳል። ብረት የታጠቀ፣ እንደ ጀግና የቆመ ምን ሆኖ ይሸነፋል? ሽንፈቱ በምንድነው? Adejumobi(2007፣ 134) እንደሚያስረዱት፥ በጊዜው የደርግ ሽንፈትን ተከትሎ፤ በአፍሪካ

ትልቅ የሚባለው የደርግ ወታደር እንዲበተንና በአብዛኛው በትግራይ ተወላጅ ወታደርና አመራር እንዲተካ ተደርጓል። በዚህ ምክንያት በርካታ የቀድሞ ወታደሮች ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ መጋለጣቸውን ያስረዳሉ። በዚህ ዘፈን ውስጥ የተካተቱት ቀጣዮቹ ስንኞች ይህንኑ ጭብጥ የሚያጠናክሩ ናቸው።

ተኩሼ ባልመታ፣ ባይጥልም ለበኔ፣
እጄን ሰጠኝ ብለሽ፣ ዝና አታፍሪ በኔ።
መንፈሴም ይረበሽ፣ ሆዴንም ይጭነቀው፣
ቆብ ሊጥል አይደለም፣ ብረት የታጠቀው።

## ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

የዘፈን ግጥሞች በተጻፉበት ዘመን የነበሩ ማህበራዊ፣ ኢኮሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ስነልቦናዊ ጭብጦችን የመሸከም አቅማቸው ከፍተኛ ነው። በዚህ ጥናት ማረጋገጥ የተቻለውም ይህንኑ እውነት ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፥ በለውጥ ላይ ያተኮሩ የለውጥ ሰሞን የአማርኛ የዘፈን ግጥሞችን አበይት ጭብጦች መፈተሽ ነው። በዚህ መሰረት፥ ከ1966 ዓ.ም እስከ 1986 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ በተከሰቱ ሁለት የለውጥ ጊዜያት (1966 እና 1983) ላይ በማተኮር፤ በጊዜው የተዘፈኑና ለውጥ ላይ ያተኮሩ የአማርኛ ዘፈኖች ግጥሞችን ዋና ዋና ጭብጦች ተፈትሿል።

ጥናቱ፥ የለውጥ ሰሞናትን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ለይቶ የፈተሸ ሲሆን፤ እነዚህም የለውጥ ዋዜማ፣ የለውጥ ጊዜና የለውጥ ማግስት በሚል የተከፋፈሉ ናቸው። በዚህ ጥናት፤ የለውጥ ሰሞን ማለት ከለውጥ ዋዜማ እስከ ለውጥ ማግስት ያለውን ጊዜ የሚያጠቃልል ነው። የለውጥ ዋዜማ የሚባለው፥ ለውጥ ከመከሰቱ ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ፤ ለውጥ እስከተካሄደበት እለት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያካትት ነው። ይህ ማለት የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ ሲባል፤ ከመስከረም 1966 እስከ መስከረም 1967 ዓ.ም. ያለውን አንድ ዓመት ይይዛል። ምንም እንኳ ለውጡ ከየካቲት 1966 ዓ.ም. ጀምሮ የተካሄደ ቢሆንም፤ ይህ ዓመት አንድም፦የለውጥ ዋዜማ፤ አንድም፦ የለውጥ ጊዜ ሆኖ የተፈተሸ ነው። ለምን ቢሉ፤ አንድም፦ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በይፋ ስልጣናቸውን ለቀው ከቤተ መንግስታቸው የወጡት በመስከረም 1967 ዓ.ም. በመሆኑ፤ አንድም፦የሕብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜአዊ ወታደራዊ መንግስት(ደርግ) በይፋ ስልጣኑን ያወጀው በዚሁ በመስከረም ወር 1967 ዓ.ም. በመሆኑ ነው። ሌላው የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ ሲሆን፤ ይህም ከግንቦት 1982 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 1983 ዓ.ም. ድረስ ያለውን አንድ ዓመት ያጠቃልላል።

የለውጥ ጊዜ ሲባል ደግሞ፥ ለውጥ ከተከሰተበት እለት ጀምሮ ወደፊት የሚቆጠሩ ሁለት ዓመታትን ብቻ የሚያጠቃልል ነው። በዚህ መሰረት የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ጊዜ ማለት፤ ከየካቲት 1966 እስከ ጳጉሜ 1967 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ሲሆን፤ የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ጊዜ ደግሞ፤ ከግንቦት 1983 እስከ ጳጉሜ 1984 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል።

ከሁለት ዓመት በኋላ የሚቆጠሩት ሌሎች ሁለት ዓመታት ደግሞ፤ የለውጥ ማግስት በሚል የቀረቡ ናቸው። ይህም ሲብራራ፤ የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ማግስት ማለት፤ ከመስከረም 1968 እስከ ጳጉሜ 1969 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ ማለት ሲሆን፤ የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ማግስት ደግሞ፤ ከመስከረም 1985 እስከ ጳጉሜ 1986 ዓ.ም. መጨረሻ ማለት ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት እነዚህ ንዑሳን ክፍሎች እያንዳንዳቸው፤ በጊዜያቸው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞችን አብይ ጭብጦች በመለየት፤ ከተግባራውያን ንድፈ ሀሳብ አንጻር ተፈትሸዋል። በዚህ መሰረት፥ በሶስቱ የለውጥ ክፍሎች(የለውጥ ዋዜማ፣ የለውጥ ጊዜና የለውጥ ማግስት) የተመለከቱና በዚህ ጥናት የተገኙ ዋና ዋና ጭብጦች ቀጥለው የቀረቡት ናቸው።

በቅድሚያ የምናገኘው የለውጥ ክፍል፥ የለውጥ ዋዜማን ሲሆን፤ ይህም የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማና የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ዋዜማ፤ በሚል ንዑስ ርዕስ የተከፋፈሉ ናቸው። በሁለቱ ለውጦች ዋዜማ የታየ የጋራ ጭብጥ ቢኖር፤ በሁለቱም ውስጥ የተሻለ ስርዓትን ተስፋ የሚያደርጉ የዘፈን ግጥሞች መሰማታቸው ነው። በዚህ ውስጥ የዲሞክራሲ፣ የኢኮኖሚና የሀገር አንድነት ጥያቄዎች የግጥሞቹ ማዕከላዊ ጭብጥ ሆነው ቀርበዋል።

በሌላ በኩል፥ የለውጥ ዋዜማዎቹ እንደየ ዘመናቸው ርቀት ለየቅል የሆኑ ጭብጦችን ማንሳታቸው አልቀረም። ለምሳሌ፥ በ1966ቱ ለውጥ ዋዜማ ከተሰሙ ጭብጦች መካከል አንዱ የመሬት ጉዳይ ሲሆን፤ በ1983ቱ ዋዜማ በአንጻሩ የብሔር ጥያቄ ጎልቶ ተስተውሏል። የ1966ቱን ድርቅ መሰረት ያደረጉ የዘፈን ግጥሞችም እንደዚሁ በ66ቱ የለውጥ ዋዜማ ላይ የተሰሙ ሲሆን፤ በ83ቱ ለውጥ ዋዜማ ላይ ደግሞ ኤርትራን የሚመለከቱ ጭብጦች ተነስተው ተዘፍነዋል።

ሁለተኛው፥ በዚህ ጥናት የተፈተሸው ክፍል የለውጥ ጊዜ ነው። ይህም የለውጥ ዋዜማ ላይ እንደተገለጸው ሁሉ፤ የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ጊዜና የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ጊዜ፥ በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው። በነዚህ ሁለት የለውጥ ጊዜያት በተለይ ሁለት አበይት የጋራ ጭብጦች ተስተውለዋል። እነዚህም፥ የመጀመርያው የድጋፍና ያለፈውን ወቃሽ ድምጾች ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ የጥርጣሬ ድምጾች ናቸው። በተለይ በ1966ቱ ለውጥ፥ ያለፈውን የፊውዳሉን፥ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ዘመን የሚወቅሱና ደርጉን የሚያሞግሱ ዘፈኖች በስፋት ተሰምተዋል። ገና ከጅምሩ ከጭለማ ወጣን፣ አዲስ ቀን ነጋልን በሚል አያሌ ሙገሳዎችን የሚያዘንቡ ጭብጦች በዚህ ዘመን ላይ ተሰምተዋል። በ1983ቱ ለውጥ ጊዜ የተሰሙት የድጋፍ

ድምጾች በአንጻሩ በጣም ጥቂት ናቸው። ሁለተኛው ጭብጥ ላይ ግን በሁለቱም ለውጦች ተመጣጣኝ ጭብጦች ታይተዋል። አዲሶቹን ስርዓቶች ገና በወራት እድሜ ውስጥ በጥርጣሬ የተመለከቱ ዘፈኖች በሁለቱም ለውጦች ሰሞን ተዘፍነዋል። ጥርጣሬዎቹ፥ አንድም ለውጡ የተሻለ አይደለም፤ እንደውም የባሰ ነው የሚል ነው። አንድም፥ የሀገሪቱ ኢኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መጪውን የሀገሪቱን አንድነትና ሰላም የሚያረጋግጡ አይደሉም ከሚል ጥርጣሬ የመነጩ ናቸው።

በ1983ቱ የለውጥ ጊዜ ሌላው ጎልቶ የሚነሳው ጭብጥ የኤርትራ መገንጠል ጉዳይ ነው። በግዛቲቱ ሀገር ሆና መገንጠል ሚና የነበራቸውን ፖለቲከኞች የሚወቅሱ ጭብጥ ያዘሉ ዘፈኖች ተሰምተዋል።

በዚህ ጥናት የተፈተሸው ሶስተኛው ክፍል የለውጥ ማግስት ነው። ይህም ከላይ እንደቀረቡት ሁሉ የ1966 ዓ.ም. የለውጥ ማግስትንና የ1983 ዓ.ም. የለውጥ ማግስት የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞችን ፈትሿል። በመሆኑም፤ በዚህ ክፍል(በለውጥ ማግስት) የተነሱት ጭብጦች በአብዛኛው ተመሳሳይ ሲሆኑ፤ እነዚህም፥ የተቃውሞ፣ የስደትና የሀገር አንድነት ጉዳዮች ናቸው።

ይሁንና በ1983ቱ ለውጥ ዋዜማ የኤርትራ ጉዳይ አሁንም የዘፈኖቹ ጭብጥ ሆኖ ተነስቷል። በተጨማሪም፤ የደርግ ወታደሮችን በሚመለከት የተነሳ ጭብጥም እንዲሁ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ተፈክሯል።

በአጠቃላይ፤ በለውጥ ሰሞን ላይ አተኩረው የተዘፈኑ የአማርኛ የዘፈን ግጥሞች፤ በዘመናቸው የተከሰቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን አንስተው በተለያየ መልክ ማንጸባረቃቸውን በዚህ ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል። ነገር ግን ጥናቱ ከተነሳበት ወሰን አንጻር ሌሎች ሊጠኑ የሚገቡ ጭብጦችን አልተመለከተም። ስለዚህ በዘፈን ግጥሞች ላይ የሚደረግ ጥናት በሌሎች ጉዳዮች ላይም አተኩሮ ሊሰራ እንደሚችል ይህ ጥናት አመላካች ነው። ለምሳሌ ከአማርኛ ቋንቋ ውጪ የተሰሩ ዘፈኖችንና ከለውጥ ባሻር ያሉ ጭብጦችን ማጥናት ቢቻል ሌላ የዘመን መልክ ማየት ይቻል ነበር።

## የዋቢ ጽሑፎች መዘርዝር

### <u>አማርኛ መጽሐፍት</u>


ሄኖክ ኃይሌ። (2010)። **ሕማማት**። ርኖቦት አታሚዎች፤ ሦስተኛ እትም።

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ። (2008)። **የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፤ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922**። ሶስተኛ እትም። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕረስ።

ባህሩ ዘውዴ። (2013)። **ፋና ወጊ የለውጥ አቀንቃኞች በኢትዮጵያ፤ በሃያኛው መቶ ዓመት መባቻ**። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ።

ተክለፃድቅ መኩሪያ። (1983)። **ዐፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት**። ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

አየለ እሸቱ። (2013)። **ክብር ዘበኛ፤ የሥልጣኔ ፈር -የለውጥ ፋና ወጊ**። የኢትዮጵያ ኮርያ ዘማቾች ማህበር። ኖቫ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤(1993)። **አማርኛ መዝገበ ቃላት**። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዘከርያ መሀመድ። (2007)። **ጥላሁን ገሰሰ፤ የሕይወቱ ታሪክና ምስጢር**። MAM printing press PLC።

ዘውዴ ረታ። (1992)። **የኤርትራ ጉዳይ፥ ከ1941-1963 (እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር)**። ሻማ ቡክስ።

ዘሪሁን አስፋው። (2009)። **የስነ ጽሑፍ መሰረታውያን**። አደይ ማተሚያ ቤት።

ይናገር ጌታቸው። (2014)። ጠመንጃና ሙዚቃ። ያልታተመ ለኅትመት የተዘጋጀ መጽሐፍ።

ጳውሎስ ኞኞ። (1984)። **አጤ ምኒልክ**። ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት።


### <u>አማርኛ ጥናቶች</u>


ፈቃደ አዘዘ። (1965)። የሶስት የወታደር የሙዚቃ ክፍሎች ዘፈኖች የአማርኛ ግጥም ጥናት። የመጀመርያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት። ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ።

ታምራት ገሰሰ:: (1971):: “ከ1966 ዓ.ም ወዲህ በብሔራዊ ትያትር የዘመናዊ ኦርኬስትራ የቀረቡ ግጥሞች ቅርጽና ይዘት:: የመጀመርያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

አስቴር ሙሉ:: (2007):: ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ::

## <u>እንግሊዘኛ መጽሐፍት</u>

Andargachew Tiruneh. (1993). **The Ethiopian Revolution: 1974-1987. A Transformation from an aristocratic to a totalitarian autocracy**. Cambridge University press.

Adejumobi Saheed. (2007). **The History of Ethiopia**. Greenwood press.

Bahiru Zewde. (2002). **A History of Modern Ethiopia: 1855-1991**. Second Edition. Ohio University Press.

C.R. Kothari. (2004). **Research methodology: methods and techniques**. University of Rajasthan Jaipur, India.

Count Gleichen. (1898). **With the mission to Menelik**. London.

Falceto Francis. (2001). **Abyssinie Swing: A Pictorial History of Modern Ethiopian Music.** Shama Books, Addis Ababa.

Ferris Jean. (1995). **MUSIC: The Art of listening.** 4thEd. Arizona state University.

Haralambos with Herald. (2013). **Sociology: Themes and perspectives.** Oxford University press.

Hammond, Ron. (2010). **Introduction to Sociology.** London: Smash words Edition.

Herman J. Cohen. (2000). **Intervening in Africa: Superpower peacemaking in a Troubled Continent**. St. MARTIN’S PRESS, LLC.

Kathryn Olsen. (2014). **Music and Social Change in South Africa.** Temple University press; Philadelphia.

Martin Plaut. (2016). **Understanding Eritrea; Inside Africa's Most Repressive State.** Oxford University press.

Pankhurst, Silvia. (1955). **Ethiopia a Cultural History.** London: Oxford University Press.

Tekeste Negash. (1997). **Eritrea and Ethiopia: the federal Experience.** Dalarna University.

Zenebe Bekele. (1987). **Music in the horn: A preliminary analytical approach to the study of Ethiopian music.** Stockholm: Sweden.

## እንግሊዘኛ ጥናቶች

Ashenafi Kebede. (1971). The Music of Ethiopia: Its Development and Cultural Setting. PhD Dissertation. Wesleyan University.

_______. (1976). Zemanawi muzika: Modern trends in traditional secular music of Ethiopia. The Black perspective in music.

Endale Beshir. (2009). THEMATIC SIGNIFICANCE OF BIBLICAL ALLUSION IN CONTEMPORARY AMHARIC SONGS. MA Thesis; Addis Ababa University.

Eckstein, Lars (2010). Reading Song Lyrics. Amsterdam: Rodopi B.V.

Elizabeth J. Kizer. (2008). Protest song lyrics as rhetoric. University of Mississippi.

Henze paul. (1991). Ethiopia in 1991 peace through struggle.

Hilina Fekaddu. (2020). Analysis of Ethiopian 'Kignts' used dominantly in popular songs produced as commercial music in the 1960-1980s: The Modern recording songs in Addis Ababa. MA Thesis; Yared music School.

Heather Skinner. (2018). "Ethnic and Cultural Identity in Music and Song Lyrics", Arts and Market. (Jan20/2022https://doi.org/10.1108/AAM-03-2018-0003).

Nigus Yilma. (2018). Thematic Analysis of Selected Amharic Song Lyrics: A Sociological Approach. PhD thesis. Addis Ababa University.

Patricia Fox Ransom. (2015). Message in the Music: Do Lyrics Influence Well-Being? University of Pennsylvania.

Selam Seyoum. The origin and development of zamanawi music in Ethiopia 1896-1974. BA Thesis. Addis Ababa University Department of History.

Tsion Yohaness. (2007). Gender Issues and Women's Portrayal in Secular Amharic Songs produced in Cassettes (in 1997). MA Thesis, Addis Ababa University,Institute of Gender Studies, Addis Ababa.

Woube Kassaye. (1995). Content analysis of secular Amharic songs produced in cassettes (1974-1994): Implications for curriculum planning. MA thesis: Addis Ababa University.

Timkehet Teffera. (2009). The Role of Political Songs in Ethiopia During the Long Protracted War (1974-1991): A Case Study on Identity, Integration and Conflict in Central and Northern Ethiopia.

## አባሪዎች

### ሀ. የለውጥ ዋዜማ ዘፈኖች ግጥሞች

**1. ኩኩሉ አለ ዶሮ**

ኩኩሉ አለ ዶሮ፣
ምን ይሰማ ይሆን ጆሮ፣
ዘንድሮ።
ለካስ ሊነጋ ነው፣
ኩኩሉ ሲል የሰማነው፣
ፀጋ ነው።
እስከ ዛሬ ኖሮ ሳንረዳ፣
ቀስቃሽ አጥተን ስንጎዳ፣
ጨለማው ነጋ መሠለኝ፡
ዶሮ ጮሆ ቀሰቀሰኝ።
ወዛደሩም ነቅነቅ አለ፣
እኩል አድሮ እኩል ዋለ፣
ሲኖር በዱቤ እየለፋ፣
ዛሬ  አገኝን በቂ ተስፋ።
ኩኩሉ አለ ዶሮ፣
ምን ይሰማ ይሆን ጆሮ፣
ዘንድሮ።
ለካስ ሊነጋ ነው፣
ኩኩሉ ሲል የሰማነው፣
ተስፋ ነው።
ዶሮ የንጋት ምልክት፣
ነውና የሚያስመለክት፣
ንቁ ንቁ እንዳትተኙ፣
ቅድሚያን ይዛችሁ ተገኙ።
ህብረታችን እየፀና፣
ጥሩ አቅጣጫ ይዟልና፣
ምንም የለ የሚያስከፋ፣
እስካሁን በአገኝነው ተሰፋ።
ኩኩሉ አለ ዶሮ፣
ምን ይሰማ ይሆን ጆሮ፣
ዘንድሮ።
ለካስ ሊነጋ ነው፣
ኩኩሉ ሲል የሰማነው፣
ፀጋ ነው።
በጨለማ በውድቅት፣
ስንዳክር ያለ ምርት፣
ቀኑን ከሌት ሳንለይ፣
ለኖርንበት በተለይ፣
አሳለፍናት ያቺን ቀን፣
በህብረት ተክዘን፣
ዶሮ ጮሆ ነግሯል ለኛ፣
ልማድ መስሎን እንዳንተኛ።

ድምፃዊት፥ ብዙነሽ በቀለ
ግጥም፥ ሳህሌ ደጋጎ
1966 ዓ.ም.

## 2. ዋይ ዋይ ሲሉ

ዋይ ዋይ ዋይ ሲሉ፣
የረሀባን ጉንፋን ሲስሉ፣
እያዘንኩን በዐይኔ ዐይቼ፣
ምን ላድርግ አለፍኳቸው ትቼ፡፡
ወይ እማማ ወይ አባባ፣
ብለው ሲሉ ሆዴ ባባ፣
አስጨነቀኝ ጭንቀታቸው፣
ምንስ ሆኜ ምንላርጋቸው፡፡
ሳያቸው ዐይኔ አፍጦ፣
ተለየኝ ልቤ ደንግጦ፣
ተብረከረከ ጉልበቴ፣
ምን ላድርግ ዋ ድህነቴ፡፡
በረሃብ ስቃይ ቸነፈር፣
ግማሹ ጎኔ ሲቸገር፣
ክው ብሎ ደርቆ አፋቸው፣
የግዜሩ ውሃ ሲጠማቸው፣
አዝማች
በዱር አምባ እየፈሰሱ፣
ለአቅመ አዳም ያልደረሱ፣
ሁሉም ህጻን ልጆች ናቸው፣
ምንስ ሆኜ ምን ላርጋቸው፡፡
ተአምር ነው የአምላክ ስራ፣
መቼ ያልቃል ብናወራ፣
አንደን ጎርፍ አጥለቅልቆት፣
ሌላው ያልቃል በድርቅት፡፡

በዝች ከንቱ ድልል ዓለም፣
መቼም ጠገብኩ የሚል የለም፣
የተገኘውን እንስጣቸው፣
ቸርነቱን አንንሳቸው፡፡
ይብላኝልኝ ለናታቸው፣
አዘንኩ እኔ ለአባታቸው፣
ከህጻን ጋር ተንከራተው፣
የሚይዙት ነገር አጥተው፡፡
ምድር ሰማይ ሆነባቸው፣
ሰማይ ጥላ ነፈጋቸው፣
በረሃብ ስቃይ ተጨነቁ፣
ተሰደው አገር ለቀቁ፡፡
ሳር ቅጠሉ ደርቆባቸው፣
እምቧ እያሉ ከብቶቻቸው፣
ተበታትነው በያሉበት፣
ወድቀው ቀሩ እንደዘበት፡፡
አዝማች

ድምጻዊ፡- ጥላሁን ገሠሠ
ግጥም ሳህሌ ደጋጎ
1966 ዓ.ም.

## 3. መለዮው ጥላ አለው

ደኔ በለው በለው(2x)፣
ቆፍጣናው ወታደር
መለዮው ጥላ አለው፡፡
ደኔ በለው በለው(2x)፣
አትለውም ወይ፣
ኧረ በለው በለው፣
አትለውም ወይ፣

ቆራጡ ወታደር አይደለህም ወይ::
ቆራጡ ወታደር ባለመለዮው፣
አይደለም ግምባሩ ያስፈራል ጥላው::
እንዲህ ተዝናንቼ ደልቶኝ የምኖረው፣
ቆፍጣናው ወታደር በመለዮው ስር ነው::
የበረሃው ዳኛ የገደል አሞራ፣
ሲነጋገር ያድራል ከጠመንጃው ጋራ::
ሲያንጎራጉር ያድራል ከጠመንጃው ጋራ::

ድምፃዊ፥ አያሌው መስፍን
ግጥም፥ አያሌው መስፍን
1966 ዓ.ም.

4. **ነይ ግቢ ግቢ**

ኧረ ነይ ግቢ ግቢ ግቢ፣
ኧረ ተይ ግቢ ግቢ ግቢ፣
ኧረ ነይ ግቢ ግቢ ግቢ፣
አንቺ ልጅ ግቢ ግቢ ግቢ፣
አቤት::
ኧረ ነይ ግቢ ግቢ ግቢ፣
ኧረ ተይ ግቢ ግቢ ግቢ፣
ኧረ ነይ ግቢ ግቢ ግቢ፣
በኔ ሞት ግቢ ግቢ ግቢ::
ውጡና አነጋግሯት አንድ ሁለት ሆናችሁ፣
የቆመችበትን ምክንያት ጠይቃችሁ፣
እሷ ውጭ ቆማ በር ተቀምጣ፣
ማን እህል ሊበላ ማን ውሃ ሊጠጣ?
የታለች በርቆማለች፣
አስገቧት አልገባም አለች፣
ፀጉሯን አራት መቶ ገምቼላታለሁ፣
ደረቷን ሶስት መቶ ገምቼላታለሁ፣
ዳሌዋን መቶ አምሳ ገምቼላታለሁ፣
ከዳሌዋ በታች አልገመትኩላትም፣
በዐይን ያላዩት ነገር እምብዛ አያስዋሽም::
የጥጃ ማሰሪያው ስሙ ነው ጉንጉን፣
እኔ ከወደድኳት ዝንጀሮም ትሁን::
አንቺም ሂጂ ሂጂ ወደ ነጫጮቹ፣
አንቺም ሂጂ ሂጂ ወደ ፈረንጆቹ፣
ለኛም እግዜር አለን ለጥቋቁሮቹ::
አሁን ምን ያደርጋል አሜሪካን ቢሉ፣
አሁን ምን ያደርጋል ጅዳ ጅዳ ቢሉ፣
መርካቶም ጅዳ ነው ጠንክረው ከሰሩ፣
ፒያሳም ጅዳ ነው ጠንክረው ከሰሩ::
የታለች በር ቆማለች፣
አስገቧት አልገባም አለች::
ድሪውንም ሸጪው ፈቅጄልሻለሁ፣
ጠልሰሙንም ሸጪው ግዴለም ብያለሁ፣
የእጅ አምባሩን ሸጪው ፈቅጄልሻለሁ፣
እግር መስቀሉን ተይ እቃወመዋለሁ::
አዝማች
አባትሽ ባጥር ላይ የወረወሩኝ፣
እናትሽ በሰፌድ ዐይን አይኔን ያሉኝ፣
ወንድምሽ በሽጉጥ ተኩሶ ሳተኝ፣
አያትሽ በምርኩዝ አንዴ ዠለጡኝ፣
ወደል ውሻ አይደለሁ ሊጥ አልደፋሁኝ፣
አንቺን አንቺን ስል ነው የተገኘሁኝ::
የታለች በር ቆማለች፣
አስገቧት አልገባም አለች::

ኧረ እናንተ ሰዎች ጉራጌን ውደዱ

ጉራጌ ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

ማን በሰራው ክትፎ ትዘንጣላችሁ፣

ማን ባፈራው ክትፎ ትዘንጣላችሁ::

ኧረ እናንተ ሰዎች ካማራ ውደዱ

ካማራ ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

ጉች ጉች ያለ ጡት ትራስ ካማራችሁ፣

የዶሮ ፍትፍቱን መብላት ካማራችሁ::

ኧረ እናንተ ሰዎች ኦሮሞ ውደዱ

ኦሮሞ ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

ወርቅና ወርቅ ልጅ ማግኘት ካማራችሁ፣

ወርቅና ወርቅ ልጅ ማየት ካማራችሁ::

ኧረ እናንተ ሰዎች ከትግራ ውደዱ

ከትግራይ ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

የስንዴ አምባሻውን መብላት ካማራችሁ፣

የቴስታውን ነገር ጥንቃቄ አርጋችሁ::

ከሁሉም ከሁሉም ሀገሬን ውደዱ

ኢትዮጵያን ውደዱ እኔ ልንገራችሁ፣

ማማር በሀገር ላይ መሆኑን አውቃችሁ፣

መኩራት በሀገር ላይ መሆኑን አውቃችሁ::

ኢትዮጵያን ውደዱ እኔ ልንገራችሁ::

ድምፃዊ ይሁኔ በላይ

ግጥም ይሁኔ በላይ

1982 ዓ.ም

5. ዝምታ

እንዲያው ዝምታ ነው ዝም ይሻላል፣

ሁሌ በእንጉርጉሮ በትካዜ ስብሰለሰል፣

ሲያነደው ሲያከስለው በሆዴ ውስጥ ይብሰል፣

ምንስ ሰሚ ላገኝ ዋይ አንጀቴ ሲቃጠል::

የኔ ዓለም ውሎና አዳርሽን ጆሮዬ እየሰማው፣

ልቤን እያደማው፣

የኔ ዓለም ይሁን ብዬ ተውኩት አይቼ እንዳላየሁ፣

ሰምቼ እንዳልሰማሁ::

የኔ ዓለም እምነቴን ዘርቼ ባንቺ ስመካብሽ፣

ቃልሽን አፈረሽ::

የኔ ዓለም ሁሉን በዝምታ በመቻል አለፍኩት፣

ልብሽን ታዘብኩት::

ልቤን ሰጥቻት፣

እሷስ ልብ የላት::

ባይኔ እያየሁት ታዝቤ አለፍኩት::

ዝምታ ወርቅ ነው፣

ሆድ ይፍጀው፣ በደልን መቻል ነው::

የኔ ዓለም ዝናብ እንኳ ባቅሙ እንደሰው ሆነና፣

ወረት ተማረና፣

የኔ ዓለም ዛፍ ባለበት ጣለ በረሃ ጠላና፣

ማጣትን አየና::

የኔ ዓለም እንኳን ሰው ግብዙ ጊዜ ሚለውጠው፣

ሲያገኝ የሚርቀው፣

የኔ ዓለም ጀምበርም ከመሸ መጥለቋን አትተው፣

አትገኝ ከስፍራው::

ክፉ ደጉን አየሁት፣

አቤት ስንቱን ታዘብኩት፣

ልቤን ሰጥቻት፣
እሷ ልብ የላት።

ድምፃዊ፥ ፀሐይ ዮሐንስ
ግጥም፥ ተመስገን ተካ
1982 ዓ.ም.

### 6. ሁሉም ቢተባበር

መተዛዘን ቢኖር መተሳሰብ ቢኖር
መረዳዳት ቢኖር ሁሉም ቢተባበር
ሰው ለሰው ቢፋቀር ሁሉም ቢተባበር
የት ይደረስ ነበር፣
ቢጥር፣
የት ይደረስ ነበር፣
ሁሉም ቢፈቃቀር በመልካም መንፈሱ፣
ክፋት ምቀኝነት የትም በደረሱ፣
መጠፋፋት ቢቀር በተንኮል በሀሜት፣
ሁሉም ቢደጋገፍ በእውነተኛ ስሜት
ሰው በሰው ባይገባ ባያጋጭም ነገር፣
ሁሉም ቀና ቢያስብ ሁሉም ቢተዛዘን፣
ማን ኧረ ማን ይደርስብን ነበር።
ቢማማር ቢረዳዳ ሁሉም በአንድነት(4x)
ያም ያም ቢተባበር ድህነት ባልነበር፣
ያም ያም ቢተባበር የት ይደረስ ነበር።
አዝማች
ሁሉም ቢንቀሳቀስ ቢጣጣር እንደአቅሙ፣
በስራ ነበረ ሀገርን መጥቀሙ፣
ቢሰራ ቢደክም ሁሉም ሰው ቢተጋ፣
አምላክ ችሮን ነበር የተፈጥሮን ጸጋ።
በዚች ቅመም መሬት በዚች በለም መሬት፣
ሁሉም ቢሰራበት ሁሉም ቢወዳደር፣
ማን ኧረ ማን ይደርስብን ነበር።
ቢጣጣር ቢረዳዳ ሁሉም በአንድነት(4x)
ያም ያም ቢተባበር መጠቃት ባልነበር፣
ያም ያም ቢተባበር የት ይደረስ ነበር።
አዝማች
ሁሉም ቢተማመን በሙያው በእውቀቱ፣
ስራ ባህል ቢሆን እንደ ጀግንነቱ፣
ቢጥር ቢፎካከር በልማት ጎዳና፣
ሁሉም ቢሰራ ነው የእድገት ብልጽግና፣
እኛው ብንስማማ እኛው ብንፋቀር፣
የለፋ ቢወደድ የሰራ ቢከበር፣
ማን ኧረ ማን ይደርስብን ነበር።
ቢጣጣር ቢረዳዳ ሁሉም በአንድነት፣
ቢማማር ቢረዳዳ ሁሉም በአንድነት፣
ቢፋቀር ቢረዳዳ ሁሉም በአንድነት፣
ቢታገስ ቢበረታ ቢጥር በአንድነት፣
ያም ያም ቢተባበር ድህነት ባልነበር፣
ያም ያም ቢተባበር እርዛት ባልነበር፣
ያም ያም ቢተባበር የት ይደረስ ነበር።

ድምፃዊያን፡- አረጋኸኝ ወራሽ፣ ፀጋዬ እሸቱና ነዋይ ደበበ
1983 ዓ.ም.

### 7. እውነት ትኖራለች

ሰው ምላሱ ታስሮ ሥጋው ቢቀበርም፣
ደግም ሆነ ክፉ ሃቅ
አይሸፈንም...አይሸፈንም።

ድምጻዊ፡-- ጸጋዬ እሸቱ

ግጥም፡- ግሩም ኃይሌ

1982 ዓ.ም.

መሬቱ አይናገር አፍ የለው እንደ ሰው፣
ደግ አይል ክፉ አይል በአፈሩ ሲያለብሰው፣
ሞት ቢጋርደውም በመቃብር ጎራ፣
አይቀርም ተዳፍኖ የሰው መልካም ስራ፡፡
በሽፍጠኛ ጭጋግ በሃሰት ዳመና፣
አትሠነብትም ሃቅ ተሸፍና...!
የሰው ልጅ ባይቆይም ዘላለም በምድር ላይ፣
እውነት ትኖራለች ከመቃብር በላይ፡፡
ሆድን እንደ ሳጥን ብናየው ተከፍቶ፣
በውስጡ ያዘለው አያልቅም ተወርቶ፣
ስንት አለ በምድር ላይ ቃልአባይ መሰሪ፣
ልቡን እያሸሸ በሃሰት መስካሪ፡፡
አፈር ለብሳ አትቀርም በሞት ተደብቃ፣
እውነትም ጊዜ አላት ትወጣለች ደምቃ፡፡
ድፍርስና ንጋት እያደር ይጠራል፣
ይዋል ይደር እንጂ ቀን ይመሰክራል፡፡
ሰው ምላሱ ታስሮ ሥጋው
ቢቀበርም...ቢቀበርም፣
ደግም ሆነ ክፉ ሃቅ
አይሸፈንም...አይሸፈንም፣
የመከራው ጽናት አወይ የሰው ፍዳ፣
በቁመናው ተባይ ሲሞት የምስጥ የምስጥ
ራት፡፡
የልቡን ሳያገኝ ሃሳቡ ሳይሞላ፣
ቀን ሲጥለው ያልፋል እንደ ዋርካ ጥላ፡፡
ፈራሹ ሰውነት በሕይወት ባይኖርም፣
ይዘገያል እንጂ ሞት እውነት አይሽርም፡፡
ታሪክና ሙያ ተለባብሶ አይቀርም፣
ብቻ እውነት ስራ ስም አይቀበርም(5x)

ሲቀብር የሚኖር፡፡

## ለ. የለውጥ ጊዜ ዘፈኖች ግጥሞች

### 1. ጉንፋን

የጥንቱ ህመሜ ያምናው እንፍሎይንዛ፣
ሊለቀኝ ነው መሰል ዘንድሮ እንደዋዛ፡፡
አሰልስሎ አንጀቴን እስኪሰበር ቅስሜ፣
ዘንድሮ ለቀቀኝ ያ ጉንፋን ህመሜ፣
በሽታው ልክስክስ የሚይዘው መርጦ፣
ዘንድሮ ተገኘ ስንቱን ግጦግጦ፣
ዘንድሮ ተገኘ የስንቱን ላብ መጦ፡፡

አዝማች

ሀኪም አላገኘው ህመሙ አልተለካ(2x)፣
የህዝቡ በሽታ ጉንፋን ኖሯል ለካ፣
ያ ተስቦ ጉንፋን ደግሞ እንዳይስፋፋ፣
ያ ደም መጣጭ ጉንፋን ደግሞ እንዳይስፋፋ፣
ተነስ የሀገሬ ሰው በአንድነት እናጥፋ፣
ተነስ የሀገሬ ሰው በህብረት እናጥፋ፡፡

አዝማች

ወደ ፈረንጅ ሀገር ገንዘብ አከማችቶ፣
ወደ ሌላ ቦታ ገንዘብ አከማችቶ፣
ለፍቶ ያገኘውን ለመብላት ተዝናንቶ፣
ስንቱን በቁም ቀብሮት የስንቱን ደም ልሶ፣
ሊሄድ ሲል ተያዘ ጉንፋን ተግበስብሶ፣
ሊሄድ ሲል ተገኘ ጉንፋን ተግበስብሶ፡፡

ህዝቡም ወታደሩ ባያንጎራጉር፣
ህዝቡም ወታደሩ ባይተባበር፣
ጉንፋን ስንቱን ነበር

መጥፋት አትጠፋም ትኖራለህ ለስም፣
ጉንፋን ግን ደህና ሁን ዳግም አትመለስም፡፡
አይመልስህ እንጅ ከተመለስክማ፣
ይሄን ተናግሬ ምን ተረፍኩ እኔማ፡፡

ድምፃዊ፡- አያሌው መስፍን

ግጥም፡- አያሌው መስፍን

1967 ዓ.ም.

### 2. እነማን ይሆኑ

ጅምሩን ሲጨርስ የጦር ኃይላችን፣
ተምሮ ራሱን ሲያውቅ መላው ህዝባችን፣
እነማን ይሆኑ መሪዎቻችን፡፡
እነማን ይሆኑ እግዜር ያደላቸው፣
ደርጉን የሚተኩ ህዝባችን መርጧቸው፣
ሀገሬን በእውነት የሚያስተዳድሩ፣
ከህዝቡ ድርሻ ላይ የማይቆነጥሩ፣
በከንቱ ውዳሴ
በሰነፍ ሽንገላ፣
በየምናምኑ ኪሳቸው ያልሞላ፡፡

ድምፃዊ፥ ንጉሴ ወልደማርያም

ግጥም፡- ንጉሴ ወልደማርያም

1967 ዓ.ም.

### 3. ጠረጠርኩሽ

እፍ እፍ ያሉት ፍቅር ጭቅጭቅ አያጣም(2x)፣
ቸኮልሽብኝና ጠረጠርኩሽ በጣም፡፡

ምንም ብታስረጂኝ መውደድሽን በዘዴ፣

ምንም ብትገልጭልኝ ማፍቀርሽን በዘዴ፣

በጣም ቸኮልሽና ጠረጠረሽ ሆዴ።

እንቧይ ነሽ ሎሚ ነሽ ግለጪው ጠባይሽን፣

የእኔ ፍላጎቴ አይደለም መልክሽ፣

ንገሪኝ ፀባይሽን ልወቀው ልረዳ፣

አስረጂኝ ፀባይሽን ልወቀው ልረዳ፣

አንችን በማለቴ ብዙ እንዳልሰቃይ፣

ብዙ እንዳልጎዳ።

አዝማች

ካንጀቴም ብወድሽ በጣም ተንገብግቤ(2x)፣

ወደድኩህ አበዛሽ ጠረጠረሽ ልቤ።

ስትጀመሪ ጣፋጭ ቆይተሽ እንደሬት(2x)፣

ይህ እንዳይሆን ፈራሁ የፍቅርሽ አብነት።

መጀመሪያ ጣፋጭ ቆይተሽ መራራ፣

እንዳይሆን ፍቅራችን በጣም ልቤ ፈራ፣

እንዳይሆን ፍቅራችን በጣም ሆዴ ፈራ።

አዝማች

ካንጀቴም ብወድሽ በጣም ተንገብግቤ(2x)፣

ወደድኩህ አበዛሽ ጠረጠረሽ ልቤ።

ፍቅር የሚጣፍጠው ሲሆን ነው በለዛ፣

በጣም ፈራሽ ልቤ መንቀዥቀዥሽ በዛ፣

ፍቅር ቀልድ አይደለም ብዙ አታንቀዥቅዥው፣

ምን ቢያወሩት ከንቱ ቀዝቀዝ አድርገሽ ያዥው።

አዝማች

ካንጀቴም ብወድሽ በጣም ተንገብግቤ፣

ካንጀቴም ብወድሽ በጣም ተንገብግቤ፣

ጠረጠርኩሽ በጣም(6x)

ድምፃዊ:- አያሌው መስፍን

ግጥም:- አያሌው መስፍን

1967 ዓ.ም.

### 4. ምን ይዋጠው

ሀገሪቱን የጎተተ ወደ ኋላ፣

በደሀ ላብ የግል ሀብቱን የሚያሟላ፣

ሰራተኛን በስልጣኑ የሚያጉላላ፣

ምን ይዋጠው ከህዝብ ላይ ጉቦ የበላ፣

ይቀጣታል አይቀርለት

ይለቀማል ከየቤቱ፣ ከየወንዙ ከያለበት።

ለውጥ መጣ ያ ጉደኛ ፈረደበት፣

ለሰራው ግፍ ተለቃቅሞ ወደ እስር ቤት።

ፍርዱን ሰጥቶ በምላሱ ሰውን ወጊ፣

ምን ይዋጠው ያ ወሬኛ ያ አዋጊ፣

አሰሪና ሰራተኛን አራራቂ፣

በሹል ምላስ በቅቤ አፉ ወሬ አራቂ፣

ሆዱ ገዳይ ጥርሱ ሳቂ፣

ለማን ያውጋው ወዴት ይግባ፣ ወዴት ይሁን ያ ሰባቂ።

ለውጥ እያየ ቁና ወሬ የሚሰፍር፣

ከዐለቃው ጋር ተያይዞ ቅጣት ሰፈር።

በሰበካ ህዝቡን ገፎ ያራቆተ፣

ያገሩን ሀብት ወደ ኪሱ የከተተ፣

ስልጣን ይዞ አደራውን የዘነጋ፣

ወደፊትም በሰራው ግፍ አለው ዋጋ፣

የደሀን ደም ላብ የጠጣ፣

ወዴት ይግባ ምን ይዋጠው ለውጥ መጣ።
ህግ ሆነ እንጂ ፍርድ ሰጪ ሁሉን ነገር፣
ግፈኛውን እሳት ከቶ መጥበስ ነበር፣
ህግ ሆነ እንጂ ፍርድ ሰጪ ሁሉን ነገር፣
አጭበርባሪን እጁን ቆርጦ መጣል ነበር።
እንደኔ ሀሳብ ሁለት ቦታ መቁረጥ ነበር፣
(አዎ)
እንደናንተም ሌላ ሌላ ፍርድ ነበር፣
(አዎ)
እንደናንተም ብዙ ብዙ ሀሳብ ነበር፣
(አዎ)
እንደኔ ግን ቆርጦ ቆርጦ፣ ከትፎ ከትፎ፣ ጎርዶ ጎርዶ መጣል ነበር።

ድምፃዊ፥ ወጋየሁ ደግነቱ

ግጥም፥ ወጋየሁ ደግነቱ

1967 ዓ.ም.

### 5. ነበረ

ነበረ(6x)
በቅርብ እንደቀረ ነበረ።
ህግና ስርዓት ይጥፉ ግድ የለንም፣
ፍትህና እውነት የኛ ግድ አይደለም፣
የሚለው ስርዓት የፊውዱ ቡርዧው
በአንክሮ ሲታሰብ የሚያስገርም ነው።
በዚያ በግፍ ሰዓት በቅርብ በቀረው፣
ችሎታና እውቀት ዋጋ ባልኖረው።
አጥንት እንደ ዲግሪ ይቆጠር ነበረ፣
ይህም ዋጋ ኖሮት ብዙ ጊዜ አኖረ።
አዝማች
ዝሙትና ስካር ይደገስ ነበረ፣
በፍርድ ማንከራተት ይፈቀድ ነበረ፣
ጉቦና አድሎ በአዋጅ ሲወጣ፣
ትንሽ ሲቀረው ነው ይሄ ለውጥ የመጣ።
አዝማች
ሶሻሊስት፣ ኮሚኒስት ስማቸውን የጠራ፣
ወይም ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ያወራ፣
ይህም እንደጥፋት ያሳስር ነበረ፣
ያ ቀልደኛው ስርዓት በቅርብ እስከቀረ።
ነበረ ነበረ ነበረ፣
ነበረ ነበረ ነበረ፣
በቅርብ እስከቀረ ነበረ።

ድምፃዊ፥ ጥላሁን ገሠሠ

1967 ዓ.ም.

### 6. ዘንድሮ

እህህሀ
ዘንድሮ(3x)፣
የስንቱ ተወርቶ የስንቱ ተነግሮ።
ዘንድሮ።
ውሎ በማደሩ ተዋሃደንና፣
መጥፎ ከደህና ጋር ተማታብንና፣
ብዙ ዓመቶች አልፈው ዛሬ ነቃንና፣
ያስቀን ጀመረ ግራ ገባንና።
አዝማች
በዚያኛው ተገርመን ጥቂት ሳንቆይ፣
የዚህኛው መባስ አያስቅም ወይ?
ይሄ ሁሉ ነገር ስንት ዘመን ኖሮ፣
በጣም ያስገርማል ጉድ አየን ዘንድሮ።
አዝማች

ብዙ ዓመት በድብቅ ሲጓዝ ከረመና፣
ዘንድሮ ላይ ሲደርስ ሸክሙ አጋደለና፣
ተዝረክርኮ ወድቆ በግልጽ ብናየው፣
የዘንድሮን ነገር ዘንድሮ አወቅነው።
አዝማች

ድምፃዊ፥ ጥላሁን ገሠሠ

ግጥም፥ ተስፋዬ ለማ

1967 ዓ.ም.

## 7. ሀገሬ ኢትዮጵያ

ሀገሬ ኢትዮጵያ ለምለሚ አበባዬ፣
ሳይሽ እርግፍ እርግፍ ይል ነበር እንባዬ።
እንባዬ ደረቀ ምኞቴ ተሳካ፣
አንድነትም መሀል ውጤት አለ ለካ።
ድል አገኘሁ ዛሬ መሰንበት ጥሩ ነው፣
ከእንግዲህ ጭሰኛ የሚለኝ ሰው ማነው?
አዝማች
ስለዚህ አንድ ላይ በህብረት ተስማምተን፣
ኢትዮጵያ እንድትቀድም መስራት ነው ያለብን።
የህብረታችን እሸት ተንዠርጓል ዛላው፣
ጠንክረን መስራት ነው ማንም እንዳይበላው።
እንድከም እንስራ ላባችን ይንጠፍጠፍ፣
ድሉ የኛ ሆኗል በተሰራብን ግፍ።
ለእርሻም መተባበር ያስፈልጋል በጣም፣
እህል እህል ብንል በምኞት አይመጣም።
አንቺ የማታ ጀምበር እንድትደሰቺ፣
ዓለም ቁንጅናዋን ብታሳይሽ ላንቺ።

ድምፃዊ፥ ጥላሁን ገሠሠ

ግጥም፥ አስካለ ብርሃኔ

1967 ዓ.ም.

## 8. አንዱን ቀን

አንድ ቀን እያልኩኝ አንድ ቀን አለፈ፣
ሌላ አንድ ቀን ስል እሱም ቶሎ አለፈ፣
የኔ አንድ ቀን አያልፍ እድሜዬ ከነፈ።
ዛሬ ያልተሳካው ይሰራል አንዱን ቀን፣
በዚያ ቀንም ባይሆን አይጠፋም ሌላ ቀን፣
እያልኩ ስቆጥር ብዙውን በአንድ ቀን፣
ቀኑ ቀኖች ወልዶ ሊያልቅ ነው የኔም ቀን።
አዝማች
አንዱ ሁለት ሆኖ ሳምንቱም አለፈ፣
ሳምንት ተደምሮ ወደ ወር ከነፈ፣
ይሄ ሁሉ ሲሆን እላለሁ አንድ ቀን፣
አንዱ ቀን ቀን ወልዶ ተለወጠ ዘመን።
አዝማች
ባንዱ ቀን አንድ ቀን ሳይታወቅ ያልፍና፣
በሌላው ሌላ ቀን ድንገት ያዘግምና፣
አንዱ ብዙ ሆኖ ስንት ቀን አለፈ፣
ከአንዱ ቀን አንዱ ቀን ሌላም ቀን ተረፈ።
አዝማች

ድምፃዊ፥ ጥላሁን ገሠሠ

ግጥም፥ ተስፋዬ ለማ

1967 ዓ.ም.

## 9. ሰላም ለሁላችን

ፍቅር ከኛ እንዳይለየን፣
እንዲቃናልን ስራችን፣

መጨቃጨቅ ይወገድና፣

ሰላም ይሁን ለሁላችን።

ኑሮ ለሰው ልጆች በእውነት ቀላል ስላልሆነ ዋዛ፣

በሆነ ባልሆነው ይቅር ጭቅጭቃችን አይብዛ።

ንትርክ ንዝንዝ ካለ በኑሯችን መካከል፣

ወዳጃችንም ይርቃል ሀብትም ቢሆን ይሸሻል።

አዝማች

ገንዘብ ፍቅር ከሌለበት የማይጠቅም ከንቱ ነው፣

ለጊዜው ያስደስት እንጂ ሲረግፍ እንደ ጤዛ ነው።

በየተሰማራበት የሰው ልጅ እንደ ሙያው፣

ነጋዴውም ወደ ንግዱ ገበሬውም ወደ እርሻው።

አዝማች

ተሰማርቶ ውሎ ሰርቶ ተደስቶ ሚኖረው፣

ከመተዛዘን በስተቀር መጨቃጨቅ ሳይኖር ነው።

ሰላምና መፈቃቀር ከጠፋ ግን ከኛ ዘንድ፣

ህይወትም መሪር ይሆናል ኑሮም እኮ አይወደድ።

አዝማች

ድምፃዊ፥ ጥላሁን ገሠሠ

ግጥም፥ ተፈራ ካሳ

1967 ዓ.ም.

### 10.ችለን ማለፍ ጥሩ

በምድር ላይ መከራው ችግሩ፣

ቢበዛ ኑሮ ማስመረሩ፣

ሁሉንም ችለን ማለፍ ጥሩ።

ባለፈው ስንት ያነው ቀርቶ፣

ፍቅር በልባችን ተዘርቶ፣

በአንድነት ጉዞ ጀምረናል፣

የብርሃን ብልጭታን ይዘናል፣

ማንነታችንን አውቀናል።

አዝማች

ድፍርሱን አጥርተን ልንጠጣ፣

ጨለማን አልፈን ልንወጣ፣

ልንበላ በፍቅር ገበታ፣

ፅዋችንን ሞልተን በእርጋታ፣

ውይይት ጀመርን በፈገግታ።

አዝማች

መጨነቅ መጠበቡ ቀርቶ፣

መኖሩ ሰው ሰውን ፈርቶ፣

ተንኮልን ክፋትን አባሮ፣

ለአንድነት በአንድነት ተባብሮ፣

መስራት ነው ፍቅርን አክብሮ።

አዝማች

ባለፈው ስንት ያየነው ቀርቶ፣

ፍቅር በልባችን ተዘርቶ፣

በአንድነት ጉዞ ጀምረናል፣

የብርሃን ብልጭታ ይዘናል፣

ማንነታችንን አውቀናል።

ድምፃዊ፡- መሐሙድ አህመድ

1967 ዓ.ም.

### 11.ብድሩን ቀመሰው

ስጋዬን ጨርሶ አጥንቴን የላሰው፣

በሰፈረው ቁና ብድሩን ቀመሰው።

እድሜዬን ስገፋ በጨኸት በሮሮ፣

ስንቱን አሳለፍኩት አንገቴ ተቀብሮ፣

የእኩልነት መብቴን አገኘሁ በይፋ፣

አገኘሁ በይፋ

ኢትዮጵያ ትቅደም የኔ ህይወት ተስፋ፥

የኔ ህይወት ተስፋ

ጎንበስ ቀና እያልኩኝ ባይጠና ህመሜ፣

መስራት እችል ነበር እኔም እንዳቅሜ።

አዝማች

የምደክመው እኔ በላተኛው ሌላ፣

ጉዱ ተገለጠ የኋላ የኋላ፣

ራብ ያገረጣው ቆስሏል ሰውነቴ፣

ከእንግዲህ ላገግም ከቀረልኝ ሆዴ፣

ጎንበስ ቀና እያልኩኝ ባይጠና ህመሜ፣

መስራት እችል ነበር እኔም እንዳቅሜ።

አዝማች

ድምፃዊ፡- ከተማ እንደሻው

ግጥም፡- ከተማ እንደሻው

1967 ዓ.ም.

## 12.ጎህ ሲቀድ

ጎህ ሲቀድ ሲነጋ ለሊቱ፣

የለውጥ አየር ማሽተት አቤት ማስደሰቱ፣

ሞራልን አላሽቆ ያረገው በረዶ፣

ያ ጨለማው ጊዜ ፍርሀት ተወግዶ፣

በዚህ ንጋት ጮራ ህይወት በሚያድሰው፣

የታፈነው ሀይል ሲጮህ ህዝብን ቀሰቀሰው።

ጣኦት ልሁን ያለው በገዛ ወገኑ፣

ሲያብረከርክ ታየ አንበሳ ዝሆኑ፣

የቱ ነው መሻሻል የቱ ነው እድገቱ፣

ባጽም ሞልቶ ሲታይ የዳቦ ቅርጫቱ፣

በታህሳስ ተስፋ አጭተን የካቲት ሰርጋችን፣

ቢዘገይም ሰምሯል መች ይሆን በዓላችን።

በሰሜን ተራራ በዝቋላ ጋራ፣

በሰላም ተንፍሷል ያ እሳተ-ጎመራ፣

እምነት ማጣት ላገር አውዳሚ ቦምብ ነው፣

ለውጡ ለኢትዮጵያችን ተስፋ ትንሳኤ ነው።

ነፍሳችን ላታጣ ጽድቅ ወይም ኩነኔ፣

ለውጡ ጉዞ ፍታሀት ሆኖ አድክሞ ወኔ፣

እናንት የለውጥ ሀይሎች ይጠንክር ክንዳችሁ፣

ህዝባችሁ ተባብሯል ምሩን ባላማችሁ።

አዝማች

ድምጻዊ፡- መልካሙ ተበጀ

ግጥም፥ መርዓዊ ስጦት

1966 ዓ.ም.

## 13.ቀባሪ አጥቶ ሬሳ

በወሎ በትግሬ በባሌ በሀረር፣

ቀባሪ አጥቶ ሬሳ በሬሳ ሲከመር፣

በረሀብ አለንጋ ሲጋረፍ ፍጥረቱ፣

መረዳዳት እንጂ አይጠቅምም ማየቱ፣

ምድርሽ የሰጡትን ሁሉን ይቀበላል፣

ተፈጥሮ ያለማው ያበቅላል ያፈራል፣

ሀብት እያለሽ ንዋይ ለዘር ዘርሽ በቂ፣

አትሆኚም ከእንግዲህ እርዳታ ጠያቂ።

ለተራበው ወገን ለጎዳው መከራ፣

ያለንን አወጥተን እናብላው እንጆራ።

ድምጻዊ፡- ከተማ እንደሻው

ግጥም፡ ጌታቸው የሻው

1967 ዓ.ም.

**14.ጥሩ ወርቅ**

አልማዝን አይቼ አልማዝን ሳያት፣

ሶስተኛዋ አልማዝ ብትመጣ ድንገት፣

ሁለቱን አልማዞች ስላስረሳችኝ፣

ምርጫዬ በምርጫ ተበላሸብኝ፡፡

ሶስቱንም አልማዞች ባያቸው ባያቸው፣

እቺም ያቺም አልማዝ ሁሉም አልማዝ ናቸው፡፡

አልማዝን ከአልማዝ መምረጥ ቸገረኝ፣

እስኪ አንዴት ይሻላል ምክር ለግሱኝ፣

ሰው የተቸገረው በሌላ ሌላ ነው፣

እኔን የቸገረኝ የአልማዞች ምርጫ ነው፡፡

በአልምዝ መቸገሬ አይደለም ቅንጦት፣

ይቀልድ ይሆናል ያልደረሰበት፤

ከአልማዝ መሀል ገብቶ በአልማዝ መቸገር፣

ለሰሚው ግራ ነው የሚያደናግር፣

የሶስስት አልማዝ ምርጫ ስላስጨነቀኝ፣

ጥሩወርቅ ተሽላ ስለታየችኝ፣

ሄድኩኝ ከጥሩወርቅ አልማዞቹን ትቼ፣

አላዋጣም ቢለኝ ነገሩን ገምቼ፡፡

ድምጻዊ፡- ጥላሁን ገሠሠ

ግጥም፡ ተስፋዬ ለማ

1967 ዓ.ም.

**15.ሎሚ ተራ ተራ**

ሎሚ ተራ ተራ ሎሚ ተራ ተራ፣

የማምዬን ነገር ጎረቤቴ አደራ፡፡

እናቴ ካንድ አባት አስራ አራት ወልዳለች፣

ሞግዚትም እናትም ሆና አሳድጋለች፣

ጧሪ በማጣቷ አሁን ታለቅሳለች፡፡

አባባም ተግዞ ወህኒ ገብቷል አሉ፣

ጋሽዬም ጤና አጥቶ ካገር ወጥቷል አሉ፣

አብዬም ሸፍቷል አምጿል ይላሉ፣

አዝማች

ወራሽ ነኝ ይል ጀመር አንዳንድ ዲቃላ፣

ካማካሪው ጋራ ተሻርኮ ሊበላ፣

እናቴን አድርጓት ሞኝና ተላላ፡፡

ታገኟታላችሁ ቁልቁል አቀርቅራ፣

የፊጫይ ስትፈጭ የጋጋሪ ጋግራ፣

ከገበያው ማዶ ከረባዳው ስፍራ፡፡

አዝማች

ድምፃዊ፡ ጠለላ ከበደ

ግጥም፡ ጌታቸው ደባልቄ

1967 ዓ.ም.

**16.ስንቱን ጉድ ቻለ**

ሰምቶ ዝም አለ ጆሮዬ፣

አይቶ ዝመ አለ ይህ ዐይኔ፣

ሆድ ከታገሰስ ከቻለ፣

ትግስትን ያህል ምን አለ፡፡

ሰዉ በወደደዉ ይገድፋል፣

ሰዉ ባፈቀረዉ ይከንፋል፣

ሆድ ከታገሰስ ከቻለ፣

መቻልን ያህል ምን አለ?

ያም ለኔ ያም ለኔ እኔም ለኔ ስላት፣ እኔም ለኔ ስላት፣

ቆንጆ ከሷ ወዲያ የሌለ መሰላት፣ የሌለ መሰላት፣

አፍቃሪዋ በዝቶ ልቧን ስለነሳት፣ ልቧን ስለነሳት፣

ፈረሰኛ ወስዶ እግረኛ መለሳት፣ እግረኛ መለሳት።

ገለል በሉ፣ ፈረሱን አስጭኖ፣

ገለል በሉ፣ ጦር እየሰበቀ፣

ገለል በሉ፣ ስንቱ ጎበዝ ጀግና፣

ገለል በሉ፣ በሷ ስም አለቀ።

እሷን እንዳለ ሆዴ፣ ፍቅር እንዳለ፣ መዉደድ እንዳለ፣

ጭንቅ እንዳለ ሆዴ፣ ሲያስባት ዋለ፣ ሲያስባት ዋለ፣

ብግን እንዳለ ሆዴ፣ ቅጥል እንዳለ፣ ክፍት እንዳለ፣

ጥብብ እንዳለ ሆዴ፣ ስንቱን ጉድ ቻለ፣ ስንቱን ጉድ ቻለ።

አዝማች

ነዶ ነዶ እስከሚያልቅ ሆዴ ሁሉን ያልፋል፣ ሆዴ ሁሉን

ያልፋል፣

ጭስ የጨሰበት ቤት እሳት መች ይጠፋል፣ እሳት መች

ይጠፋል፣

ከጥንት ጀምሮ ስናየዉ የኖርነዉ፣ ስናየዉ የኖርነዉ፣

ሲነድ ሲቃጠል የሚስቅ እሳት ነዉ፣ የሚስቅ እሳት ነዉ።

ገለል በሉ፣ ዳቦዉም ይቆረስ፣

ገለል በሉ፣ እስኪ ስም ይዉጣለት፣

ገለል በሉ፣ ስንቱን አነደድሽዉ፣

ገለል ገለል፣ አፋጀሽን እንበላት።

ችሎ ዝም አለ ሆዴ፣ ሰምቶ ዝም አለ፣ አይቶ ዝም አለ፣

ችሎ ዝም አለ ሆዴ፣ ያልፋል እያለ፣ ያልፋል እያለ፣

ይሁን እያለ ሆዴ፣ ይቅር እያለ ክፍት እያለ፣

ይሁን እያለ ሆዴ፣ ስንቱን ጉድ ቻለ፣

ስንቱን ጉድ ቻለዉ፣ ስንቱን ጉድ ቻለዉ፣

ስንቱን ጉድ ቻለ ሆዴ፣ ስንቱን ጉድ ቻለዉ።

ድምፃዊ፡- ቴዎድሮስ ታደሰ

ግጥም፡- ተመስገን ተካ

1984 ዓ.ም.

## 17.ሕልምሽ ቅዠት ነው

አመጣው ፍቅር ፍርጃውን፣

እኔ እንጃልኝ መሰንበቻውን፣

እኔ እንጃከልኝ መሰንበቻውን፣

ቀልዱን ተይ የቀን ቅዠቱን፣

አብርጂው ነገር እሳቱን፣

ያምጣልን እስቲ ምህረቱን።

እኔን ሲኦል ብለሽ ጓዝሽን ጠቅልለሽ፣ ገነት ገባሁ ያልሽው፣

ከኔ ተለይተሽ ስትሄጂ ከመንገድ፣ ማር አገኘሁ ያልሽው፣

ወለል ካለው ሜዳ ወርቅ አልማዝ ልትበይ እንቁ አገኘሁ ያልሽው፣

በገሀድ አልታየም ያንቺስ ህልም አልሆነም አንቺ እንደፈታሽው።

ልፍታልሽ እኔ ህልምሽ ቅዠት ነው፣

ያሰብሽው ሁሉ እንቆቅልሽው ነው፣

ገነቱም ሲኦል ሜዳው ገደል ነው፣

አልማዙም ነሃስ ማሩም ሬት ነው::

እኔማ ከሃዲ ብዬ አልሰይምሽም፣

ዘንድሮስ ጠላሽኝ ብዬ ስም አልሰጥሽም::

አጀብ ነው ኮከብ ቆጣሪው አዋቂው በዝቶ፣

ማን ይመን? ማን ይምጣ? በዳይ ተበዳይ ግራ ተጋብቶ::

አመጠው ፍቅር ፍርጃውን፣

እኔ እንዳከልኝ መሰንበቻውን(2x)፣

ቀልዱን ተይ የቀን ቅዠቱን፣

አብርጂው ነገር እሳቱን፣

ያምጣልን እስቲ ምህረቱን::

እምባሽ ካይንሽ ሽፋን ከጉንጭሽ ካይን ዳር ሲታፈስ ሲቀዳ፣

ብያኔው ተዛባ እውነት ነው ተባለ አረግሽን ባለእዳ::

ፍርዱ ደፈራርሶ ጉሽ ሆኖ ባይጠራ ቅራሪው ባይቀርም፣

በሰፈሩት ቁና እያደር አንድ ቀን መሰፈር አይቀርም::

እኛው ተማምን ፈር ካላስያዝነው፣

ስንጥር ኖረን ካፈራረስነው::

ቅዠቱን ሁሉ እውን ነው ካልነው፣

ምኑን ከረምነው?

ምኑን ጠፋነው?

እኔማ ብካሰስሽም አላውቅም ፍርዴን፣

ልቻለው ያቃጥለው እንጂ ይብላው ሆድ ሆዴን::

እንግዲህ በዳይ ተበዳይ እስከሚታወቅ፣

ይበቃል በሆድ ቂም ይዞ ማፍቀር መታረቅ::

እንግዲህ ሳንተማመን እንዴት እንዝለቅ፣

ዘንድሮስ ስንተዋወቅ አንተላለቅ::

እኔማ በብቸኝነት ልኑር ያለ ሰው፣

ዘንድሮስ፣ ዘንድሮስ እሱ ያመጣውን እሱ ይመልሰው(2x)::

ድምፃዊ፦ ቴዎድሮስ ታደሰ

ግጥም፦ ተመስገን ተካ

1984 ዓ.ም.

### 18.ሴትን በሴት

ስትሞሽር ከርማ በፍቅር ዳስ፣ በመውደድ ዳስ(2x)፣

ወጣች ጫጉላ ረግጣ፣ ወጣች ጫጉላ ረግጣ፣

ሆሆሆ ያች ቀበጥባጣ::

ለመርሳት ብሞክር ዘዴ አጣሁላት፣

(ተቀባዮች- እሾህን በሾህ ነው ሴትን በሴት)

እንዳቃጠለችኝ በምን ላንድዳት?

(እሳትን በሳት ነው ሰው ተካባት)

ጠቁሙኝ ዋግምቱን ከሆዴ ላውጣት፣

(እሾህን በሾህ ነው፣ ሴትን በሴት)

በምን ልበቀላት ምላሿን ልስጣት?

(እሳትን በሳት ነው፥ ሰው ተካባት)

ማን በልጡብሽ ከኔ ከማን እልፍኝ ገባሽ(2x)?

ማነው አቀማጥሎ ያኮራሽ ያደራሽ(2x)?

ፍቅርን እንደ ቅርጫ እያቀራመትሽው(2x)፣

ቅብጥብጥ ልብሽን ለስንቱ መገብሽው?(2x)

ቀድሞ መጠንቀቅ ሰው ሲጠረጥር፣

ከገንፎ መሃል አይጠፋም ስንጥር፣

የእረኛ ወንጭፍ ሁሉን ቢያለምድም፣

እርግብና ቆቅ አይላመድም።
የፍቅር ፀበል ፅዋው ሲጠጣ፣
እንዲህ አይደለም ጎጆ ሲወጣ።
ዋ!
ወገኛ፥ መስሎሽ ነው እንጂ ዋዘኛ፣
ፌዘኛ፥ ደሞ አንቺን ብሎ ሰርገኛ፣
ወትሮም አድሏዊ ዳኛ፣
ይላል የዶሮ ሻኛ፣
ማቀራረቡን እንጂ መገንጠል አናውቅ እኛ።
ወገኛ፥ መስሎሽ ነው እንጂ ዋዘኛ፣
ፌዘኛ፥ ደሞ አንቺን ብሎ ሰርገኛ፣
ወትሮም አድሏዊ ዳኛ፣
ይላል የዶሮ ሻኛ፣
ማቀራረቡን እንጂ መለየት አናውቅ እኛ።
አዝማች
ለብዙ ሳስባት እንደናት ሳምናት፣
(አትለማመጣት አትለምናት)
ወጣች ከጉያዬ የኔናት ስላት፣
(መላ ፈልግላት ሰው ተካባት)
እኔን የሚያስጠላ ምን አቀመሷት?
(አትለማመጣት አትለምናት)
ሞት መስሎ እየታየኝ ከሷ መለየት፣
(መላ ፈልግላት ሰው ተካባት)
ሂጂ በመሰለሽ እኔ ባንቺ አልፈርድም፣
ላም ነጂዋን እንጂ ጌታዋን አታውቅም(2x)፣
አምባር ቀለበቱ ቢጠፋ ማተብሽ፣
ይታወቅ እንግዲህ ባል አልቦ መሆንሽ(2x)።
አዛኝ ቅቤ አንጓች ስታባብለኝ፣
አንድ ነን ብላ እዩዋት ስትሸጠኝ።
ደስታና ሃዘን ሲፈራረቁ፣
ወደው አይስቁ ካልተጨነቁ።
አወይ መሰንበት እድሜ ማፅረጉ፣
ስንቱን አሳየን ወይ መኖር ደጉ።
ዋ!
ወገኛ፥ መስሎሽ ነው እንጂ ዋዘኛ፣
ፌዘኛ፥ ደሞ አንቺን ብሎ ሰርገኛ፣
ወትሮም አድሏዊ ዳኛ፣
ይላል የዶሮ ሻኛ፣
ማቀራረቡን እንጂ መገንጠል አናውቅ እኛ።
መለየት አናውቅ እኛ(3x)።

ድምፃዊ፦ አስናቀ ገብረየስ

ግጥም፦ ተመስገን ተካ

1984 ዓ.ም.

### 19.ያሁኑ ይባስ

ተገን የለኝ እኔስ ባይተዋር ነኝ፣
የለኝ መፅናኛ፣
ወገን የለኝ ምን ጠፋ የሚለኝ፣
ሆኜ ብቸኛ።
ወዴት ነሽ ሙና ያንቺው ብሶተኛ፣
ያገሩ ጎዳና ጠፍቶብኛልና፣
አዋዩኝ ሙና ደባብሺኝ አትርሺኝ፣
ምንጊዜም አስታውሽኝ፣
እንደ ወፍ በረረች ፈጠነች ከነፈች፣
ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።
ተይ ተመለሽ በሏት አጥፍቼ እንደው ልካስ፣
ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።

ይሄ ሁሉ ሩጫ ወዴት ለመድረስ፣
ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።
እንዲህ ቀላል ነው ወይ የካቡትን ማፍረስ፣
ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።
ለምን አላዝን ለምን አይከፋኝ፣
የኑሮው ቅያስ ዘዴው ሲጠፋኝ፣
ጨዋታ አይጥመኝ አልሆን እንደሰው፣
ጎኔን ትዝታ እያፈረሰው፣
እንደ ኩታ ሰሪ ጭንቀት ሲያዳውረኝ፣
እኔን እንደ ሽክላ እየሰባበረኝ፣
ቀረብኩት ወዳጅ ለክፋት ሲድረኝ፣
ቅን እንዳልሆንኩለት ስቆ እየገደለኝ፥
አይ የኔ ድካም አይ የኔ ልፋት፣
አንገበገበኝ እንደ ግር ሳት።
የኔስ የጉድ ነው እንዲያው የጉድ ነው፣
ጢት ማታ እዬዬ እንዲያው ልፋት ነው።
ለማን ላዋየው የልቤን የሆዴን፣
እኔስ ጉዳቴን፣
ትዝታሽማ ሲያበረኝ ሲያከንፈኝ፣
እዬዬ አተረፍኩኝ።
እረጋ በይ በሏት ምነው መገስገሷ፣
ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።
ጠልፎ እንዳያስቀራት የገዛ ቀሚሷ፣
ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።
እንዳቀራረቧ እንደ አለሳለሷ፣
ያሁኑ ይባስ ደሞ ያሁኑ ይባስ።
ማን ነበር ለሰው ልጅ ተቆርቋሪ እንደሷ።
አንቺ ባለዘመድ መካሪሽ ብዙ ነው፣
የኔን ልብ ያስከፋው ብቸኝነቱ ነው፣
መለየት ፈርዶብኝ በማጣት ብቀጣም፣
እኔን ያለልኝ እለት አስታማሚ አላጣም።

ድምፃዊ፥ ተፈራ ነጋሽ

ግጥም፥ ዝምበላቸው ድፋቅ

1984 ዓ.ም.

**ሐ. የለውጥ ማግስት የአማርኛ ዘፈኖች ግጥሞች**

**1. ጊዜ ደጉ ነገር**

ጊዜ ደጉ ነገር ህይወቴ፣
ጊዜ ደጉ ነገር ህይወቴ፣
ያሳየኝ ሁሉን መስታወቴ፣
ያሳየኝ ሁሉን መስታወቴ።
ወይ ጊዜ ሁሉን ለይቶ የሚያሳይ፣
የአንድነት የፍቅር የጋራ ሲሳይ፣
ህብረትን አወቀ ሁሉም በዘርፉ፣
የሰላም መንገድ ህይወት ሆነ ትርፉ።
ወይ ጊዜ ሁሉን ለይቶ የሚያሳይ፣
የአንድነት የፍቅር የጋራ ሲሳይ፣
ህብረትን አወቀ ሁሉም በዘርፉ፣
የሰላም መንገድ ህይወት ሆነ ትርፉ።
አዝማች
ፍቅሬም በልቤ ውስጥ ገብታ አድሳ፡ት፣
ልቤን ደስ አሰኘች አለች ደስ ብሏት፣
የጋራ መሰረት የጋራ ደስታ፣
ደግሞ ልንኖር አለች እፎይታ።
አዝማች
የህይወት መንሰላል መወጣጫዬ፣
አደረሰን ምኞት ሆነ አቅጣጫዬ፣
የህብረት አንድነት ፍሰሃ ሆኖን፣
ጊዜ ደጉ ነገር አሳየን ሁሉን፣
የህይወት መንሰላል መወጣጫዬ፣
አደረሰን ምኞት ሆነ አቅጣጫዬ፣
የህብረት አንድነት ፍሰሃ ሆኖን፣
ጊዜ ደጉ ነገር አሳየን ሁሉን።

ድምፃዊ፡- መሐሙድ አህመድ

ግጥም፡- ያልታወቀ

1968 ዓ.ም.

**2. ንጋት**

ነጋ ነጋ መስከረም ጠባ፣
የጸደይ አደይ ታዬ አበባ፣
ያብዮቱን ደውል አስተጋባ፣
ያ ጨለማ ወራት ድጡ ማጡ አለፈ፣
መስከረም ሁለት ቀን ጉሙ ተገፈፈ።
ያ የጭንቁ ዘመን ጭጋጉ ለቀቀ፣
መስከረም ሁለት ቀን አደይ ፈነጠቀ፣
አሰቃይቶን ነበር ጨብጦ አኮራምቶ፣
ሄደ ያ ደመና ጠፈጠፉን ትቶ።
እንኳን አለፈ እንጂ ጨለማው ክረምቱ፣
ለጠፈጠፉማ ቀላል ነው ብልሀቱ።
ሳሩ ከደጃችን ብልሀቱ በእጃችን፣
ከእንግዲህ ጠፈጠፍ ውጣ ከቤታችን፣
ሰርጎ ገብ ጠፈጠፍ የጎጂችን ጠሩ፣
ነገ ዛሬ ሳንል ይደፈን ሽንቁሩ።
ክረምቱስ ካለፈ ውሎ አድሮ ነበረ፣
ጠፈጠፉ ጎዳን አየበረበረ፣
ሰርጎ እየገባ ቤታችንን የጎዳው፣
ይደፈን በቶሎ የጠፈጠፍ መግቢያው።
ጠፈጠፉ ጠፍቶ እንዲሟሟቅ ቤቱ፣

አዲሱ እልፍኛችን ይጥበቅ መሰረቱ፣

የጸደይን ጸሀይ እንደልብ ለመሞቅ፣

የጠፈጠፉን ምንጭ ኩሬውን ነው ማድረቅ፡፡

ድምጻዊ፡- ቀለመወርቅ ደበበ

ግጥም፥ ቀለመወርቅ ደበበ

1969 ዓ.ም.

### 3. ኧረ ተይ

ኧረ ተይ ለሁሉም ሀገር የጋራ ነው፣

አብረን ብናስብበት ምነው፣

እባክሽ በፍቅር እንያዘው ተስማምተን፣

የማይዘልቅ አምባጓሮ ትተን፡፡

ትዝብት ነው ትርፉ በኋላ በሀገር ቀልድ የለም እወቂ፣

አስቢበትና የሚበጅ ነገር አትርፊ ተጠንቀቂ፣

ከማይሆን ሀሳብ ተጠበቂ፣

ይልቅ በአንድነት ተስማምተን እንያያዝና እጅ ለእጅ፣

ኩኩሉ ጨዋታ አናርገው ቀልደን በከንቱ ጊዜ አንፍጅ፣

ይሻላል ፍቅር እኮ ቢደረጅ፡፡

አዝማች

ዘለቄታም የለው አያምርም የማይዘልቅ ሀሳብ ይቅርብሽ፣

የማይሆን አይሆንም ልንገርሽ በተንኮል ከሚያስበልጥሽ፣

ይኸው ነው የሚያዛልቅሽ፡፡

የሚሆን ይሆናል ብትሰሚኝ ልባችን ከፀና በፍቅር፣

ስለዚህ አስቢበት በጣም በተንኮል መለያየት ይቅር፣

በሰላም ከመኖር በስተቀር፡፡

አዝማች

የዓለም ሰላም ምልክቱ ፍቅር ስለሆነ በምድር ላይ፣

ሁሉንም ለኛ ብለን ይዘን ተባብረን እንኑር በአንድ ላይ፣

ነገርኩሽ ከእንግዲህ ችላ አትበይ፡፡

በቅንነት ብንተሳሰብ ይሻለናል ለዘለቄታው፣

ኧረ ተይ አይሆንም ብያለሁ አያስፈልገንም ቱማታው፣

እስከዚህ ድረስ ነው ጨዋታው፡፡

አዝማች

ድምፃዊ፥ ጥላሁን ገሠሠ

ግጥም፥ ተዘራ ኃይለሚካኤል

1968 ዓ.ም.

### 4. ተመለሺ

ተመለሺ አንቺ ልጅ ተመለሺ፣

ተመለሺ ናፍቆቴ ተመለሺ፣

እኔን ብቸኛ አድርገሽ የት ትሄጃለሽ፣

አንቺ ልጅ ተመለሺ፡፡

ናፍቆቴ ተመለሺ፡፡

ጥፋቴን ልወቀው ይገለጥ ሚስጥሩ፣

እንዲህ ያስከፋት ምንድነው ነገሩ፣

እስኪ ጠይቁልኝ ምን እንደበደልኳት፣

እስኪ ጠይቁልኝ ምን እንዳስከፋኋት፣

ጥላኝ ሄደች ፍቅር እኔ እየወደድኳት፡፡

ወዳጅ ዘመዶቼ ምነው ዝም አትበሉኝ፣

ቆርጣ መሄዷ ነው የዛሬን ሸምግሉኝ፡፡

የዛሬን ሸምግሉኝ ምነው ዝም አትበሏት፣

አልቆረጠም ሆዴ ተይ ተመለሺ በሏት፡፡

የምታውቂው ዘመድ ታመመ ብላችሁ፣
ያቺን ልጅ በመላ አምጡልኝ እባካችሁ፡፡
እሷ ለታመመ ለሞተም ግድ የላት፣
እንድያው እሺ ብትል ነይ ተመለሺ በሏት፣
አመት ሁለት አመት የተዋደደ ሰው፣
ሦስትና አራት አመት የተፋቀረ ሰው፣
አራት አምስት አመት አብሮ የኖረ ሰው፡፡

ድምጻዊ፡- አያሌው መስፍን

ግጥም፡- አያሌው መስፍን

1969 ዓ.ም.

**5. ወጀብ ነው**

ወጀብ ነው ወጀብ፣
የዛሬው ዝናብ፡፡
አጀብ ነው አጀብ ወጀብ፣
ኦ የህልሜ ዝናብ፡፡
ጭለማው አልሳሳም፣
ገና ነው አልነጋም፡፡
ወገግ ሳይል ሌቱ፣
መጣደፌ ምነው፣
ወይ እኔ ለሁሉ
አልኩ እሪ በከንቱ፣
የትናንቱ ትንቢት
ሁሉም የጠበቀው፣
ተቀይሮ ሲገኝ
ጤና እንደመለመን፣
የነገውን ሳይ
የዛሬን ባስቻለኝ፡፡
እስኪ አስችለኝ ሆዴ ቀኑን እንድገፋው፣
ችዬ እንዳሳልፈው፣
መውደድ ማማረሩም መፍረድ ታግሶ ነው፣
የመጣም የሄደው አንዱ ባንዱ ሲስቅ፣
አንዱ አንዱን ሲነቅፍ፣
ብቸኩል ባይነጋም ለምን ልጣ እንቅፍፍ፣
አልነጋም ወይ ሌቱ፣
ገና ነው ሰዓቱ፣
አሃ
አልነጋም ወይሌቱ፣
አሄ
ገና ነው ሰዓቱ፡፡
አሃ
አልነጋም ወይ ሌቱ፣
አልነጋም ወይ
ወይ እሪ በከንቱ፡፡
አዝማች
የምሽቱን ትዳር ብጠላም ባማርረው፣
ብንጓም መንጋቱን፣
የልቤን የአሳቤም
ባይሞላም ብቸኩል ጊዜ አይስት ተግባሩን፡፡
ለኔ የከፋው ዘመን ጭለማ ነው ያልኩት፣
ግራ ያጋባኝ ወቅት፣
ሌላው ወዶት ነበር አለ ያልጠገበው፣
አዝኖ ያለፈበት፡፡
ተስፋ አትጣ ልቤ ታገሰው ይነጋል፣
ተወው ችዬ ልደር፣
የገፋም ይገፋል ተራ ዋንጫው አይቀር፡፡
እስኪ ልለይበት ጭለማና ብርሃን፣

ልለይ እየቆየሁ፣
አቀርቅሬ ልኑር ሳውቅ እየተሞኘሁ።
አልነጋም ወይ ሌቱ፣
ገና ነው ሰዓቱ፣
አሃ  አልነጋም ወይ ሌቱ፣
አሄ  ገና ነው ሰዓቱ።

ድምፃዊ፡- ይሁኔ በላይ
ግጥም፡- ፀጋዬ ደቦጭ
1985 ዓ.ም.

6. **ያስጠይቃል**

ኦሆ
እሀሀ
ኦሆ
እሀሀሀ
የሰራሽኝ ስራ
የሰራሽኝ በደል፣
የሚያከራርመን
የሚያኖርም አይደል።
እሀሀ ጧት ማታ፣
በዚህ ዓይነት ዘለቅናታ።
ያሰርሽውንም ካልተፈታ፣
በዚህ ዓይነት ከረምናታ።
ከረምናት( አሃሃ)
ከረምናት።
የሰራሽኝ ስራ ሲሰማሽ ጥፋትሽ፣
የገዛ ህሊናሽ ሲወቅስሽ መንፈስሽ፣
ትፀፀቻለሽ ኋላ ደሞ በስራሽ፣
ያሳየኝ ይሆናል አምላክ እግሬ ላይ ወድቀሽ፣
ትጠየቂያለሽ ደሞ አንቺም በተራሽ።
የትኛው ውበት ነው አሃ፣
እንዲህ ያኮራሽ፣
ያስጠይቃል አሃ፣
ያስጠይቃል አዎ፣
ያስጠይቃል አንድ ቀን።
ያስጠይቃል አይቀርም፣
ያስጠይቃል አንቺንም፣
ያስጠይቃል(4x)
መቼም ይሁን
ወይ በሰማይ ወይ በምድር፣
የት ይቀራል የሰው ብድር።
ጡር ነው
ኩነኔ ነው ፅድቅም የለውም፣
አጉል ፀሎት ለቅስፈት ነው፣
ኪሳራ ነው ትርፍም የለው፣
ያንቺ ፍቅር ዞሮ እዳ ነው።
ላንመለስ ብንወቃቀስ፣
ላንገናኝ ብንጠቃቀስ፣
የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ።
የኔን ተይው
ዛሬም እዛው ነሽ ወይ፣
ሁሌም እዛው ነሽ ወይ፣
የመውደድን ስሌት አታጠኚም ወይ፣
ፍቅርን ማብዛት እንጂ መቀነስ ነው ወይ፣
ያንቺ መውደድ ለኔ ማካፈል እያለ፣
ፍቅር ለመቀነስ ልብሽ ተቻኮለ።
አዝማች

እህህ ጧት ማታ፣

በዚህ ዓይነት ዘለቅናታ።

ያሰርሽውንም ካልተፈታ፣

በዚህ ዓይነት ከረምናታ።

ከረምናት( አሃሃ)

ከረምናት።

ገና ከጠዋቱ ፍቅራችን ሲወጠን፣

ለዚህ ነበር ለካ ቅብጥብጥ ያረገን፣

ይጣፍጥ ነበረ አጀማመራችን፣

አላማረም እንጂ ኋላ አጨራረሳችን።

አይወነጀልም ደርሶ መውደድ እንደገዳይ፣

ያስጠይቃል ፍቅር ሲግል የቃልኪዳን አጉዳይ።

ያስጠይቃል አዎ፣

ያስጠይቃል አንድ ቀን።

ያስጠይቃል አይቀርም፣

ያስጠይቃል አንቺንም፣

ያስጠይቃል(4)

መሽም ነጋም፣

ዛሬም እዳ ነገም እዳ፣

ውሃ መልስ ውሃ ቅዳ፣

ጉድ ነው።

ወይ አትሄድ ወይ አትመጣ፣

ዛሬም ያው ነሽ የልቤ ጣጣ፣

የሚያባጀኝ ልቤን ሰውሮት፣

ቁርጤን ልወቅ እስኪ ዘንድሮ፣

ባልመጣ እቃ ብቻ እያሽው፣

አገላብጠሽ ባልመረመርሽው፣

ሲጠይቁሽ ላትመልሽው፣

የኔን ተይው።

ዛሬም እዚያው ነሽ ወይ፣

ነገም እዚያው ነሽ ወይ፣

ሁሌም እዚያው ነሽ ወይ፥

የረጋ ውሃ ሁሌ ባለሽበት፣

አንዳንድ ቀን በጄ ብትይ ምናለበት፣

ብቻዬን ለሽክም ያንሁሉ መከራ፣

ምናለ ቢያዝንልኝ አንጀትሽ ቢራራ።

ዛሬም እዚያው ነሽ ወይ፣

ነገም እዚያው ነሽ ወይ፣

ሁሌም እዚያው ነሽ ወይ።

ድምፃዊ፦ ፀሐይ ዮሐንስ

ግጥም፦ ተመስገን ተካ

1985 ዓ.ም.

### 7. መስሎሻል

(አራፍ አይቸኩልም ረጋ እያሉ ጨዋታ አልበዛም)

በጣም በጣም በጣም፣

ያራዳ ልጅ ጥሎ አይጥልም፣

እያሉ ማጃጃል አልበዛም፣

በጣም በጣም በጣም።

የልብሽን ሰርተሽ ይቅርታ፣

ወግ አርገሽ ማሩኝ ጨዋታ፣

አይደል አይደል

ያንተ ነኝ እያሉ መደለል፣

እንደ ልጅ በጡጦ ማታለል፣

አይደል አይደል፣

አሹፊ ግዴለም መስሎሻል፣

ተጨዋች ነሽ በጣም መስሎሻል፣

የዋህ አግኝተሻል፣
ሲሉ ሰምተሻል፣
አራዶች ሲያረጉ አይተሻል፣
ይዛቃል ባካፋ መስሎሻል፣
ይታለባል አይዞሽ መስሎሻል፣
ሊበላ ሊፈቀድ መስሎሻል፣
አንከርፋኝ እንደ አሮጌ ጥላ፣
ነቃሁ እንጂ ከቀን በስተኋላ፣
ተለያየን እንዳይሆን ሆነና፣
ቆቅና ርግብ መች ይላመድና::
ልብ ያለህ ልብ በል፣
ልብ ያለህ ልብ በል(3)::
መወደድ ቅርስ ነው፣
ከቆንጆዎች ጓዳ፣
ውበት እንደ ሸቀጥ፣
አይወጣም አራዳ::
አንቺ ሰው በኔ ላይ እንዴት ሰው ያምርሻል፣
ጋደም ስልልሽ የተኛሁ መስሎሻል(2)::
መስሎሻል(2)
እንዳሞራ ልትበር፣
እጥፍ አርጋው ልትቀር፣
አነጣጥራ ልትመታ፣
የዐይኗን መረብ ዘርግታ፣
ያቺ ምላጭ ልትላጨኝ፣
እንደ ጋቢ ልትቋጨኝ፣
ገራገር ነው እያለች፣
ከሰው መሃል ስታጨኝ፣
የላጭን ልጅ ምን በላት፣
እንደሚሉት አይነት ነው::
መርዟን ልትረጭ እንደ እባብ፣
ተገናኘን ካብለካብ፣
ስታሻሽኝ ስታቅፈኝ፣
እንደ ቆዳ ልትገፈኝ፣
ልትደግስ ደስ ጥላ፣
ሞኙን ልቤን ልትበላ፣
አዝማች
በጥርስ እያሳቁ ሰው መግደል፣
ያፈቀረን ወዳጅ መበደል፣
አይደል አይደል፣
ፍቅር ነው ጨዋታ ወይ ጣጣ፣
ወደድኩህ እያሉ ለበጣ፣
አይደል አይደል፣
አንቺ ብልጥ እኔ ሞኝ መስሎሻል፣
እንደ ባዝራ ፈረስ መስሎሻል፣
ባሻ ምትጋልቢ::
ተነቃቃን ተለያን እስኪበቃን::
አላየሁ አልሰማሁ መስሎሻል፣
ዝም ያለ ሞኝ ነው መስሎሻል፣
ጥርሴ ቢስቅልሽ መስሎሻል፣
ፍቅር ሰጥተሽ ፍቅር ተቀበይ፣
እያሞኘሁ ከሰው ልኑር አጥበይ፣
በቁም ነገር እንዲያው ማፌዙን ተይ፣
ፌዝ ካማረሽ ሲመችሽ ብቅ በይ፣
ሲመችሽ ብቅ በይ(4)::
ባልተሟሸ ምጣድ ነገር እያሰፋሽ፣
አወኩ አወኩ እያልሽ አንቺ ሰው አጠፋሽ፣

አንቺ ሰው በኔ ላይ እንዴት ሰው ያምርሻል፣

እንዴት ሰው ያምርሻል፣

ጋደም ስልልሽ የተኛሁ መስሎሻል፣

የተኛሁ መስሎሻል፣

መስሎሻል(4)

እንደ አገዳ ልትመጠኝ፣

እንደ ወይራ ልትፈልጠኝ፣

እንደ ጥጧ ልትነድፈኝ፣

እንደ ሸማ ልትጠልፈኝ፣

ሙልጭ አርጋ ልታጥበኝ፣

ልታሰጣኝ ከደጇ፣

ገና እርጥብ ነው እያለች፣

ልታረገኝ ወዳጇ።

ጉም ሲበተን እያች፣

የጨሰ ነው ትላለች፣

አይኔን በጉም ከልላ፣

ጭስ ነው ብላ ልትበላ፣

የሞኝ ሰው ብልሃቱ፣

ተቀምጦ ከሳቱ፣

እፍ እያለ ሲያጋየው፣

የጨሰውን ማን አየው።

ድምፃዊ፡- ፀሐይ ዮሐንስ

ግጥም፡- ተመስገን ተካ

1985 ዓ.ም.

8. **ጎጆሽ ይሻላል**

እንደምነሽልኝ እንደምን ባክሽ፣

ከተማው ኑሮው እንዴት አረገሽ፣

ሁሉንም ትተሽ ተመለሽ፣

ውብ ዓለም እባክሽ፣

ጎጆሽ ይሻላል ንብረትሽ፣

የደሃው ትዳርሽ።

ሳስበው ትዝታሽ ሆነብኝ ስቃይ(2x)፣

የኔ ሀሳብ ትዝታዬ ተመለሽ ጎዳናዬ።

የማምናት ትዳሬ ውብ ዓለሜ፣

ከጥንት ያሳደኳት ውብ ዓለሜ፣

ከሀገር ከወገን ውብ ዓለሜ፣

አንድ አለችኝ ያልኳት፣

ጥላኝ ኮበለለች ውብ ዓለሜ፣

እኔ እየወደድኳት።

እኔስ ከማፍቀር፣

ከመንሰፍሰፌ ዋይ ከመውደድ በቀር፣

ቤቴን አፍርሳው ትጓዘዋለች አላልኩም ነበር።

እሷስ ቆርጣለች ለካስ ሄዳለች ዋይ በኔው ጨክና፣

ጨለማ አልብሳኝ ሃዘን አውርሳኝ ዋይ ቤቴን በትና።

የኔ ሀሳብ ትዝታሽ ሆነብኝ ስቃይ(2x)፣

የኔ ሀሳብ ትዝታዬ ተመለሽ ጎዳናዬ፣

የኔ ሀሳብ ትዝታዬ ተመለሽ ጎዳናዬ።

እንደምነሽልኝ እንደምን ባክሽ፣

ከተማው ኑሮው እንዴት አረገሽ፣

ሁሉንም ትተሽ ተመለሽ፣

ውብ ዓለም እባክሽ፣

ጎጆሽ ይሻላል ንብረትሽ፣

የደሃው ትዳርሽ።

እንደናት እንደሀት ውብ ዓለሜ፣

እያቀማጠልኩሽ ውብ ዓለሜ፣

የኔ ሚስጥረኛ ውብ ዓለሜ፣

ውብ ዓለሜ እያልኩሽ ውብ ዓለሜ፣

ጥለሽኝ የሄድሽው ውብ ዓለሜ፣

አሁን ምን በደልኩሽ ውብ ዓለሜ።

እቤት ስገባ የለችም ቢሉኝ ዋይ፣

እራሴን ስቼ፣

እንቦሳ ከብቱን ወይፈን በሬዬን በሜዳ ትቼ፣

አንቺን ፍለጋ በሰው ሀገር ላይ ዋይ ተንከራትቼ፣

እንባ እያፈሰስኩ ተመለስኩልሽ ዋይ አንቺን አጥቼ።

ሳስበው ትዝታሽ ሆነብኝ ስቃይ(2x)፣

የኔ ሀሳብ ትዝታዬ ተመለሽ ጎዳናዬ።

ድምፃዊ፦ ኤፍሬም ታምሩ

ግጥም፦ አበበ መለሰ

1985 ዓ.ም.

9. **ሀገሬ ሰው አጣሽ ወይ**

አንደኛው ስክብሽ አንዱ ያፈርስሻል፣

አንዱ ሲያስድግሽ አንዱ ይዘርፍሻል፣

አንዱ ሲሞትልሽ ደግሞ አንዱ ይሾምሻል።

ምንድነው ነገሩ ጥሩ ያልበቀለብሽ፣

ምንድነው ነገሩ ዘር ያልበቀለብሽ፣

አንቺ ደሀ አገሬ ኢትዮጵያ ዛሬ ማን ያስብሽ(2x)?

እስቲ ከራሴ ልጀምር ወቀሳ፣

ምን ሠራሁ ላገሬ ልጠየቅ ልነሳ፣

እስቲ ሁላችን ያብከንክን ይቆጨን፣

ከራብ ስደት ሌላ ምን ታሪክ አቆየን?

አ... ገና ሀገር ማለት ትርጉሙ አልገባንም፣

አ... የባንዲራ ኩራት ውሉ አልተረዳንም።

አ... እንደ ታሪካችን እንደ ጥንት ቀደምቱ፣

አ... ላንድነት እንጣር ወገኖቹ በርቱ።

ወንዝ እያለሽ አለማሽም፣

ልጅ እያለሽ አልተጦርሽም፣

ውለታሽስ ይሄ ነው ወይ?

ሀገሬ ሰው አጣሽ ወይ(3x)?

አዝማች

እስቲ ከራሴ ልጀምር ወቀሳ፣

ምን ሠራሁ ላገሬ ልጠየቅ ልነሳ፣

እስቲ ሁላችን ያብከንክን ይቆጨን፣

ከራብ ስደት ሌላ ምን ታሪክ አቆየን?

አ... አላከበርንሽም ወልደሽ አልጦርንሽም፣

አ... ወንዝ አለሽ ሀብታም ነሽ አላለማንሽም፣

አ... አጥፊ ልጆችሽ ነን ይቀር በይ ሰብስቢን፣

አ... ኢትዮጵያ እናታችን ማሪን አትርገሚን።

ወንዝ እያለሽ አለማሽም፣

ልጅ እያለሽ አልተጦርሽም ፣

ውለታሽስ ይሄ ነው ወይ፣

ሀገሬ ሰው አጣሽ ወይ፣

ሀገሬ አሳቢ አጣሽ ወይ ፣

ሀገሬ ልጅ አጣሽ ወይ፣

ሀገሬ አሳቢ አጣሽ ወይ?

ሀገሬ ሰው አጣሽ ወይ?

ሀገሬ አሳቢ አጣሽ ወይ?

ድምፃዊ፥ ነዋይ ደበበ

ግጥም፥ ነዋይ ደበበ

1985 ዓ.ም.

**10.ሰላም አይለየን**

ሰላም አይለየን ፍቅር አይለን፣

ፀጋህ አይለየን ጥላህ አይለየን፣

ፍቅር አይለየን መውደድ አይለየን፣

አምላኬ ሆይ

ባርክልን ኢትዮጵያን ያላንተስ ማን አለን።

ሰላም ይደርባት ፍቅር ይስፈንባት፣

ስምህ ይንገስባት ፀጋህ ይዝነብባት፣

ዘርተን እንቃምባት ወልደን እንሳምባት፣

አምላኬ ሆይ

ባርክልን ኢትዮጵያን ያላንተስ ማን አላት።

ከማያልቀው ሀብትህ ከማይጎለው ፍቅርህ ሰላም እንዘክራት፣

የኢትዮጵያን አምላክ ከሚመጣው ሁሉ ከክፉ ሰውራት፣

ከፍቅርህ ዛፍ ወጥታ የሰላምን ፍሬ እንድትመግባት፣

እጆቿን ዘርግታ ትማፀንሃለች አምላክ ጭንቋን ስማት።

አሳምረው መጨረሻውን ስጠን ሰላሙን።

ስትለምንህ እጆቿን ዘርግታ እስቲ ስማት ጌታ።

አምላኬ ሆይ በቃሽ በላት፣

ምህረትህን አትንፈጋት፣

የተባረከች መሬት የተቀደሰች ምድር፣

የሠላም ደሴት አድርጋት የተላበሰች ፍቅር።

የተመኘነው ይሁን ፀሎታችንን ስማን፣

በሰላም አሳድረን በቸር አውለን ባማን።

ፈጣሪያችን አልፋና ኦሜጋ ፍቅርን ስጠን ፀጋ፣ አባቴ ሆይ አልፋና ኦሜጋ ፍቅርን ስጠን ፀጋ።

አዝማች

ልጆቿ ተላምደው ተዋልደው ተዛምደው ሲኖሩ፣ ተሳስበው በአንድ መዓድ ዙሪያ የፍቅሯን እንጎቻ ሲበሉ ተሻምተው፣

የሀገር ልጅ በፍቅር ተሳስቦ ተዛዝኖ የመኖሯን ባህል፣

አታሳጣት ጌታ ሰላምና ደስታ አይራባት እንደ እህል።

ሀገራችን የሁሉም አድባር ናት እምዬ የኛ እናት፣

ስትለምንህ እጆቿን ዘርግታ እስቲ ስማት ጌታ፣

አምላኬ ሆይ በቃሽ በላት፣

ምህረትህን አትንፈጋት፣

የሰላም ምድረገነት የሰው ልጆች አብነት፣

አስታጥቃት በዙሪያዋ የፍቅርን መቀነት፣

የምንዋደድ ያድርገን የማይለየን ፍቅር፣

አንተው ጠብቀን ጌታ ከለላ ሁነን አጥር።

ፈጣሪያችን አልፋና ኦሜጋ ፍቅርን ስጠን ፀጋ፣

አባቴ ሆይ ልጆችህ ነንና አውጣን ከፈተና፣

ፈጣሪያችን አልፋና ኦሜጋ ፍቅርን ስጠን ፀጋ።

አባቴ ሆይ ልጆችህ ነንና አውጣን ከፈተና።

ድምፃዊ ፀሐይ ዮሐንስ

ግጥም፡- ተመስገን ተካ

1985 ዓ.ም.

## 11.ገዳይ ነሽ ገዳይ

እኔ እንደ ጀግና፣ ሽጉጥ ታጥቄ፣ ሽጉጥ ታጥቄ፣

ቀረሁኝ ወድቄ።

እኔ እንደ ጀግና፣ ብረት አንግቼ፣ ብረት አንግቼ፣

ቀረሁኝ ተረትቼ፤

እህህ ካቃተኝ(2x)፣

አዝነሽ ብተዪኝ፤

እህህ ካቃተኝ(2x)፣

አዝነሽ ብተዪኝ፤

ተይ ገዳዬ፣ ቤልጂግና ጓንዴ፣

ተይ ገዳዬ፣ ሰናድሩ እያለኝ፣

ተይ ገዳዬ፣ አረታኝም ብረት፣

ተይ ገዳዬ፣ ፍቅርሽ ነው የጣለኝ፣

ተይ ገዳዬ፣ ተጠቂ ነኝ ብዬ፣

ተይ ገዳዬ፣ የመውደድ ተበዳይ፣

ተይ ገዳዬ፣ እንዴት ሽንጎ ላውጣ

ተዪ ገዳዬ፣ ፍቅርን ያህል ጉዳይ።

ተኩሼ ባልመታ፣ ባይጥልም ለበኔ፣

እጄን ሰጠ ብለሽ፣ ዝና አታፍሪ በኔ።

ዝናር ቢጠቀለል፣ ቢዞር በወገቤ፣

እንዳንቺ ያለ ገዳይ፣ መች ይችላል ልቤ፣

እህህ ገዳይ ነሽ ገዳይ(2x)፣

አዝማች

ተይ ገዳዬ፣ መንፈሴም ይረበሽ፣

ተይ ገዳዬ፣ሆዴንም ይጭነቀው፣

ተይ ገዳዬ፣ ቆብ ሊጥል አይደለም፣

ተይ ገዳዬ፣ ብረት የታጠቀው፤

ተይ ገዳዬ፣ በጦር አልተወጋሁ፣

ተይ ገዳዬ፣ አልተመታሁ ባልቤን፤

ተይ ገዳዬ፣ ወትሮም ለመውደድ ነው፣

ተይ ገዳዬ፣ የሰጠሁት ልቤን።

ሆድ እንዳይቆርጥ እንጂ፣ ሚዛን አጥቶ ፍርድሽ፤

ቢያስርም ቢፈታኝም፣ ይዞኛል መውደድሽ።

ፍቅርሽ ቢወነጀል፣ ምን ሊባል ነው ክሱ፣

ያለምኩበት እኔ፣ የገደለኝ እሱ።

እህህ ገዳይ ነሽ ገዳይ(2x)፣

አዝማች

ተይ ገዳዬ፣ ቤልጂግና ጓንዴ፣

ተይ ገዳዬ፣ ሰናድሩ እያለኝ፣

ተይ ገዳዬ፣ አልረታኝም ብረት፣

ተይ ገዳዬ፣ ፍቅርሽ ነው የጣለኝ፤

ተይ ገዳዬ፣ ተጠቂ ነኝ ብዬ፣

ተይ ገዳዬ፣ የመውደድ ተበዳይ፤

ተይ ገዳዬ፣ እንዴት ሽንጎ ላውጣ

ተዪ ገዳዬ፣ ፍቅርን ያህል ጉዳይ።

ተኩሼ ባልመታ፣ ባይጥልም ለበኔ፣

እጄን ሰጠኝ ብለሽ፣ ዝና አታፍሪ በኔ፣

ዝናር ቢጠቀለል፣ ቢዞር በወገቤ፣

እንዳንቺ ያለ ገዳይ፣ መች ይችላል ልቤ።

እህህ ገዳይ ነሽ ገዳይ(3x)።

ድምፃዊ፡- ኤፍሬም ታምሩ

ግጥም፡- ይልማ ገብረአብ

1985 ዓ.ም.

## 12.ቀን ሲጥል

አስታውሼሻለሁ ትናንትናም ዛሬም፣

አነሳሳሻለሁ ትናንትናም ዛሬም፣

ጭብጥ ኩርምት አልኩኝ፣ናፍቆትሽን አዝዬ፣

ማለፉ አይቀር ብዬ፣

ጭብጥ ኩርምት አልኩኝ፣ናፍቆትሽን አዝዬ፣

ማለፉ አይቀር ብዬ::

ቀኑ እንደመጨለም፣ በኔው ላይ አለብኝ፣

አድማስ ዳመናውን፣ በኔው ላይ ጣለብኝ፣

ደጉን ቀን ያምጣልኝ፣

እንኳን ጊዜው መሽቶ፣ ሌቱም አይነጋልኝ፣

ብራ ባረገልኝ፣

እንኳን ቀን ታክሎ፣ ሌቱም አይነጋልኝ::

ደግሷል ይህ ሰማይ ለማታው፣

በርክቷል በጊዜ ጉምታው፣

ሊጥል ነው እንግዲህ ፍቅርሽ በፋንታው፣

ቀዝቀዝ እያለብኝ መኝታው፣

ስፍስፍ እያረገኝ ትዝታው፣

ባየሽው ናፍቆትሽን መንፈሴን መታው::

ጀምበር በጠዋቱ፣ ገና በንጋቱ ተሸፍና በጉም፣

አየሩ ቀዝቅዞ፣ ዳመናው አግቶ ዙሪያው ሲያጎመጉም፣

በማለዳ አካፍቶ፣በቀንም በርተቶ ዶፉን እየጣለ፣

እንዳጣ መድረሻ፣ እንደ ሆደ ባሻ እኝኝ ሲል ዋለ::

ሁሉን አቀዝቅዞ፣አገሩ ሲያካፋ፣ አገሩ ሲያካፋ፣

ሰማይም እህ ሲል እንደ ሰው ሲከፋ፣ እንደ ሰው ሲከፋ፣

ዐይን አላየም እንጂ በሌት በጨለማ፣ በሌት በጨለማ፣

እንዲያው በረዶ ነው ቀን የጣለውማ፣ ቀን የጣለውማ::

የሚያዳምነው፣

የሚያጨግገው፣

ኧረ ነይ ናፍቆትሽ ነው፣ ቀኑን ያጨለመው::

ኧረ ነይ ናፍቆትሽ ነው፣ ቀኑን ያጨለመው::

ቻልኩት ናፍቆትሽን፣

ቻልኩት ናፍቆትሽን፣

ዓለሜ አልቻልኩም ትዝታሽ ገደለኝ፣

ዓለሜ አልቻልኩም ትዝታሽ ገደለኝ፣

አዝማች

ወሸባው ሲጋረፍ ሽውታው፣

ደጃፉን ወጨፎ ሲመታው፣

ብርዱን ሲያሳልፈው ሰው በመኝታው፣

የኔም ቤት ተብሎ ቀዝቃዛው፣

ጎኔን ጣል አደረኩ ካጎዛው፣

ይረግፋል ልቤ ላይ፣ የኔ ሃሳብ ቤዛው::

ትላልቅ አዳራሽ አላሰብኩም ጭራሽ፣ ሆዴም አላለመ፣

መች ጠበበኝ ፍቅርሽ፣ ይበቃኛል ልብሽ፣ እዚያው ከከረመ፣

እንግዲህ ለሌላው አካሌ እንዲደላው ካሰብሽልኝ ለኔ፣

ኩርማን አንጀት ስጪኝ ከሆድሽ አኑሪኝ ስፍራ አይፈጅም ጎኔ።

ያሳር ምድር ሆኖ ሲያቀረዝዝ ጤዛ፣ ሲያቀረዝዝ ጤዛ፣

ያዘለው ጠብ ሲል ሲረግፍ እንደ ዋዛ፣ ሲረግፍ እንደ ዋዛ፣

ያንጊዜ ሲያራርቅ ሰው ከሰው ነጥሎ፣ ሰው ከሰው ነጥሎ፣

ብራ አልሆን እያለ ሲያስጨንቅ ቀጥሎ፣ ሲያስጨንቅ ቀጥሎ፣

ወይ ሲያነጣጥር፣ ወይ ሲነጣጥል፣

ወይ ሲያነጣጥር፣ ወይ ሲነጣጥል፣

ለካ እንዲህ ያስቀይማል፣ያስጠላል ቀን ሲጥል፣

ለካ እንዲህ ያስቀይማል፣ያስጠላል ቀን ሲጥል፣

ወይ ሲያነጣጥር፣ ወይ ሲነጣጥል፣

ወይ ሲያነጣጥር፣ ወይ ሲነጣጥል፣

ለካ እንዲህ አለያይቶ፣ያስቀራል ቀን ሲጥል(2x።

ድምፃዊ፦ ኤፍሬም ታምሩ

ግጥም፦ አክሊሉ ስዩም

1985 ዓ.ም.